

የብዝሃነት አስተዳደር እና የመንግስታት ግንኙነት ለጠንካራ የፌደራል ስርዓት ግንባታ

ከ 21 ኛ የኢትዮጵያ ብሄር፤በሄረሰቦች እና ህዝቦች ቀን በዓል አከባባር አስተምህሮ መወያያ ሰነድ

መስከረም/2019

አዲስ አበባ

1. መግቢያ

የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች መብት መከበር ሕገ መንግሥታዊ ዋስትና ያረጋገጠው የኢፌዲሪ ሕገመንግሥት የጸደቀበትን ቀን ህዳር 29 በየዓመቱ በተለያዩ ሁነቶች ላለፉት 20 ዓመታት ሲከበር ቆይቷል። በ 2019 ዓ.ም ለ 21 ኛ ጊዜ "በብዝሃነት የደመቀች በምክክር የጸናች ኢትዮያ " በሚል መሪ ቃል ይከበራል። ይህንን በዓል ምክንያት በማድረግ የብዝሃነት አስተዳደር እና የመንግስታት ግንኙነት ምንነት ፤አስፈላጊነት፣ ባህሪያት እና ለጠንካራ የፌደራል ስርዓት ግንባታ በሚኖራቸዉ ሚና ዙሪያ የሚያጠነጥን ሰፊ የአስተምህሮ ሥራ ለመሥራት ታቅዷል።

ብዝሃነት የደመቀ ሁኖ የሚቀጥለዉም ሆነ ምክክሩ የጸና ሀገር የሚገነባዉ በጠንካራ በህብረ በሄራዊ ፌደራላዊ ስርዓቱ ማእቀፍ የፌደራሉም ሆነ አባል መንግስታት እንዲሁም ማህበረሰቡ ብዝሃነትን በመስተዳደር እና ለሃገረ መንግስቱ ግንባታ ወሳኝ በሆነዉ የመንግስታት ግንኙነት ዙሪያ ሳይንሳዊ እና ተቀራራቢ የሆነ አረዳድ ሲኖረን እና ለተግባራዊነቱ ተፈላጊ የሆኑ አስተሳሰቦችን መላበስ ሲቻል ነው። ስለሆነም ይህ የሥልጠና ሰነድ በህብረ በሄራዊ ፌደራላዊ ስርዓት ብዝሃነትን ማስተዳዳር እና የመንግስታት ግንኙነት የደመቀ ብዝሃነት እና ጠንካራ ሀገረመንግስት ግንባታ ያላቸዉን ተያያዥና ወሳኝ ሚና በዝርዝር ይተነትናል።

ሰነዱ በዘርፉ የተካሄዱ ጥናቶችን እና በሥልጠና እና በምክክር መድረኮች የተገኙ ግብዓቶችን እና ከዘርፉ ጋር ተያያዝነት ያላቸውን ማጣቀሻ ጽሑፎች መሠረት ተደርጎ ተዘጋጅቶ የቀረበ ነው።

ከአሠልጣኖች ሥልጠና በኋላ በሚኖሩ ሥልጠናዎች ክልሎች እና የከተማ አስተዳደሮች የሰነዱን ጭብጥ መሠረት አድርገው የአካባቢያቸውን ተጨባጭ ሁኔታና ተሞክሯቸውን በማካተት ሊያዘጋጁት እና ሊያቀርቡት ይችላሉ።

2. የሰነዱ ዓለማ፣

በአገራችን ህብረ ብሄራዊ ፌደራላዊ ሥርዐት የብዝሃነትን አስተዳደር እና የመንግስታት ግንኙነትን ስርዓትን በመዳበር ጎብረ ብሔራዊ አንድነት ሥር እንዲሰድና እንዲዳብር ሰፊ የአስተምሮ ሥራ መሥራት ነው።

ክፍል 1፣ የብዝሃነት አስተዳደር

1.1. የበዝሃነት ምንነት

ብዝሃነት ከሰዉ ልጆች ተፈጥሮ ለምሳሌ ወንድና ሴት ሆኖ መፈጠር ፤ የማህበራዊ እና ባህላዊ መገለጫዎች ብዝሃ መሆን ለምሳሌ የተለያዩ ቋንቋዎች፤ ባህሎች፤ እሴቶች ወዘተ-- መኖር ጋር ተያይዞ በአንድ መንግስታዊ አስተዳዳር ዉስጥ የሚኖሩ ማህበረሰቦች መካከል የሚታዩ የመህበረሰቡን ብዝሃ መገለጫዎች መኖር የሚያመላክት ነዉ።

የብዘሀ ማንነት ጉዳይ እና አጀንዳ ከጥንት ጀምሮ ያለና የነበረ ቢሆንም ከሁለተኛ የአለም ጦርነት ማብቂያና እና በአለም ላይ ከ 1950 እና 1960 ዎቹ በኋላ የቀጥታ ቅኝ አገዛዝ ከማክተሙ ጋር ተያይዞ በ 21 ኛዉ ክ/ዘመን ብሄርተኝነት እና ሀይማኖተኝነት እየተቀነቀነ በመምጣቱ የብዘሀነት ማንነት መብቶች ማለትም እንደ ቋንቋ፣ ባህል፣ ራስን በራስ ማስተዳደር፣ የዉክልና የእምነት እና የህይማኖት ነፃነቶች በአጠቃላይ እዉቅና ጉዳይ ገፍቶ በመምጣቱ ብዘሀነት መገለጫ በሆኑባቸዉ ሀገራት ይህን በአግባቡ ማስተዳደር የመንግስታት የፖለቲካ እና የአስተዳደር ስርአት ጉዳይ እየሆነ መጥቷል።

በተወሰኑ ጉዳጉች ላይ አብዛኛዉ ማህበረሰብ ተቀራራቢ የሆኑ መገለጫዎች ኑረዉት የተወሰኑ አናሳ ቁጥር ያላቸዉ የማህበረሰቡ ክፍሎች የተለየ መገለጫዎች ሲኖራቸዉ የብዝሃነት ጉዳይ የአናሳ ቁጥር ያላቸዉ ማህበረሰቦች አያያዝ/ መብት በሚል ሲገለጽ የቆየ ሲሆን ጉዳዩም የእኩልነት መብትን በማረጋጋጥ ከዚም አለፍ ሲል ማግለልን የሚከለክሉ ህጎች በማዉጣት በዚህ ማእቀፍ ብዘሃነት ሲስተናገድ የቆየ እና በብዙ ሃገሮችም ይህኑ ለመተግበር ጥርት ሲደረግ ይስተዎላል። ይህም በዋናናት አናሳ ቁጥር ላላቸዉን ማህብሰቦች እንደ ማህበረሰብ የሚመለከት ጉዳይ ሳይሆን በዋናነት የማህበረሰቡ አባል የሆነዉን ግለሰብ የሚመለከት እና ግለሰቡ በማንኛዉም ሁኔታ የእኩልነት መብቱ እንዲከበርለት የማረጋጋጥ እና ማግለል እና መድልኦ እንዳይፈጸምበት መከላከልን መሰረት ያደረገ ነዉ። ይህ ጉዳይ አለማቀፋዊ ቅቡልነት እያገኘ የመጣ እና በተለያዩ የተባባሩ መንግስታት ዲክላሪሽኖች እና ኮንቬሽኖች የጋራ መግባባት የተፈጠረበት ሲሆን ዴሞክራሚያዊ የሆነ ህገመንግስት ያላቸዉ ሃገሮችም የሕገመንግስታዊ ድንጋጌዎቻቸዉ አካል እየሆነ መጥቷል። በሀገራችን በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገመንግስት አንቀጽ 25 የእኩልነት መብት ስር እንደሚከተለዉ ተደንግጓል "ሁለም ሰዎች በህግ ፊት እኩል ናቸዉ፤ በመካከላቸዉም ማንኛዉም አይነት ልዩነት ሳይደረግ በህግ እኩል ጥበቃ ይደረግላቸዎል።በዚህ ረገድ በዘር፤ በብሄር፤ በሄረሰብ፤ በቀለም፤ በጾታ፤ በቋንቋ፤ በፖለቲካ በማህበራዊ አመጣጥ፤በሃብት፤በትዉልድ ወይም በሌላ አቋም ምክንያት ልዩነት ሳይደረግ ሰዎች ሁሉ እኩልና ተጨባጭ የህግ ዋስትና የማግኘት መብት አላቸዉ"

ከዚህ ጋር ተያይዞ አከራካሪ የሆነዉ ጉዳይ የአንድ አናሳ ቁጥር ያለዉ ማህበረሰብ አባል የሆነ ግለሰብ በግለሰብ ደረጃ የእኩልነት መብት ማረጋጋጥ እና ከአድሎ እና መገለል መከላከል ለግለሰቡን በርግጥ የእኩልነት መብቱን ያረጋግጥለታል ወይ ከአድሎና ከመገለል ይከላከልለታል

ወይ የሚለዉ ጉዳይ ነዉ። ማህበረሰቡ እንደ ማህበረሰብ በመንግስታዊ አስተዳዳሩ እንደሚኖሩ ሌሎች ማህበረሰቦች የማህበረሰቡ መገለጫዎች የሆኑ ቋንቋ፤ባህል፤ታሪክ፤ ወዘተ.. እኩል ቦታ ካላገኙ ይህ ባልሆነበት ሁኔታ እንዴት ብሎ ነዉ የማህበረሰቡ አባል የሆነ ግለሰብ የእኩልነት እድል የሚረጋገጥለት እና ከመገለል እና መድሎ መከላከል የሚቻለዉ ፣ እኩል መነሻ ሁኔታዎች በሌላቸዉ ሁለት ግለሰቦች መካከል እንዴት ነዉ የእኩልነት መብትን ማረጋገጥ የሚቻለዉ የማህበረሰቡ ባህልና ቋንቋ የመንግስታዊ አስተዳዳሩ አንድ መገለጫ ባልሆነበት ሁኔታ መድሎና መገለልን እንዴት መከላከል ይቻላል የሚሉትአናሳ ቁጥር ካላቸዉ ቡድኖ አያዝ ጋር ተያይዞ ሰፊ ዉይይት እየተደረገባቸዉ የቀጠሉ ሲሆን ጉዳዩ አናሳ ቁጥር ካላቸዉ ቡድኖች አያያዝ ወደ የብዝሃነት አያያዝ ወይም አስተዳዳር ወደሚል ከፍ ያለ ሃሳብ ዕያደገ የመጣበት ሁኔታ ይታያል ።

በ 21 ኛው ክፍለ ዘመን፣ ውጤታማ የሆነ የብዝሃነት አስተዳደር (አያያዝ) መኖር መሠረታዊ እና አስፈላጊ ጉዳይ ነው። ይህም የእያንዳንዱ ግለሰብ መብት እንዲከበር፣ እኩል ዕድል እንዲያገኝ እና በሀገሩ ጉዳይ ላይ እኩል ባለቤት ሆኖ እንዲሳተፍ ያረጋግጣል።

የብዝሃነት አስተዳዳር ብዝኅነት መገለጫቸው የሆኑ የተለያዩ ማኅበረሰቦችን በአብሮነት ለማስቀጠል (ወደ አንድ ለማምጣት) እና ተቻችለው ለመኖር እንዲችሉ ዴሞክራሲያዊ የሆነ ግንኙነት እና አካታች የሆነ ሥርዐት አስፈላጊ መሆኑን መሰረት ያደረገ እሳቤ ነዉ።

በአሁኑ ዘመን ዴሞክራሲን ከማስፋት ጋር ተያይዞ ሊኖሩ የሚችሉ ተግዳሮቶች በዋናነት ብዝኅ ማንነትን ማስተናገድ ላይ የሚመሠረቱ ናቸው። በዓለም አቀፍ ደረጃ ዴሞክራሲን ለማስፋት ከሚገጥሙ ተግዳሮች መካከል ብዝኅነት መገለጫቸው በሆኑ ማኅበረሰቦች ውስጥ የሚኖሩ የተለያዩ ፍላጎቶችን በአብላጫ ዴሞክራሢ መንገድ ብቻ አግባብ ማስተናገድ አለመቻል ነው።

ብዘሀነት በባህሪዉ አነስተኛ ቁጥር ያላቸዉ ቡድኖች ከመኖራቸዉም በላይ እንደ አጠቃላይ አብላጫ ቁጥር 50 በመቶ በላይ ያለዉ ክፍል በአብዛኛዉ ስለማይኖር የአብላጫ ዴሞክራሲ ቡድኖችን የተገለሉ ስለሚያደርግ እና ዉሳኔ ዎች ላይ የነሱን ፍላጎቶች የሚካተቱበት እና የዉሳኔዉ አካ የሚሆኑበትን አግባቡ ማስተናገድ ባለመቻሉ ሌላ ገፅታ ያለዉ የመግባባት ዴሞክራሲ እየተቀነቀነ ለመምጣቱ እንደ ምክንያት ይወሰዳል።

በዓለማችን የዘመናዊ መንግሥታት ታሪክ ብዝኅነት መገለጫቸው የሆኑ ማኅበረሰቦች ፌዴራል ሥርዐትን እና ዴሞክራሲን አስተሳስረው የተገበሩ፣ ብዝኅነታቸውን ጠብቀው ጠንካራ አገራዊ አንድነት የገነቡና የማኅበረሰባቸውን ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ እድገት ማሳካት የቻሉ ናቸው።

ለምሳሌ፦ ሲዊዘርላንድ፣ ቤልጀየም፣ ካናዳ፣ ህንድ፣ ስፔን፣ ማሊዥያና ብራዚል ተጠቃሾች ናቸው።

ይሁን እንጂ የፌዴራል ሥርዐትን በሕገመንግሥታቸው ቢደነግጉም ብዝኀነትን ዴሞክራሲያዊ በሆነ አግባብ ማስተናገድ ተስኗቸው መጨረሻቸው የፌዴራል ሥርዐቱን ወደ መሀል እና ወደ ዳር ጎታች በሆኑ አክራሪና ጸረ ዴሞክራሲ ኃይሎች ጫና መፍረስና መለያየት የመጨረሻ እጣ ፋንታቸው የሆኑ አገራት እንደ ነበሩ ይታወቃል።

ለምሳሌ፦ የቀድሞው ሶቭየት ዩኒን እና የምስራቅ አውሮፓ ፌዴሬሽኖች፣ በድህረ ቅኝ ግዛት በምስራቅ፣ በማዕከላዊ እና በምዕራብ አፍሪካ ተፈጥረው የነበሩ የተለያዩ ፌዴሬሽኖችን መጥቀስ ይቻላል።

በመሆኑም ከአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ እና ማኅበራዊ ውቅር አንጻር ብዝሃነትን በአግባቡ በማስተዳደር ዴሞክራሲያዊ የሆነ ኅብረብሔራዊ ፌዴራል ሥርዐትን ለመገንባት የሚያስችሉ ተቋማትን እያጠናከሩ፣ የአሠራር ሥርዐቶችን እየዘረጉ፣ በአፈጻጸም ሂደት የሚጋጥሙ ተግዳሮቶችን ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሕገመንግሥታዊ ሥርዐቱን ተከትሎ፣ ሥርዐቱን በሚያጠናክር መልኩ በወቅቱ እየፈቱ ጠንካራ አካታች እና ሁሉም የኔነው የሚለው አገረ መንግሥት እየገነቡ መሄድ የሁላችንም ኃላፊነት እና ግዴታ ነው።

ብዝሃነትን የሚያስተናግድ አንድነትን መገንባት ትልቅ የፖለቲካ ጥበብን ይጠይቃል የሕብረብሔራዊነትን ነባራዊ ሁኔታ ተቀብለው ፈተናውን ያለፉ ጥቂት ሃገራት ሲሆኑ ነባራዊ ሁኔታዉን ባለመቀበል የተለየ ሁኔታ ለመፍጠር

-መዋጥ (assimilation) ፣

-በኃይል ማፈናቀል፣

-እጅግ በከፋ ሁኔታ ጫፍ ሲይዝ ደግሞ የተለየ ማንነት ለማጥፋት በመንቀሳቀስን

ወጥ ማህበረሰብ ለመፍጠር የሞከሩ ቢኖሩም ሙከራዉ ያልተሳካ ሲሆን በ 21 ኛዉ ክፍለዘመን ደግሞ ብዝሃነትን በአግባባ ከማስተናገድ ዉጭ የሚታሰቡ አማራጮች ሊሆን አይችሉም። ይህ ከሆነ እስከ አሁን ብዝሃነትን በአግባቡ ለማስተዳዳር ያሉ የአደረጃጀት እና አሰራር ስርዓቶችን መፈተሽ ተገቢ ነዉ። መሳሪያዎች

1.2. ብዝሃነትን ለማስተዳደር ጥቅም ላይ ሊዉሉ የሚዉሉ የፖለቲካ እና የአስተዳዳር ስርአቶች

1.2.1 የፌደራል ስርዓት እንደ አንድ ብዝሃነትን የማስተዳደሪያ ስርዓት

የፌዴራል ሥርዓት ብዝሃነት መገለጫዉ በሆነበት ማኅበረሰብ ውስጥ ብዝሃነትን ለማስተናገድ እካታች እና ሁሉን አቀፍ የሀገር ግንባታን ለማጠናከር ከሚያገለግሉ የመንግሥት አስተዳደር ዘይቤዎች አንዱ ነው። ከዚህ አንጻር ለብዝሃነት አስተዳደር ምሁራዊ መሠረት የጣሉት ዊሊያም ሊቪንግስተን (1956) ሲሆኑ፣ እሳቸውም በፌዴሬሽኖች ውስጥ ብዝሃነት ለማስተናገድ ጫና የሚያደርጉ የማኅበራዊ ኃይሎችን መኖር የሥርዓቱን ባህሪ እንደሚወስኑ አጉልተው አሳይተዋል። WATTS (2008) እንዳመለከቱት፣ በእነዚህ ማኅበራዊ ኃይሎች እና በፖለቲካ ተቋማት መካከል ያለው የእርስ በእርስ ግንኙነት በዓለም ዙሪያ ያሉ ፌዴሬሽኖች ምስረታ፣ ልዩ መዋቅር እና ቀጣይነት ያለው አሠራር ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ አሳድሯል።

በፌዴሬሽኖች መካከል ያለው የውስጥ ብዝሃነት ባሕርይ ስለሚለያይ፣ እነዚህን ብዝሃነቶች ማስተዳደር ወሳኝ ነው። በተለይም ቋንቋዎች የባህል መሠረት በመሆናቸው እና መንግሥታት ደግሞ ከባህል አንጻር ገለልተኛ መሆን ስለማይችሉ ብዝሃነትን ማድተዳዳር የግድ ይላቸዋል። የፌደራል ስርዓት ከመነሻዉ በህዝቦች መፈቃቀድ፤ ስምምነት እና የጋራ ርዕይ ስለሚመሰረት እና ስልጣንን ህገመንግስራዊ በሆነ አግባብ ስለሚከፋፍል በዝሃ የሆነ የመህበረሰቡ ክፍሎች በራስ አስተዳደር እና በጋራ አስተዳደሩ እንዲሳተፉ እና ተለያያ የማህበረሰቡ ክፍሎች ቋንቋቸዉን፤ በህላቸዉን የሚገልጽበት የፖለቲካ ምህዳር እንዲገኙ በማስቻል ብዝሃነት የሚስናገድበት የአስተዳደት ስርዓት ለማበጀት ያስችላል። ብዝሃነቶች ማስተዳደር አሳታፊ እና አስተማማኝ ሀገር ለመገንባት እና ለመምራት ወሳኝ ጉዳይ ይሆናል።

ብዝሃነት መገለጫቸዉ በሆኑ ፌደሬሽኖች ለብዝሃነት እዉቅና በመስጠት የብዝሃነት መገለጫ የሆኑ ቋንቋ ፤ባህል እና ሃይማኖት ማስተናገድ የሚያስችል ሁኔታዎችን በመፍጠር ሁሉንም አካታች የሆነ የሁሉም መብት አንጻራዊ በሆነ መልኩ እኩል የሚከበርበት እና የእኩል ተጠቃሚነት እድል እየተረጋገጠ የሚሄድበት ሰርዓት በመፍጠር መቻል እና አፍራሽ ከሆነ የዉድድር ስሜት በመዉጣት በትብብር እና በመፈቃቀድ ላይ የተመሰረተ ግንኙነትን በሚያጠናክር መልኩ ብዝሃነትን ማስናገድ መቻል ለህብረ,ብሄራዊ-ፌደሬሽኖች ሰኬታማ መሆን ወሰኝ ጉዳይ ነዉ

በየትኛውም አገር ውስጥ በተለያየ እይታ የሚገለጹ የብዝኃነት መገለጫዎች እንዳሉ ብዙዎች ይስማማሉ። ስለዚህ የትኛውም አገር በውስጡ የሚታዩ የብዝኃነት መገለጫዎች በተለይም ወሳኝ የሆኑ የማንነት መገለጫዎች ተብለው የሚገለጹ የቋንቋ፣ የሃይማኖት፣ የባህል፣ የታሪክና የመሳሰሉ መገለጫዎች ይኖሩታል። አገራት ለእነዚህ የማንነት መገለጫዎች ዕውቅና ይሠጣሉ፤ ዕውቅናውም በፌዴረሽኖች ከሕገመንግሥት መግቢያ ጀምሮ የቃላት አጠቃቀምን ባካተተ መልኩ የተለያዩ እርምጃዎችን በመውሰድ ብዝኃነትን ያንጸባርቃሉ። ብዝኃነትን የማስተናገድ ጉዳይ ዴሞክራሲያዊ ፌዴራላዊ ሥርዐት የሚከተሉ አገራት ቁልፍ አጀንዳ ነው። ይህም ብዝኃነትን በብቃት ለማስተናገድ የሚችል ፌዴራላዊ ዴሞክራሲን የመገንባት ጉዳይ ነው። አንዳንድ አገራት ይህንን ብቃት አስጠብቆ ለማስቀጠል በብዝኃነት አያያዝ ዙሪያ የሚታዩ ችግሮችን በተከታታይነት በጥናት

በመለየት መፍትሔዎችን ያቀርባሉ፣ የፖለቲካ ሊህቁም በዚህ ጉዳይ በጥልቀት በመወያየት ብቃቱን እያሻሻለ እንዲሄድና ለአዳጊና ተለዋዋጭ ሁኔታዎች የሚመጥን ዕይታ እያጎለበተ እንዲሄድ ይደረጋል።

ኅብረብሔራዊ የፌዴራል ሥርዐት የሚከተሉ አገራት በሕገመንግሥቶቻቸው መግቢያ ጀምሮ ኅብረብሔራዊነትን ያንጸባርቃሉ። ለምሳሌ የስዊዝን ሕገመንግሥት ያየን እንደሆነ በሕገመንግሥቱ መግቢያ ካንቶኖች ለኅብረብሔራዊ የፌዴራል ሥርዐት በተለይም ብዝኃነትን ከመቀበልና ከማቀፍ አንጻር ቁርጠኝነታቸውን ያሳዩ ሲሆን፣ በዚሁ መሠረት ብዝኃነታቸውን በማክበርና በጋራ ለመኖር ከመወሰናቸውም አልፈው አንዱ ሌላኛውን በማክበርና በእኩልነት ለመኖር ቃልኪዳን መግባታቸውን ገልጸዋል። ይህም በስዊዝ ሕገመንግሥት መግቢያ ላይ የተገለጸው ለኅብረብሔራዊነት ወይም ለብዝኃነትና ለእኩልነት የተሰጠውን ቦታ ያንጸባርቃል። ለዚህም ነው ፍሊነር የተባሉት ምሁር ልክ እንደ አሜሪካ ሕገመንግሥት "እኛ የአሜሪካ ሕዝብ..." በማለት ካንቶኖች የስዊዝ ፌዴሬሽን የወጡነት መፍትሔን አልተከተሉም ብለው ይገልጻሉ። ይልቁንስ "የካንቶኖች ሕዝቦች" በማለት ይገልጻሉ። በተመሳሳይ መልኩ የስፔን ሕገመንግሥት በመግቢያው ብዝኃነትን በብዙ ቁጥር የተቀበለ ሲሆን፣ በዚሁ መሠረት ሕገመንግሥቱ "አገረ-ስፔን ሁሉንም ስፓኒያርዶችንና ሁሉንም የስፔን ሕዝቦች ሰብዓዊ መብቶችን፣ ባህሎቻቸውን፣ ወጎቻቸውን፣ ቋንቋዎቻቸውን እና ተቋሞቻቸውን ያስከብራል" በማለት ያትታል።

ከስዊዝም ሆነ ከስፔን ሕገመንግሥቶቹ መግቢያ የምንረዳው እነዚህ አገራት ለብዝኃነት ወይንም ለማንነት መገለጫዎች ዕውቅና እንደሰጡ ከመግለጻቸውም በላይ አገራቱ የተመሠረቱት በእነዚህ የማንነት መገለጫ ምሰሶዎች ላይ እና እነዚህን ምሰሶዎች መጠበቅ እንዳለባቸው ያስገነዝበናል።

ከብዝሃነት ቁልፍ መገለጫዎች ውስጥ አንደኛው ቋንቋ ሲሆን፣ ኅብረብሔራዊ የፌዴራል ሥርዐት የሚከተሉ አገራት የቋንቋን ብዝኃነት ያከብራሉ። ለምሳሌ ስፔን እ.አ.አ እስከ 1978 ድረስ ካስቲላን ቋንቋ የአገሪቱ ትልቅ ቋንቋ ነበር። ይሁንና ከ 1978 በኋላ ሌሎች ቋንቋዎች በስፔን ነጻ ማኅበረሰቦች (*autonomus communities*) ተጨማሪ ቋንቋዎች ዕውቅና እንዲያገኙ ተደርጓል።

በተጨማሪ ካናዳን ያየን እንደሆነ በተለይም የክዩቤኮችን የዘመናት የቋንቋ ጥያቄን ለመመለስ በማሰብ ካናዳ ውስጥ ፈረንሣይኛ የአገሪቱ ኦፊሰላዊ ቋንቋ እንዲሆን ከመደረጉም በላይ፣ ትምህርት ቤቶች እንግሊዝኛንና ፈረንሳይኛን እንዲያስተምሩ ተደርጓል። በመሆኑም ማንኛውም ሰው በፌዴራል መንግሥታቱ ተቋማት ውስጥ ለመቀጠር ግድ እንግሊዝኛንና ፈረንሳይኛን ማወቅ ይጠበቅበታል። በተመሳሳይ መልኩ ደቡብ አፍሪካም እንግሊዝኛን ጨምሮ ለአሥራ አንድ ቋንቋዎች በሕገመንግሥቷ ዕውቅና ሰጥታለች።

እነዚህ የብዝኀነት መገለጫዎች ብዝኀነትን ዕውቅና ከመስጠት ጋር ተያይዞ የሚታዩ ሲሆን በአገራችንም በኢፌዴሪ ሕገመንግሥት አብዛኞቹ መገለጫዎች የተካተቱ ቢሆንም በአገሪቱ ሊህቃን መካከል በነዚህ የብዝኀነት መገለጫዎች አስፈላጊነት እና ሕገመንግሥታዊ የመሆን ጉዳይ ላይ ደረጃውን የጠበቀ መግባባት ተፍጥሯል ማለት አይቻልም ነበር አሁን ከሃገራዊ ምክክሩ ማግስት በነዚህ ጉዳዮች ላይ መግባባት ይፈጠራል ተብሎ ይጠበቃል። ብዝኀነት በሃገር ደረጃ ብቻ የሚኖር ሳይሆን ብዝሃነት ሰፋቱና መጠኑ ይለያይ እንጂ እንደ ማህበረሰብ በሁሉም ደረጃ የሚታይ ማህበራዊ ነባራዊ ሁኔታ ነዉ ከዚህ አኳያ የፌደራል ስርዓት መልካምድርን መሰረት ያደረገ አደረጃጀት በመሆኑ እና በአንድ ተያያዥ በሆነ መልካምድር ለሚኖሩ ማህበረሰቦች በቋንቋቸዉ እንዲተዳደሩ፤በህላቸዉን እንዲገልጽ የራስ አስተረዳደርን የመፈቅድ በመሆኑ በዚያ መልክዓንድር ዉሥጥ ተሰባጥረዉ የሚኖሩ ሌሎች ማህበረሰቦች ቋንቋና ባህል ለማስተናገድ ማለትም ብዝሃነትን ለማስተናገድ የሚስችል ተጨማሪ የአስተዳዳር ስርዓት ማየት የግድ እንደሚል በብዙ አጥኝዎች ሃሳብ የቀረበበት እና በአንዳንድ ፌደሬሽኖችም ተግበራዊ የሆኑ ተሞክሮዎች ያሉበት ጉዳይ ነዉ። እነዚህ ጉዳዮች እንደ ተጨማሪ የአስተዳደር ስርኣቶች ከዚህ በሚቀጥለዉ ክፍል በዝርዝር ቀርበዋል።

1.2.2. የተግባቦት ዴሞክራሲ እንደ ብዘሃነት ማስተዳደሪያ ስርዓት

አጠቃላይ ዴሞክራሲ የሕዝብ ሉዓላዊነትን ለማስፈን የሚጥር የፖለቲካ ሥርዓት ነው። በተግባር ሲገለጥ፣ የሕዝቡ ሉዓላዊነት የሚረጋገጥበት መንገድ በዋነኛነት ሕዝብ በመረጠው ፓርቲ መተዳደሩ ሲሆን ከዛም በተጨማሪ ግን የሕዝቡን መሠረታዊ መብቶች በቋሚነት የሚያከብርና የሚያስከብር ሥርዓትን መፍጠር ያስገድዳል። ከዛም ከፍ ሲል--በይዘታዊ ትርጓሜው--የሀብት ፍትሐዊ ክፍፍል መኖር ዜጎች መብቶቻቸውን በሚገባ ለማስጠበቅና ለማጣጣም ስለሚያስችላቸው አስፈልጊ መስፈርት ሆኖ ሊታይም ይችላል።

ምሁራን ዴሞክራሲ የሕዝብ ሉዓላዊነት የሚያስጠብቅ ሥርዓት መሆኑን ቢቀበሉም «የሕዝብ ሉዓላዊነት» የሚለው ፅንሰ ሐሳብ በፖለቲካ አና ሕግ ሊቃውንት ዘንድ በርካታ ክርክሮችን አስነሥቷል። «ሕዝብ» እንዴት ይተረጎማል፣ እነማንንስ ያካትታል፣ በአንድ ሀገር ውስጥ አንድ ሕዝብ አለ ብሎ መበየን ይቻላል ወይ፣ ሉዓላዊነቱስ በምን ዓይነት ሕዝባዊ ተሳትፎ (ለምሳሌ ምን ዓይነት ምርጫ በማድረግ?) ይገለጻል ወዘተ የሚሉ ጥያቄዎች ሲያወዛግቡ ሰነባብተዋል።

ይህ ውዝግብ በተለይ የማንነት ጥያቄ በሚነሣባቸው ሀገሮች ውስጥ በከፍተኛ የጡዘት ደረጃ ላይ ቆይቷል። አንደአብነት ብንወስድ፣ የአብላጫ ድምፅ ዴሞክራሲን (majoritarian democracy) እና የተግባቦት ዴሞክራሲን consociational democracy) በሚደግፉ ኃይሎች መካከል ሰፋፊ ልዩነተቶች ለዘመናት ተስተናግደዋል። የአብላጫ ድምፅ ዴሞክራሲ የሚደግፉ ኃይሎች የአንድን ሀገር ኗሪዎች በአንድ ሕዝብነት በመረዳት የዚያ ሕዝብ ሉዓላዊነት የሚረጋገጠው አብላጫው ቁጥር የሚሻው መንግሥትና ሥርዓት በመመሥረትና የአናሳውን መብት ደግሞ በማክበር እንደሆነ ያትታሉ። በመንግሥት የሚወጡት ሕግጋትና አሠራሮች ቅቡልነታቸው የሚረጋገጠው የአብዛኛውን የማኅበረሰብ ክፍል ፍላጎት በማንፀባረቃቸው እንደሆነ ያስቀምጣሉ።

በሌላ በኩል የተግባቦት ዴሞክራሲ አራማጆች፣ በተለይ ብሔር፣ ሃይማኖትና መደብ ላይ የተመረኮዙ የማንነት ጥያቄዎች ባደገደጉበት የፖለቲካ ዓውድ፣ የአብላጫ ዴሞክራሲ ሥርዓት አነስተኛ ቊጥር ያላቸውን ማንነቶች በመድፈቅ ለዘላቂ የበታችነት ይዳርጋል ብለው ይከሳሉ። ይህ አካሄድ ደግሞ የፍትሕና የዘለቄታዊ መረጋጋት ጥያቄ ስለሚያስነሣ ሁሉን አካታች በሆነ ሥርዓት መቀየር አለበት ብለው ይሞግታሉ።

እነዚህ ክርክሮች አሁንም ድረስ ዓለምአቀፋዊ፣ ምሁራዊና ፖሊሲ-ተኮር ዕልባት ያልተገኘላቸውና እያንዳንዱ ዴሞክራሲያዊ አገር እንደሁኔታቸው እየመረጠ ወይም እያዳቀለ የሚተገብራቸው ሥርዓቶች ናቸው።

የተግባቦት ዴሞክራሲ ብዝሃነት ጎልቶ በሚገኝባቸው ሀገራት የዴሞክራሲ ስርዓትን ተግባራዊ ለማድረግ ተጨማሪ ገጽታዎችን የያዘ የዴሞክራሲ አይነት ነው። ሀገራችንም ብዝሃነት ዋነኛው መገለጫ እንደሆነ ይታወቃል። የተግባቦት ዴሞክራሲ በሀገራችን ዴሞክራሲያዊ የህብረ-ብሄራዊ ፌደራላዊ ስርዓት ግንባታን ለማጠናከር የሚጫወተዉ ሚና በሀገራችን የፖለቲካ ሊህቃን እንዲሁም በዘርፉ ምሁራን በተለያየ አግባብ በስፋት ሲነሳ ይስተዋላል። የተግባቦት ዴሞክራሲ በውስጡ አራት መገለጫ ባህሪያትን ይይዛል። የመጀመሪያውና ዋነኛው መገለጫ ባህሪ ከምርጫ በኋላ በሚደረግ ድርድር እና ምክክር ቡድኖች ወይም የብዝሃ ማህበረሰብ መሪዎች በጋራ የሚመሰረት መንግስት/Grand Coalition/፣ሲሆን ይህንን ባህሪ የሚያጠናክሩ ሌሎች ሶስት ባህሪያት ደግሞ የቡድኖቹ/የአነሳ ቡድን እነሱን በሚመለከቱ ጉዳዩች ድምጽን በድምጽ የመሻር ስልጣን/Mutual Veto or Minority Veto/፣ተመጣጣኝ ውክልና/Proportional Representation/ እና የቡድኖቹ/የማህበረሰብ ቡድኖቹ ነፃነትና የራስ ገዝነት ስልጣን/Segmental Autonomy /ናቸው።

1.2.2.1. በቡድኖች ወይም የብዝሃ ማህበረሰብ መሪዎች በጋራ የሚመሰረት መንግስት አብይ ጥምረት /Grand Coalition/

ዐብይ ጥምረት (grand coalition) በማኅበርሰቡ ውስጥ በሚገኙ ዐበይት ቡድናዊ ክፍሎች የተውጣጡ የፖለቲካ መሪዎች መካከል የሚደረግ መንግሥታዊ ጥምረት ነው። ይህም ጥምረት ሀገር እንዲያስተዳድር ሲሰየም፣ ዓላማው ከሁሉም ቡድኖች (segments) የተውጣጡ ልሂቃንን በሙሉ ወይንም በከፊል በማካተት ቅቡልነቱ የሰፋ መንግሥት መመሥረት ነው። ጥምረቱ ቀድሞ በተወሰኑ ቡድኖች መካከል (corporatist grand coalition) አልያም በየጊዜው ሕብረተሰቡ ቅቡልነትን በሚቸራቸውና በሂደት ሊለዋወጡ በሚችሉ ኀይሎች መካከል (liberal grand coalition) ሊደረግ ይችላል።

ቡድን ወይም የብዝሃ ማህበረሰብ ክፍሎች መሪዎች መንግስትን በጋራ የሚመሰርቱበት ሂደት መኖር የተግባቦት ዴሞክራሲ ዋነኛ መገለጫ ነው። በማህበረሰቡ ወይም በሀገር ደረጃ ጎልተው የሚገኙ የተለያዩ ቡድኖች ወይም ማንነቶች/Major Cleavages/ ከምርጫ በኋላ የአገኙትን መቀመጫ ይዘዉ አንድ ላይ በመምጣት የጋራ መንግስት የሚመሰርቱበት ሂደት ነው። በማህበረሰቡ ዋና ዋና ብዝሃ ማንነቶች ለአብነትም የሀይማኖት መሪዎች/ብዝሃነቱ በሀይማኖት የሚገለፅ ከሆነ/፣የብሄር መሪዎች ወይም የሌላ ማንነት መሪዎች በጋራ መንግስት የሚመሰርቱበት ነው። የጋራ መንግስት በተለያየ መልኩ የሚመሰረት ሲሆን ይህም የቡድን መሪዎችን በጋራ ያካተተ የፖለሜንታዊ የካቢኔ አደረጃጀት ወይም የብዝሃን

ቡድኖች የጋራ ምክር ቤት ወይም ኮሚቴ ወይም የብዝሃ ቡድኖችን በጋራ የሚያካትት ፕሬዝዳንት እና ከፍተኛ የፕሬዝዳንታዊ የስልጣን እርከኖች የጋራ መንግስትን ሊመሰረት ይችላል። የተረጋገና ጠንካራ የብዝሃ ቡድኖች የጋራ መንግስት ለመመስረትም ብዝሃ ማንነቶች ተመጣጣኝ ወይም በእኩል ደረጃ ቢሆኑ ይመረጣል።ብዝሃ ማንነቶቹ መካከል ሰፊ የሆኑ የቁጥር የብዛት ልዩነቶች ካሉ አነስተኛ ቁጥር ባላቸው ቡድኖች ላይ ጫና ሊፈጥር ስለሚችል ወይም አንዱ ከፍ ያለ ስልጣን ሊፈልግ ይችላል። ይህም በመካከላቸው ውጥረትን ሊፈጥር ይችላል። ስለዚህ ሚዛናዊ የስልጣን ክፍፍል ለማድረግ በብዝሃ ቡድኖቹ መካከል የሚኖረው ልዩነቶች የጎሉ መሆን የለባቸውም። የብዝሃ ቡድኖቹ ብዛትም የተረጋገ የጋራ መንግስት ለመመስረት የሚኖረው ሚና ከፍተኛ ነው። ለአብነት ሁለት ቡድኖች ብቻ ቢሆኑ በሁለቱ መካከል የሚኖረው ውድድር የጋራ መንግስቱ እንዳይረጋጋ ሊያደርግ ይችላል። አንዱ ቡድን በሌላው ቡድን ላይ ፉክክርን በመፍጠር እንዲሁም አንዱ በሌላኛው ላይ ጫና የሚፈጥርበትን ሁኔታ ሊፈጥር ይችላል።ስለዚህም የብዝሃ ቡድኖቹ ቁጥር ከሁለት በላይ መሆን ለስልጣን ክፍፍሉ አመቺ ሁኔታን ይፈጥራል። በአብዘኛው የተሻለና የተረጋገ የጋራ መንግስት ለመመስረት የብዝሃ ቡድኖቹ ቁጥር ከ 3-4 ቢሆን ተመራጭ ይሆናል። የብዝሃ ቡድኖች ቁጥር በርካታ ከሆነም ለስልጣን ክፍፍሉ አስቸጋሪ ስለሚሆን የጋራ መንግስትን ለመቋቋም ከባድ ያደርገዋል።

1.2.2.2. ውሳኔን/ድምፅን የመሻር ስልጣን/Mutual Veto or Minority Veto/

ውሳኔን የመሻር ስልጣን ለሁሉም ብዝሃ ቡድኖች የሚሰጥና የጋራ መንግስት አስተዳደሩን የሚያጠናክር ሌላኛው የተግባቦት መንግስት መገለጫ ባህሪ ነው። በጋራ መንግስት በትብብር የሚመረው እያንዳንዱ የቡድኑን መሰረታዊና ዋና ዋና ጉዳዮችን የሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ውሳኔዉን ያለመቀልበስ ስልጣን አላቸው። ይህም ስልጣን ቡድኖቹ ፍላጎቶቻቸውን የሚጎዱ ውሳኔዎች የሚኖሩ ከሆነ ተግባራዊ እንዳይደረግ በማድረግ መብታቸውና ፍላጎቶቻቸው እንዲከበር ጠንካራ ከለላ ይሰጣቸዋል። በተግባቦት ዴሞክራሲ ውሳኔዎች የሚወሰኑት ብዝሃ ቡድኖቹ በጋራ በሚያደርጉት ምክክር ነው።ውሳኔን የመሻር ስልጣን ለሁሉም ቡድኖች የሚሰጥ በመሆኑ በውሳኔ ሂደት ችግር ሊፈጥር ይችላል። ነገር ግን ሁሉም ቡድኖች ይህ ስልጣን ያላቸው በመሆኑ ውሳኔዎችን በትብብር የሚወስኑበትን ሂደት ይፈጥራል። ይህም በውሳኔ አወሳሰን ሂደት መዘገየት ወይም ውሳኔዎችን መወሰን ያለመቻል/Decision making dead-lock/ እንዲፈጠር ሊያደርግ ይችላል። ሆኖም ይህ ጉዳይ እንዳይፈጠር በጋራ በምክክር የሐሉንም ፍላጎት ባማከለ መልኩ መወሰን የግድ የሚል ሲሆን ዉሣኔዉን ለማሳለፍ የሚስችል ስምምነት ላይ ለመድረስ የሚሰራ የጋራ ኮሚቴ በማቋቋም ኮሚቴዉ በጉዳዩ ላይ ተስርቶ አስማሚ ሃሳብ ይዞ እዲመጣ ማድረግም እንደ መፍትሄ ይታያል።

1.2.2.3.ተመጣጣኝ ውክልና/Proportional Representation/

ይህም ማለት ተመጣጣኝ ውክልናን፣ የፖለቲካ ውክልና፣ የሲቪል ሰርቪስ አካታች መሆኑ ፣ በተጨማሪም የመንግሥት በጀት ምደባ ተቀዳሚ መስፈርት/መለኪያ እንዲሆን ማድረግ ነው። ከምርጫ ሥርዓት አንጻር ስናየው ደግሞ ከአብላጫ ድምፅ ስልት ተቃራኒ በሆነ መልኩ የተመጣጣኝ ውክልና ስልትን በመጠቀም ሥርዓቱን ይበልጥ ፍትሐዊ እንዲሆን ማድረግን ያመላክታል።

ተመጣጣኝ ውክልና የጋራ መንግስት ለማጠናከር የሚረዳ ሌላኛው የተግባቦት ዴሞክራሲ ባህሪ ነው። ተመጣጣኝ ውክልና ሁለት መሰረታዊ ጥቅሞችን ይሰጣል። የመጀመሪያዉ ቡድኖቹ ወይም የተለያዩ ማህበረሰብ ክፍሎች ካጋገኙት የምርጫ ድምጽ አኳያ ተመጣጣኝ የፓርላማ ወንበር እንዲያገኙ እና ብዝሃ ሃሳቦች እና ፍላጎቶች የፓርላማ ዉክልና በማግኘት በማህበረሰቡ ዉሥጥ ያሉ ጥያቄዎች እና ሃሳቦች ወደ ፓርላማዉ እንዲቀርቡ እና የዉይይት አጀንዳ እንዲሆኑ በማድረግ ከፓርላማ ዉጭ በሌላ ህገወጥ በሆነ አግባብ መራመድ የሚችሉበትን ነባራዊ ሁኔታ ይቀንሳል፣፤ በዋናነት ደግሞ በማህበረሰቡ ዉሥጥ ያለዉ ብዝሃነት አንጻራዊ በሆነ መልኩ በፓርላማ መቀመጫ እንድገለጽ በማድረግ የሚባክን የሕዝብ ድምጽን በመቀነስ ብዘሃነትንማ ማሰተናገድ ያስችላል።

1.2.2.4 የማህበረሰባዊ ቡድኖቹ ነፃነትና የራስ ገዝነት ስልጣን/Segmental Autonomy

የማህበረሰብ ቡድኖቹ ነፃነትና የራስ ገዝነት ስልጣን ማህበረሰቡን የሚመለከቱ ጉዳዮች በራሳቸው እንዲወስኑ ያስችላቸዋል። የጋራ ጉዳዮች ሚዛናዊ ውክልና ባለው መንገድ በጋራ የሚወሰን ሲሆን የግል ጉዳዮች ደግሞ ብዝሃ ቡድኖቹ በራሳቸው የሚወስኑበትን ነፃነት ይሰጣቸዋል። ለብዝሃ ቡድኖችን የራሳቸውን ጉዳይ በራሳቸው የመወሰን ባህሪይ ከፌዴራሊዝም የራስ አስተዳደር መርሆ ጋር የሚመሳሰል ሲሆን በተግባቦት ዴሞክራሲ ራስን በራስ የማስተዳደር ነፃነት ብዝሃ ቡድኑ በአንድ አከባቢ መኖርን/territorial priniciple/ መነሻ ሳያደርግ ብዝሃ ቡድኑ በማህበረሰቡ ውስጥ በማነኛውም ሁኔታ ተበታትኖ የሚገኝም ቢሆን ስልጣኑን እንዲጠቀም ያስችላል።

የተግባቦት ዴሞክራሲን በአግባቡ ለመገንዘብ እነዚህን አራት መሰረታዊ መገለጫ ባህሪያትን መገንዘብ ያስፈልጋል። ባህሪያቱ እርስ በርስ የሚቀራረቡና አንዱ ሌላውን ሚያጠናክሩ ናቸው። እነዚህ መሰረታዊ ባህሪያት ብዝሃነት ወይም የተለያዩ ብዝሃ ፍላጎቶች ባሉባቸው ህገራት የዴሞክራሲ ስርዓትን ተግባራዊ ለማድረግ ያስችላሉ።

1.2.3. ተግባርን መሰረት ያደረገ መልካምድራዊ ወሰን የሌለዉ የራስ አስተደዳደር (functional non-territorial authonomy)

ይህ የራስ አስተዳደር አይነት ከአዲስ የአስተዳዳር እሳቤ ጋር የተያያዘ ሲሆን ይህም አስተዳደርን ለመንግስታዊ ተቋማት ብቻ የተሰጠ አድረጎ ከሚወስድ እሳቤ አስተዳደርን ከመንግስት ተቋማት ጎን ለጎን ማህበረሰቡ በተለያየ መልኩ የሚሳተፍበት ተግባር አድርጎ የሚወስድ እሳቤ እያደገ መምጣት ጋር የሚያያዝ ነዉ። በመልካምድር ያልተገደበ የራስ አስተዳዳር ብዝሃነት ባላቸዉ ሃገራት የቡድን መብቶችን በማክበር የብዝሃነትን አስተዳደር ተግባራዊ ለማድረግ የተነደፈ ንድፈ ሃሳብ እና በተግባር የተሞከረ የአስተዳደር ዘይቤ ነዉ።

ከመጀመሪያው የዓለም ጦርነት በኋላ በቁጥር አናሳ የሆኑ ማህበረሰቦች ጥበቃ ለማደረግ ከነበሩ እንቅሰቃሴዎች ጋር ተያይዞ በ 1920 አና 30 ዎች የባልቲክ መንግስታት በሚባሉት ኢስቶኒያ፤ ላትቪያ እና ሊቶኒያ መልካራምድራዊ ወሰን የሌለዉ ወይም ባህልን በራስ ማስተዳደር የአዉስትሮ ማርክሰስቶች ሬነን እና ባወርን ንድፈ ሃሳብ መሰረት አድርጎ ማቋቋም የስርዓቱ መጀመሪያ ተደርጎ ይወሰዳል።

ባህልን በራስ ማስተዳደር ዋና መገለጫ ግለሰቦችን መሰረት ባደረገ መልኩ በመልካምድር ያልተወሰኑ አናሳ ቁጥር ያላቸዉ ማህበረሰቦችን የሚወክሉ ህዝባዊ ተቋማትን ማቋቋም ሲሆን ተቋማቱም አናሳ ቁጥር ያላቸዉን ማህበረሰቦች (ቡድኖች) የባህል እና ትምህርት ጉዳዩች እንዲስተዳደሩ ስልጣን ይሠጣቸዎል። ይህ ሞዴል በተለያዩ መንግስታዊ አስተዳደሮች ዉስጥ ተበታትነዉ የሚኖሩ አናሳ ቁጥር ያላቸዉ ማሕበረሰቦች (ቡድኖች) ተጨባጭ የሆነ የራስ አስተዳዳር ከመልካምድራዊ የራስ አስተዳዳር አነስተኛ የሆነ ጫና በሚፈጥር መልኩ ለመተግበር አስችሏቸዎል።

ይህ ምድር አልባ ራስ አስተዳደር ከፌደራል ስርዓት ጋር ጎን ለጎን ማካሄድ ፌደረል ስርዓት መልካምድራዊ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ብዝሃነትን በየደረጃዉ ለማስተናገድ የሚገጥሙትን ተግዳሮቶች ለመፍታት የሚስችል ቁልፍ ተጨማሪ አስስተዳደር ስርዓት ተደርጎ ይወሰዳል። ሐኖም ስርዓቱን ለመተግበር በህላቸዉ፤ቋንቀዋቸዉ፤ የአኗኗር ዘይቤአቸዉ ወዘተ.. በጋራ መጠቀም የሚፈልጉ ግለሰቦችን ስምምነት እና የአስተዳደር ወሰን ሳይገድባቸው በጋራ መሰባሰብን እና የጋራ ተቋማት መመስረትን የሚጠይቅ ሲሆን ይህን የሚደግፍ የህግ ማእቀፍ መኖር ያስፈልጋቸዎል። ይህ አደረጃጀት በቤልጀም የፌደረል ስርዓቱ ከተዎቀረባቸዉ ፕሮቪንሶች በተጨማሪ መልካምድር አልባ በሆኑ የጀርመን ፤ የፍላሚሽ እና ዋሎን የባህል ኮሚኒቴዎች በሚል የተደራጀ እና ለኮሚኒቲዎቻቸዉ በትምህርት ፡በባህል፤ ቅርስ ጥበቃ ወዘተ፤... በመሳሰሉ ማህበራዊ ጉዳዩች አገልግሎት የሚቀርቡ እና ባህል ብዝሃነትን የሚስቀጥሉ ማህበራት እንዳሉ ይታወቃል። በሃገራችንም የፌደራል ስርዓቱ እያጋጠሙት ያሉ ተግዳሮቶች አኳያ በተለያዩ ክልሎች ተበታትነዉ የሚገኙ ማህበረሰቦችን ጥያቄዎች ለመፍታት እንደ አንድ አማራጭ መንገድ እነደ አካባቢዉ ተጨባች ሁኔታ እየተጠና መተግበር እንደ አንድ የመፍትሄ አቅጣጫ ሊታይ ይችላል። ዙሮ ዙሮ አንድ ጠንካራ ፌደራል ስርዓት ለመገንባት ብዝሃነትን በተለያዩ አግባቦች በማስተናገድ አብሮነትን እና መተማመንን ይበልጥ እያሳደጉ መሄድ የግድ የሚል ነዉ።

1.2.4. ሌጋል ፕሩላሪዝም (legal pluralism)

የፌዴራል ስርአት በባህሪዉበፌደራል መንግስት እና በአባል መስተዳድሮች መካከል በህገ መንግስት በሚደረግ የስልጣን ክፍፍል ላይ የተመሰረተ በመሆኑ ሁሉም እርከኖች በተሰጣቸዉ የስልጣን ገደብ ዉስጥ ሆነዉ የየራሳቸዉ ህግ የማዉጣት ስልጣን ያላቸዉ በመሆኑ ስርአቱ በባህሪዉ ሌጋል ፕሉራሪዝም ወይም የህግ ብዘሀነት የሚፈጠርበት ነዉ።

ብዝሃ የሆኑ የህግ መሰረቶች በአንድ መንግስታዊ አስተዳደር ዉሥጥ ተግባራዊ ማድረግ ብዘሃነትን ለማስተናገድ እንደ አንድ መሳሪያ ተደርጎ ይወሰዳል። ከዘህ አኳያ ሃገሮች በፐርላማ የሚደነገጉ ዘመናዊ ህጎችን ከመጠቀም ጎን ለጎን ነባር የሆኑ ሃገር በቀል ባህላዊ ህጎችን ስራ ላይ ቸእንዲዉሉ መፍቀድ እና ስራ ላይ ማዎል በማህበረሰቡ በባህሉ ተግባራዊ በመሆን ላይ ያሉ ብዝሃ ህጎችን ማካተት ስለሚያስችል ማህበረሰቡ አሴቱ አድርጎ በወሰዳቸዉ እና አለመግባባቶችንም የማህበረሰቡን አስቴ መሰረት አድርገዉ ዝርላቂ የሆነ እና አብሮነትን የሚያጠናክር መፍተሄ የሚሰጡ ሰርዓቶችን እንዲከተል በማስቻል ብዘሃነትን ለማስተናገድ የሚስችል ሁኔታን መፍጠር ያስችላል። ይህ ለማድረግ ሃገራት ከባህላዊ የእርቅ፤ የሽምግልና፤ የግልግል ሰርዓቶች አዉቅና መስጠት እና ከዘመናዊ የህግ ስርዓት ጋር ተናበዉ እና ተመጋግበዉ የሚሄደበትን ስርዓት መወሰን ይጠይቃል ። ይህም ሀገራቱ ብዝሃ የሕግ ስርዓት እንደሚከተሉ አመላካች ከመሆኑም በላይ የትኛዉ ስርዓት አስከምን ድረስ መወሰን

ስልጣን እንዳለዉ በግልጽ በማመላከት በሁለቱ ስርዐሳቶች መካከል በማህላቸዉ ሊኖር የሚችል ግጭትን መከላከል የጠቀናጀ እና የማህበረሰቡን የሕትህ ጥያቅ የሚመለስ አካሄድን መቀየስ ያስችላል። ብዝሃ ህግ ተግባራዊ ሲደረግ ከአንዳንድ ባህላዊ አሰራሮች እና አካሄዶች ጋር ተያይዞ ከዘመናዊ የሰብአዊ መብት እሳቤዎች እና ከሴቶች መብቶች ጋር የሚጣረሱ አካሄዶች ህጋዊ እዉቅና እንዳይሰጣቸዉ ጥንቃቄ ማድረግ እና ሰፊ ዉይይት በማድረግ መግባባት መፍጠርን ይጠይቃል። ብዘሃ ህግን መጠቀም የብዝሃ ማህበረሰብ ባህሎች እና እሴቶችን በስራ ላይ በማዎል በአምድ በኩል የተለያየ ማህበረሰቦች እንደ ሃገር ያላቸዉን አስተዎጽኦ በመጠቀም መህበረሰቡን የሚመለከቱ ጉዳዩችን በራሱ በማህበረሰቡ እንዲፈቱ በማድረግ ብዝሃነትን ማስተናገድ ሲሆን እነንደሃገርም ከባቢዊ ችግሮች በራሱ በከባቢዉ ማህበረሰብ በህላዊ ስርዐቶች የሚፈቱ ከሆነ እንደ ሃገርም አለመግባባቶች እና ግጭቶች ከስር ከመሰረቱ እየተፈቱ ስለሚሄዱ ሀገራዊ ሰላመን ለማረጋገጥ የሚስችል ሲሆን ይህም ብዘሃነትን ያቀፈ ጠንካራ ፌደራላዊ ስርዓት ለመገንባት ያስችላል።

1.2.5. አሳታፊ የሆነ ዴሞክራሲ (participatory democracy)

አሳታፊ የሆነ ዴሞክራሲ በሂደቱ ብዝሃ የሆኑ ፍላጎቶች እና እሳቤዎችን ማስተናገድ የሚችል በመሆኑ ብዝሃነትን ለማስተዳደር እንደ አንድ መሳሪያ ተደርጎ ይወሰዳል። አሳታፊ የሆነ ዴሞክራሲ ማህበረሰቡ አርሱን የሚመለከቱ ገጉዳዩች በእራሱ ተሳትፎ እንዲወሰኑ ስለሚፈቅድ ብዝሃነት ባለበት

ማህበረሰብ ዉሥጥ የብዝሃ ማህበረሰቡን ፍላጎትማህበረሰቡን በሚመለከቱ መሰረታዊ ጉዳዩች ላይ በራሱ ተሳትፎ ዉሳኔ ላይ እንዲደረስ በማድረግ ብዝሃነትን በዉሳኔ አሰጣጥ ላይ ማስተናገድ ስለሚያስችል ብዝሃ የሆኑ ማህበረሰቦች ወሳኔዎች ላይ የሚደርጉትን ተሳትፎ አካታች እና የሁሉም ፍላጎት ሚዛን በጠበቀ መልኩ እንዲስተናገድ በማድረግ ብዝሃነት ለማስተዳደር ጠቃሚ መሳሪያ ነዉ።

አሳታፊ የሆነ ዴሞክራሲ በዉክልና ዴሞክራሲ ከሚኖረዉ በተወሰነ ጊዜ ገደብ በምርጫ ድምጽ በመስጠት ተወካይን ከመምረጥ በዘለለ ቤጊዜዉ በሚኖሩ ዉሳኔዎች ላይ በተለያ አግባቦች እና ደረጃዎች መሳተፍን ስለሚፈቅድ በሰጡት ድምዝ እንኳ ይወክለናል ያሉት አሸናፊ ሆኖ ም./ቤት ባይገባም የእነሱ ፍላጎቶች ለማቅረብ እነሱን የሚመለከቱ ዉሳኔዎች በሚሰጡበት ወቅት የመሳተፍ እድል ስለሚፈጥር በዉሳኔዎች የሚገለሉበት ሁኔታ ስለማይኖር ብዝሃ ፍላጎቶችን ለማስተናገድ ዋና ዴሞክራሲዊ ሂደት በመሆን ብዝሃነቴን የማስተናገጃ መሳሪ ሆኖ ያገለግላ። በሀገራችንም ይህ አሳታፊ ዴ፣ክራሲ በቀበሌ ደረጃ ተግበራዊ ማድረግ የሚቻልበት ሁኔታዎች በመፍጠር ብዝሃ ሃሳቦች እና ፍላጎቶችን በማስተናገድ አካታች የሆነ የዉሳኔ አሰጣጥ ስርአትን መገንባታ ለፌደረላዊ ስርዓቱ መጠናከር ወሰኝ ነዉ።

ዴሞክራሲ ዜጋዉ በነቂስ ወጥቶ የሚፈልገዉንና ይጠቅመኛል የሚለዉን ፓርቲ መምረጡ ዋነኛ መገለጫ ቢሆንም የተመረጠዉ ፓርቲ መንግስት ከሆነ በኋላ መንግስት በሚወስናቸዉ ዋና ዋና እና ህዝብን በቀጥታ በሚመለከቱ ጉዳዮች ህዝቡን በሚገባ ማሳተፍ እና እና የቡድን መብቶችና ጥቅሞችን ከግለ መብቶች ጋር በሚገባ አጣጥሞ ማስኬድ ብዘሀነትን የማስተናገድ አንዱ መሳሪያ ነዉ።

1.3.የብዝሃነት አስተዳደር እድሎች እና ፈተናዎች በኢትዩጵያ

1.3.1 እድሎች

ሃገራችን ኢትዩጵያ ብዘሃነት መገለጫዎ የሆነች ሀገር መሆኗ ነባራዊ ሃቅ ነዉ። ማህበረሰባችን ብዝሃነቱን ጠብቆ በአብሮነት ተጋምዶ የኖረ እየኖረ ያለ መሆኑ በሃገራች ብዝሃነትን ለማስተዳደር ማህበረሰባዊ ዉቅራችን መሰረት ያደረገ እና ማህበረሰባዊ እሴቶችን በጠበቀ መልኩ ብዘሃነትን ለማስተዳደር መልካም እድሎችን ያሉን መሆኑን መወሰድ ይቻላል።

መአገራችንትንሃገራች ብዝሃነትን ለማስተዳደር ማህበረሰባዊ ዉቅራችን መሰረት ያናራ ራችንትንሃገራች ብዝሃነትን ለማስተዳደር ማህበረሰባዊ ዉቅራችን መሰረት ያደረገ እና ማህበረሰባዊ እሴቶችን በጠበቀ መልኩ ብዘሃነትን ለማስተዳደእና ተዋልደዉ በሰላም ለዘመናት የኖሩ መሆናቸዉ የኢትዮጲያ ህዝብ በባህሪዉ ፌዴራትድ ማህበረሰብ መሆኑን መረዳት ይቻላል። ከዚህም በላይ ብዘህ ማንነቱ የተለያዩና እጅግ አስደናቂ የሆኑ ሀገር

በቀል የግጭት አፈታት እና የሙገት መፍቻ፣ የጋብቻ፣ የህይማኖት፣ወዘተ ትስስሮች እና ስርአቶች ያሏቸዉ መሆኑ ብዘሀነትን በአግባቡ ለማስተዳደር ምቹ ሁኔታ የፈጠረ በመሆኑ በአግባቡ ልንሰራበት እና ልንጠቀምበት ይገባል።

መሰረታዊ ከሆነዉ መህበረሰባዊ መነሻዎች በተጨማሪ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገመንግሰት ከመግቢዉ ጀምሮ ለዝሃነት አዉቅና የሠጠ እና በአንቀጽ 5 እና በአንቀጽ 39 (1-4) ሥር ለኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች የቋንቋ፣ የባህል እና የራስን እድል በራስ የመወሰን መብቶችን በመስጠት ብዝሃነትን በግልጽ የተቀበለ የህግ ማዕቀፍ መሆኑ ብዝሃነትን ለማስተዳደር ቀደም ባሉ ጊዚያት ያልነበሩ ህጋዊ እድሎችን ፈጥሯል ። በፌዴራል ደረጃ ከማንነት ጋር የተያዘ ብሃት ዉክልናን እና ተሳትፎን ለማረጋገጥ ሕገ-መንግሥቱ የፌዴሬሽን ምክር ቤትን ያቋቁማል (አንቀጽ 61/2) እንዲሁም በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ውስጥ ለአነስተኛ ቁጥር ላላቸዉ ብሔረሰቦች ቢያንስ 20 ወንበሮችን ይመድባል (አንቀጽ 54/3)። ብዘሃ የፖለቲካ ተሳትፎን ለማረጋገጥ እንዲቻል በአንቀጽ 38/1 ማንኛዉም ኢትዮጵዊ ዜጋ በቀለም፤ በዘር፤በብሄር፤በብሄረሰብ ፤ በጾታ፤ በቋንቋ፤በሃይማኖት፤ በፖለቲካ አቋም ፤በልላ አመለካከት፤ በሌላ አቋም ላይ ተመሰረተ ልየዩነት ሳይደረግበት የመምረጥ እና የመመረጥ መብትን የደነገገ ብዝሃነትን መሰረት ያደረገ የጾለቲካ ተሳትፎን የደነገገ ብዝሃነትን ለማስተናገድ የሚችል ማዕቸፍ መኖሩ እንደ አንድ እድል ይታያል። በአንቀጽ 88 በህገመንግስቱ በተደነገገዉ የፖለቲካ ዓላማዎች መንግስት በዴሞክራሲያዊ መርሆዎች ላይ በመመስረት ህዝቡ በሁሉም ደረጃዎች ራሱን በራሱ የሚያስተዳድርበትን ሁኔታ ማመቻቻል

ያለበት መሆኑን እና የብሄሮችን፤በሄረሰቦችንና የህዝቦች ማንነት የማክበር በዘሁ ላይ በመመርኮዝ በመካከላቸዉ እኩልነትን፤ አንደነትና እና ወንድማማችነትን ማተናከር ግዲታ አለበት። እነዚህ ድንጋጌዎች ብዝሃነትን በመቀበል እና በማስተዳደር ህገራዊ አንድነትን ለማጠናከር የሚደስቸሉ ህገመንግስታዊ ድንጋጌዎች መሆናቸዉ ብዝሃነትን ለማስተዳደር መልከም መነሻዎች ናቸዉ።

በህገራን ብዝሃነትን ከማስተዳደር ጋር ያዞ በተግባር ያሉ መልካም ቸድሎችን ስንመለከት ባለፉት የደራል ስርዓቱ ከተዘረጋበት ጊዚ ጀምሮ ብዝሃትን ለመቀበል እና ብዘሃትን ለማደስተዳደር ከብዝሃ ቋንቀዋች በትምህርት በአስተዳደር እና በመህበረሰቡ እለት ተእለት ተግባራት ስራ ላይ ለማዋል የጠሄደበት ርቀት፤ ከብዝሃ በህልን (ከአለባባስ፤ ሙዚቃ፤ አመጋገን) ጋር ዒዘፕ ለማስተዎወቅ እና ለማሳደግ እየጠሰሩ ያሉ ተግባሮች፤ ብዝሃነት በራስ አስተዳደር እና በገራ አስተዳደር ለመተግበር እየጠደረጉ ያሉ ጥረቶች ለቀጣይ ብዝሃነትን ለማስተረናገድ እንደ መልካም እድሎች ይወሰዳሉ።

1.3.2 ፈተናዎች

ብዝሃነትን መአግባቡ ማስተናገድ ሰፊ የአመለካከት ለዉጥን የሚጠይቅ ዉስብስብ የሆነ ጉዳይ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ምንም እንኳ ብዝሃነት መገለጫችን ቢሆንም ይህን ከማስተናገድ አኳያ ከቀጠለዉ የፖለቲካ ባህላችን ጋር ተያይዞ ፈተናዎች ገጥመዋል።

1.3.2.1. የሃገሪቱ መገለጫ የሆነዉን ብዝሃነትን ተቀብሎ ብዝሃነትን ያቀፈ አንድነትን በመገንባት ዙሪያ ያሉ ዉስንነቶች

በየትኛውም ሀገር ውስጥ በተለያየ እይታ የሚገለጹ የብዝኃነት መገለጫዎች እንዳሉ ብዙዎች ይስማማሉ። ስለዚህ የትኛውም ሀገር በውስጡ የሚታዩ የብዝኃነት መገለጫዎች በተለይም ወሳኝ የሆኑ የማንነት መገለጫዎች ተብለው የሚገለጹ የቋንቋ፣ የህይማኖት፣ የባህል፣ የታሪክና የመሳሰሉ የማንነት መገለጫዎች ይኖሩታል። ሀገራት ለእነዚህ የማንነት መገለጫዎች እዉቅና ይሠጣሉ እዉቅናዉም በፌዴረሽኖች ከሕገመንግሥት መግቢያ ጀምሮ የቃላት አጠቃቀምን ባካተተ መልኩ የተለያዩ እርምጃዎችን በመውሰድ ብዝኃነትን ያንጸባርቃሉ።ብዝሃነትን የማስተናገድ ጉዳይ ዴሞክራሲያዊ ፌደራላዊ ስርዓት የሚከተሉ ሃገራት ቁልፍ አጀንዳ ነው። ይህም ብዝሃነትን በብቃት ለማስተናገድ የሚችል ፌደራላዊ ዴሞክራሲን የመገንባት ጉዳይ ነዉ። አንዳንድ ሃገራት ይህንን ብቃት አስጠብቆ ለማስቀጠል በብዝሃነት አያያዝ ዙሪያ የሚታዩ ችግሮችን በተከታታይነት በጥናት በመለየት መፍትሄዎችን ያቀርባሉ፣ የፖለቲካ ሊህቁም በዚህ ጉዳይ በጥልቀት በመወያየት ብቃቱን እያሻሻለ እንዲሄድና ለአዳጊና ተለዋዋጭ ሁኔታዎች የሚመጥን ዕይታ እያጎለበተ እንዲሄድ ይደረጋል።

ሕብረብሔራዊ የፌዴራል ሥርዓት የሚከተሉ ሀገራት በሕገመንግሥቶቻቸው መግቢያ ጀምሮ ሕብረብሔራዊነትን ያንጸባርቃሉ። ለምሳሌ የስዊዝን ሕገመንግሥት ያየን እንደሆነ በሕገመንግሥቱ መግቢያ ካንቶኖች ለሕብረብሔራዊ የፌዴራል ሥርዓት በተለይም ብዝኃነትን ከመቀበልና ከማቀፍ አንጻር ቁርጠኝነታቸውን ያሳዩ ሲሆን፣ በዚሁ መሠረት ብዝኃነታቸውን በማክበርና በጋራ ለመኖር ከመወሰናቸውም አልፈው አንዱ ሌለኛውን በማክበርና በእኩልነት ለመኖር ቃልኪዳን መግባታቸውን ገልጸዋል። ይህም በስዊዝ ሕገመንግሥት መግቢያ ላይ የተገለጸው ለሕብረብሔራዊነት ወይም ለብዝኃነትና ለእኩልነት የተሰጠውን ቦታ ያንጸባርቃል። ለዚህም ነው ፍሊነር የተባሉት ምሁር ልክ እንደ አሜሪካ ሕገመንግሥት "እኛ የአሜሪካ ሕዝብ..." በማለት ካንቶኖች የስዊዝ ፌዴሬሽን የወጡነት መፍትሄን አልተከተሉም ብለው ይገልጻሉ። ይልቁንስ "የካንቶኖች ሕዝቦች" በማለት ይገልጻሉ። በተመሳሳይ መልኩ የስፔን ሕገመንግሥት በመግቢያው ብዝኃነትን በብዙ ቁጥር የተቀበለ ሲሆን፣ በዚሁ መሠረት ሕገመንግሥቱ "ሀገረ-ስፔን ሁሉንም ስፓኒያርዶችንና ሁሉንም የስፔን ሕዝቦች ሰብዓዊ መብቶችን፣ ባህሎቻቸውን፣ ወጎቻቸውን፣ ቋንቋዎቻቸውን እና ተቋሞቻቸውን ያስከብራል" በማለት ያትታል።

ከስዊዝም ሆነ ከስፔን ሕገመንግሥቶቹ መግቢያ የምንረዳው እነዚህ ሀገራት ለብዝኃነትን ወይንም ለማንነት መገለጫዎች ዕውቅና እንደሰጡ ከመግለጻቸውም በላይ ሀገራቱ የተመሠረቱት በእነዚህ የማንነት መገለጫ ምሰሶዎች ላይ እና እነዚህን ምሰሶዎች መጠበቅ እንዳለባቸው ያስገነዝበናል።

ሌላኛው ሕብረብሔራዊ የፌዴራል ሥርዓት ለብዝኃነቶች ዕውቅናን የሚሰጡት የተለያዩ ምልክቶችን በመጠቀም ሲሆን፣ ፌዴሬሽኖቹ የሚጠቀሟቸው እነዚህ ምልክቶች ደግሞ የሀገሪቱን መጠሪያ ጨምሮ፣ ሀገሪቱ የምታከብራቸውን ሕዝባዊ በዓላት፣ በሀንግዎቻቸው ላይ የሚሰቅሉዋቸው ሰንደቅዓላማዎች፣ ኦፊሰላዊ ዓርማዎች እና የመሳሰሉትን የሚጨምር ነው። ይህ ማለት ደግሞ ሕብረብሔራዊ የፌዴራል ሥርዓትን የሚከተሉ ሀገራት ሕብረብሔራዊነትን የሚገለጹ ባህሪያትን ያንጸባርቃሉ ማለት ነው። ሰንደቅ ዓላማ የአንድ ሀገር መገለጫ ሆኖ፣ በተለይም

ሕብረብሔራዊ የፌዴራል ሥርዓት በሚከተሉ ሀገራት ሰንደቅ ዓላማ ሕብረብሔራዊነትን ከማንጸባረቅ አንጻር ከፍተኛውን ሚና ይጫወታል። ለምሳሌ የስፔንን ሕገመንግሥት ካየን ሕገመንግሥቱ የስፔንን ሰንደቅ ዓላማ ከመግለጽ አልፎ ለክልሎች ሰንደቅ ዓላማዎች ሕገመንግሥታዊ ዕውቅና ሰጥቷል። እነዚህም ሰንደቅ ዓላማዎች ከፌዴራሉ ሰንደቅ ዓላማ ጋር በክልሎቹ በዓላት ቀን ጨምሮ በህንጻዎች ላይ መሰቀል እንዳለባቸውም ጭምር ደንግጓል። ስለሆነም ለክልሎቹ ሰንደቅ ዓላማዎች የተሰጠው ዕውቅና ሀገሪቱ ሕብረብሔራዊነትን ከመቀበልና ከማክበር የመነጨ የፖሊሲ አቅጣጫ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል።ቋንቋ የማንነት ቁልፍ መገለጫዎች ውስጥ አንደኛው ሲሆን፣ ሕብረብሔራዊ የፌዴራል ሥርዓት የሚከተሉ ሀገራት የቋንቋን ብዝኃነት ያከብራሉ። ለምሳሌ ስፔን እ.አ.አ እስከ 1978 ድረስ ካስቲላን ቋንቋ የሀገሪቱ ትልቅ ቋንቋ ነበር። ይሁንና ከ 1978 በኋላ ሌሎች ቋንቋዎች በስፔን ነጻ ማኅበረሰቦች (*autonomus communities*) ተጨማሪ ቋንቋዎች ዕውቅና እንዲያገኙ ተደርጓል። በተጨማሪ ካናዳን ያየን እንደሆነ በተለይም የክዩቤኮችን የዘመናት የቋንቋ ጥያቄን ለመመለስ በማሰብ ካናዳ ውስጥ ፈረንሣይኛ የሀገሩቱ ኦፊሰላዊ ቋንቋ እንዲሆን ከመደረጉም በላይ፣ ትምህርት ቤቶች እንግሊዝኛንና ፈረንሳይኛን እንዲያስተምሩ ተደርጓል። በመሆኑም ማንኛውም ሰው በፌዴራል መንግሥታቱ ተቋማት ውስጥ ለመቀጠር ግድ እንግሊዝኛንና ፈረንሳይኛን ማወቅ ይጠበቅበታል። በተመሳሳይ መልኩ ደቡብ አፍሪካም እንግሊዝኛን ጨምሮ ለአሥራ አንድ ቋንቋዎች በሕገመንግሥቷ ዕውቅና ሰጥታለች።

እነዚህ የብዝሃነት መገለጫዎች ብዝሃነትን እዉቅና ከመስጠት ጋር ተያይዞ የሚታዩ ሲሆን በሃገራችንም በኢ.ፊ.ዴ.ሪ ህገመንግስት አብዛኞቹ መገለጫዎች የተካተቱ ቢሆንም በአገሪቱ ሊህቃንመካከል በነዚህ የብዝሃት መገለጫዎች አስፈላጊነት እና ህገመንግስታዊ የመሆን ጉዳይ ላይ ደረጃዉን የጠበቀ መግባባት ተፍጥሯል ማለት አይቻልም ። ከዚህ በጠጨማሪ ብዝሃነትን ከማስተናገድ አኳያ በክልልሎች፤ በዞኖች፤ወረዳዎእ እና ቀበሌዎች አካባቢ ያለበትን ሁኔታ እና የተሰጠዉ እዉቅና ላይ መነጋጋር ወቅታዊ እና ወሳኝ ጉዳይ ይመስላል። ሰዉ የሚኖዉ በዋናነት የመኖሪያ ከባቢዉ በቀበሌዉ በመሆኑ ቀበሌዉ ላይ ብዝሃነትን መቀበል እና እንደ አንድ መሬት ላይ ያለ አዉነታ በመወሰድን የብዝሃነት አስተዳደርን በደረጃዉ የበለጠ ማተናከር እና የሚታዩ ተግዳሮቶች ካሉ በዉይይት እና በአብሮነትቨ እሳቤ መሻገር ይገባል። ዴሞክራሲዊ ፌደራል ስርዓር ግንባታ በአገራችን ተጨባች ሁኔታ ህብረ-በሄራዊነትን በተቀበለ ብዝሃንትን በሚያስተናግድ አግባብ መሄድ ካልቻለ ዉጤታማነቱ አጠያያቂ ከመሆኑም በላይ አገራችን ከቆየችበት የግጭት አዙሪት ዉስጥ ወጥተን ዴሞክራሲያዎ ፌደራላዎ ስርዓታችን ለመገንባት የሚያስችሉ መደላድሎችን መጣል የማንችል መሆኑን የጋራ ግንዛቤ መያዝ ይገባል።

ብዝሃነትን ከማስተናገድ ጋር ተያይዞ ያሉ ጅምሮችን በማጠናከር እና ተግዳሮቶቹን ለመሻገር የሚስችሉ ዉይቶችን በማድረግ በየደረጃዉ ፌደራል ዴሞክረሳሚ ግንባታ ሂደት ማጠናከር ይጠይቃል።

1.3.2.2. የዳበረ እና ተቋማዊነትን የተላበሰ የመንግስታት ግንኙነት በተገቢዉ አለመገንባት

መንግስታት ነጻነታቸዉን ጠብቀዉ አይቀሬ የሆነዉን ትስስራቸዉን በሚታወቅ፤ ሊተነበይ በሚችል እና የፈደረል ስርዓቱን በካበረ መልኩ ማስቀጠል ከሌሎች ጠቀሜታዎቹ ባሻገር መንግስታት ቀጣይነት ያለዉ ምክክር፤ የተሞክሮ ልዉዉጥ፤ በአዋሳኝ ቦታዎቻቻዉ በሚኖሩ ማህብሰቦች መካከልየህዝብ ለህዝቦች ግንኙነት በማድረግ፤ በጋራ ተጠቃሚ የሚሆኑባቸዉን የጋራ ልማቶችን በመስራት፤ የብዝሃነት አስተዳደር ላይ የሚጠቅሙ ህጎችን ለማዉጣት የሚያስችሉ ዉይይቶችን በማደረግ የመንግስታ ግንኙነትን እንደ አንድ የብዝሃነት አስተዳደር መሳሪ አድርጎ መተቸም ይቻላል፤፤ ዝርዝር የመንግስታት ግንኙነቶችን የሚመለከቱ ጉዳዩዎ በሚቀጥለዉ ክፍል ቀርቧል

ብሃነትን ካማስተዳደር ጋር የገጠመን አንዱ ፈተና አልፎ አልፍ እንደሚታየዉነ በክልሎች የውስጥ ህዳጣን ቡድኖች (internal-minorties) **መብት አለመከበር ነዉ ።። መልክዓምድርና ብሔርን በጥብቅ ማቆራኘት ጋር ተያይዞ የሚታየው ክፍተት ነው። ብሔሮች የሠፈሩበትን መልክዓምድር መሠረት አድረጎ ራስ ገዝ አስተዳደር መሰጠቱ ተገቢ ቦሆንም ብሔሮች የሚገኙበት መልክዓምድር አንድ ወጥ የሆነ አድርጎ በማየት በተግባር በመሬት ላይ የሚታየውን ብዝኃነት ግንዛቤ ውስጥ አለማስገባት ይታያል።**

ዋናው ነጥብ በይበልጥ የብሔርና መልክዓምድር ትስስር የጠነከረ ከሆነ ብሔሩ የኔ ራስ ገዝ ክልል ነው ብሎ በሚያስተዳድረው ክልል ውስጥ የሚኖሩ የውስጥ ህዳጣን ማኅበረሰቦች የሚያገኙት የሕግ ዕውቅና ሆነ ጥበቃ በተሟላ መልኩ ላይሆን ይችላል። የዚህ አመክንዮ በመልክዓምድሩ የራስ ገዝ ሥልጣን ያለው ብሔር ይህ መልክዓምድር እንደ የራሱ ራስ ገዝ ሥልጣን ተግባራዊ የሚያደርግበት ክልል አድርጎ በመውሰድ ከህዳጣን ማኅበረሰቦች ጋር ለመጋራት ፍላጎት አያሳድርም። ተቃርኖ በሚመስል መልኩ ሕብረብሔራዊ ፌዴራሊዝም በሀገር ደረጃ ለብዝኃነት ዕውቅና ቢሰጥም በክልሎች ደረጃ ለብዝኃነት ዕውቅና በተገቢዉ መንገድ የማሰጥበት ሁኔታ ይታያል።

በአንድ በኩል ጽንሰሃሳቡ አሃዳዊ የሆነውን ብሔረ መንግሥት ለማስወገድ ከፍተኛ ተነሳሽነትን የሚያሳይ ሲሆን በሌላ በኩል ይህንኑ ሞዴል ብሔረ ክልል በሚል ተክቷል። ስለሆነም በህዳጣን እና አብላጫ ባለው ማኅበረሰብ መካከል ያለውን የግንኙነት ችግር ሀገራዊ ከሆነ መልኩ ወደ ክልላዊ ወደ ሆነ መልኩ ቀይሮታል።

ይህ ብሔርና መልክዓምድርን በጥብቅ ያቆራኘ ሕገመንግሥታዊ ሥርዓት ባህሪ የሆነው ችግር ቀደም ብሎ በካርል ሬነር (2005) በሚከተለው መልኩ የተለየ ጉዳይ ነው፣፣ "በኔ መልክዓምድር ውስጥ የምትኖር ከሆነ ለእኔ ውሳኔዎች ተገዢ

መሆን፣ ለኔ ሕግ ተገዢ መሆን፣ የኔን ቋንቋ መናገር፣ ይህ የአገዛዝ መገለጫ እንጂ የእኩልነት መብት አይደለም"፣፣ ሬነር ችግሩን ከላይ በትምህርተ ጥቅስ በተቀመጠው መልኩ ከማብራራቱም በላይ ለዚህ ችግር መፍትሄ ብሎ ያቀረበው ሀሳብ በሌላ ብሔር መልክዓምድር ውስጥ ለሚኖሩ ህዳጣን ማኅበረሰቦች መልክዓምድር አልባ ራስ ገዝነት(non-territorial autonomy) መስጠትን ነው።

መልክዓምድር አልባ ራስ ገዝ አደረጃጀት አሁን ካሉ ተጨባጭ የሆነ መረጃዎች አኳያ ተግባራዊነቱ በጣም ደካማ ሆኖ ታይቷል። ጽንሰ ሃሳቡ ለፖሊሲ አውጪዎች ማራኪ ከመሆንና ለችግሩ መፍትሄ ሰጥተናል ለማለት ጥቅም ላይ ከመዋል የዘለለ ትርጉም ያለው አይደለም። በመሆኑም መልክዓምድር አልባ ራስ ገዝነት ትክክለኛ ራስገዝነት አይደለም (ኮክሌ 2006)። ሆኖም እንደ አንድ አማራጭ መፍትሄ የየክልሉን ነባራዊ ሁኔታና የህዳጣን ማኅበረሰቦችን አሰፋፈር መሠረት አድርጎ መጠቀም ችግሩን ለመፍታት አንድ ተጨማሪ መፍትሄ አድርጎ ማየት ይቻላል።

ከመልክዓምድር አልባ ራስ ገዝነት በዘለለ በብሔረ ክልል ውስጥ የሚኖሩ የውስጥ ህዳጣን ማኅበረሰቦችን ችግር ለመፍታት ሌሎች መፍትሄዎችን ማየት ተገቢ ነው። አንዱ መፍትሄ ሊሆን የሚችለው በብሔረ ክልሉ ላለው አብላጫነት ላይ መሠረት ላደረገ እንቅስቃሴ ውጫዊ የሆነ ተጨባጭ የሆነ ወሰን ማስቀመጥ ይሆናል ይህ ሲባል መሠረታዊ የሆኑ የሰው ልጅ መብቶችና ነጻነቶች /bill of rights/ ሰፋ ባለ መልኩ በፌዴራል /ህገራዊ/ ሕገመንግሥቱ ውስጥ እንዲካተቱ በማድረግ የፌዴራል መንግሥቱ ህዳጣን ማኅበረሰቦችን በተመለከተ ጣልቃ የሚገባበት ሥልጣን መስጠት፣ በሌላ መልኩ ውስጣዊ በሆነ መልኩ አብላጫ ድምጽን መሠረት አድርጎ ውሳኔ የሚሰጥበትን አካሄድ ላይ ገደብ ማስቀመጥና ሥልጣን በክልል ደረጃ ለህዳጣን ቡድኖች በማጋራት በራሱ በብሔረ-ክልሉ ሕገ መንግሥት መፍታት ይቻላል።

በአጠቃላይ ራስገዝነት በህዳጣን ብሔሮች ላይ የሚኖር ማግለልና ጭቆና ምላሽ ቢሆንም ራሱ በቀላሉ ተመልሶ ሌሎችን ህዳጣን ቡድኖች የማግለያና የመጨቆኛ መሣሪያ ስለሚሆን ጉዳዩን በጥንቃቄና የሁሉንም መብት በሚያከብርና ሚዛናዊ በሆነ መልኩ መተግበር ይጠይቃል።

ብዝሃነትን ከማስተዳደር አኳያ ተጨማሪ ፈተናዎች ከሆኑት ዉስጥ አስፈላጊው የፌዴራላዊ አስተሳሰብ እና መንፈስ አለመዳበር፣ መደበኛ እና ተቋማዊ የሆነ የመንግሥታት ግንኙነት (Intergovernmental relations) ሥርዓት አለመዳበር እና ለፌዴራል ሥርዓቱ በትክክል ስራ ላይ ለማዋል አስፈላጊ የሆኑ ተቋማዊ የጥበቃ ዘዴዎች በሚፈለገዉ ደረጃ

አለመጠናከር ናቸው። ብዝሃትን በፌደራል ስርዓት ከማስተናገድ አኳያ በክልሎች፣ በዞኖች፣ በወረዳዎች እና በቀበሌዎች አካባቢ ያለበትን ሁኔታ እና የተሰጠው ዕውቅና ላይ መነጋጋር ወቅታዊ እና ወሳኝ ጉዳይ ይመስላል። ምክንያቱም ሰው የሚኖረው በዋናነት የመኖሪያ አካባቢው በቀበሌው በመሆኑ ቀበሌው ላይ ብዝኀነትን መቀበል እና እንደ አንድ መሬት ላይ ያለ እውነታ በመወሰድ የብዝኀነት አስተዳደርን በደረጃው የበለጠ ማጠናከር እና የሚታዩ ተግዳሮቶች ካሉ በውይይት እና በአብሮነት እሳቤ መሻገር ይገባል። ዴሞክራሲያዊ ፌዴራል ሥርዐት ግንባታ በአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ኅብረብሔራዊነትን በተቀበለና ብዝኀነትን በሚያስተናግድ አግባብ መሄድ ካልቻለ ውጤታማነቱ አጠያያቂ ከመሆኑም በላይ አገራችን ከቆየችበት የግጭት አዙሪት ውስጥ ወጥተን ዴሞክራሲያዊ ፌዴራላዊ ሥርዐታችን ለመገንባት የሚያስችሉ መደላድሎችን መጣል የማንችል መሆኑን የጋራ ግንዛቤ መያዝ ይገባል። ብዝኀነትን ከማስተናገድ ጋር ተያይዞ ያሉ ጅምሮችን በማጠናከር እና ተግዳሮቶቹን ለመሻገር የሚያስችሉ ውይይቶችን በማድረግ በየደረጃው የፌዴራል ዴሞክራሲ ግንባታ ሂደት ማጠናከር ይጠይቃል። በአሁኑ ወቅት መንግሥት በተለያዩ የሪፎርም እርምጃዎች እና ሀገራዊ ምክክር በማካሄድ እነዚህን ፈተናዎች ለመፍታት እና ብዝሃነትን ቀቀፈ አንድነትን በማጠናከር ሁሉን አቀፍ የገረመንግስት ግንባታን ተግባራትን በማከናወን ላይ ይገኛል።

1.2.3 ሀገራዊ ምክክር እና በዉይይት ችግር የመፍታት ባህል ለዘላቂ ሀገር ግንባታ

የአንድ ሀገረ መንግስት ግንባታ በተሳካ መንገድ እዉን ለማድረግ በሀገሩ ዋና ዋና የሀገር ግንባታ ምሶሶዎች ለአብነት በሀገ መንግስት፣ ስርአተ መንግስቱ ዋና ዋና ምሶሶዎች፣ የፖለቲካ ስርአት፣ በዋና ዋና ሀገራዊ ምልክቶች ወዘተ ላይ መግባባት የግድ ይላል። ከላይ በተጠቀሱ የሀገረ መንግስት ግንባታ ዋና ዋና ጉዳዮች ዙሪያ መግባባት ከሌለ እና በእነዚህ ምክኒያት ግጭቶች ካሉ የግድ ሀገራዊ ምክክር እንደሚያስፈልግ የዘርፉ ሙሁራን ይስማሙበታል። ሀገራችን ኢትዮጲያ የጥንት የመንግስት ምስረታ ታሪክ ያላት ሀገር ብትሆንም ነገስታትና ስርአቶች በተለዋወጡ ቁጥር በሚፈጠሩ ቅራኔዎች እና መደባዊ እና ስርአታዊ ስር ነቀል ለዉጦች በሚፈጠሩት አለመግባባት እና እነዚህን በዉይይት እና በንግግር በጠረጴዛ ዙሪያ ከመፍታት ይልቅ በሀይል እና በትጥቅ ትግል አዙሪት የእርስ በርስ ጦርነት እና ግጭት ምክኒያት የሀገረ መንግስት ግንባታችን ያልተጠናቀቀ ሀገር ሆነናል።

ይህንን በአግባቡ በመገንዘብ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ተቋቁሞ ወደ ስራ በመግባት በቅርብ ጊዜ የተካሄደዉ ሀገራዊ ምክክር በአይነቱ የተለየ እና ዉጤታማነቱ የተመሰከረለት መሆኑ እንደ ሀገር ባልተግባባናቸዉ ዋና ዋና ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ ተግባብተን ለቀጣይ ሀገረ መንግስት ግንባታ መሰረት ከመጣሉም በተጨማሪ በቀጣይ አለመግባባቶች እና ግጭቶች ሲፈጠሩ እንኩዋን

በጠረጴዛ ዙሪያ በመይይት እና በንግግር አለመግባባትን የመፍታት ባህልን ለማዳበር ምቹ ሁኔታ የፈጠረ ነዉ ብሎ መዉሰድ ይቻላል። በመሆኑም አንድ ጊዜ ብቻ ምክክር አካህደን ከችግር የምንወጣበት ሳይሆን አለመግባባትን በንግግር እና በመይይት መፍታትን ባህል ለማድረግ ሁሉም አካል የራሱን ኃላፊነት ሊወጣ ይገባል።

ከላይ የብዘሃነት አስተዳደርን ዉጤታማ ለማድረግ በስራ ላይ ሊዉሉ የሚችሉ አማራጮች ማለትም የፌዴራል ስርአት፣ የተግባቦት ዴሞክራሲ፣ ብዘሃ ህጎች መኖር፣ አሳታፊ ዴሞክራሲ ማዳበር ወዘተ ያልናቸዉ በባህሪያቸዉ መይይት ንግግር የሚጠይቁ ቢሆንም ባልተግባባንባቸዉ ዋና ዋና ጉዳዮች ላይ ለመግባባት የተደረገዉ ሀገራዊ ምክክርን እንደ እድል በመዉሰድ እና በመጠቀም ዉጤታማ እንዲሆን ሁሉም አካላት የድርሻቸዉን መወጣት ይገባል።

ክፍል 2፡- በፌዴራል ስርዓት የመንግስታት ግንኙነት

2.1. የመንግስታት ግንኙነት ምንነት

በፌዴራል ስርዓት የመንግስታት ግንኙነት ማለት በየደረጃዉ የሚገኙ የመግስት አሰተዳደሮች እርስ በእርሳቸዉ ያላቸዉን መስተጋብር የሚገልጽ ትንሰ ሃሳብ ሲሆን ግንኙነቱ የሁሉም መንግሥታት መገለጫ ባህሪ ሲሆን አፈጻጸሙ ከመንግስታት መንግስታት የሚለያይ ነዉ፤ በተለይ ከፌዴሬሽኖች ተፈጥሮአዊ ባህሪያ አኳያ የመንግሥታት ግንኙነት የተለየ ቦታ አለዉ ምክንያቱም ፌዴሬሽኖች በተናጥል መሻሻል የማይችል ህገመንግስትን መሠረት ያደረገ የስልጣን ክፍፍል መሰረት አድርገዉ ማለትም ለፌዴራመንግስት ለብቻ የተሰጠ እና/ወይም ለክልል መንግስታት ለብቻ የተሰጠ፤ በጣምራ የተሰጠ እና ቀሪ ሥልጣን ለፌዴራል ወይም ለክልል የተሰጠ በሚል የሚዎቀሩ ቢሆንም በህገመንግስት ስልጣንን በምንም መልኩ እንዳይገናኝ አድረጎ መከፋፋል የማይቻል በመሆኑ ትስስሩ አይቀሬ መሆኑ እና በተናጠል ተፈጻሚ የሚሆኑ እና ከግንኙነቱን የሚያመልጡ ዉስን ፖሊሲዎች ብቻ በመሆናቸዉ ትስስሩ እየጨመረ በሄደ ቁጥር የበለጠ ትብብርና ቅንጅት የሚጠይቅ መሆኑ ነዉ።

አሁን አሁን መንግስታት ለህበረተሰቡ የሚሰጡት አገልግሎት እየሰፋ በመምጣቱ ትስስር የመንግስታቱ መገለጫ እየሆነ ከመምጣቱ ጋር ተያይዞ የመንግስታት ግንኙነቱ የፌዴራል ስርዓቱ ተግባራዊ ከመሆን ጋር ተያይዞ የሚታይ ነዉ። የመንግስታት ግንኙነት ተዋናኞች እንዱ የሌላዉን አቅም (ማለትም በህግ የተሰጠ ስልጣንን፤ፈንድ፤ተቋሚዊ አቅም፤ቴክኒካዊ ብቃትን፤መረጃ)

የራሳቸዉን ግብ ለማሳካት ሲለሚፈልጉት ትስስሩ መኖር የግድ ይላቸዎል (አግራኖፍ,2004; ዋትስ, 2008 ; ራይት, 1974)።

ከዚህ በተጨማሪም ፌደሬሽኖች በቀጥታ በህዝብ የተመረጡ እና ለአንድ ህዝብ የሚሰሩ ቢያንስ ሁለት መንግሥታት ያሏቸዉ በመሆኑ ለዚህ አንድ ማህበረሰብ የተቀናጀ፤ የተጣጣመ እና ሁሉም እኩል ዕድል የሚያገኝበት አገልግሎት ማቅረብ የሚጠበቅባቸዉ መሆኑ የመንግስታት ግንኙነቱ የበለጠ ተፈላጊ ያደርገዎል።

በመሆኑም የመንግስታት ግንኙነት የፌደራል ሥርዓት ተግባራዊነት ዋነኛ መገለጫዎች ተደርጎ ይወሰዳል። የመንግስታት ግንኙነቱ የፌደራል ሥርዓቱ በትክክል እንዲሰራ ቀጣይነት ያለዉና የተረጋጋ እዲሆን ወሳኝ በመሆኑ የፌደራል ሥርዓቱ ኖርሸ ሲስተም፣ ላይፍ ብለድ፤ የሞተር ዘይት ተብለዉ በንጽጽራዊ ሁኔታ ይታያል። በመሆኑም በዚህ ክፍል የመነግስታት ግንኙነት ጠቀሜታዎች፤ የግንኙቱ ገጽታዎች ቸእና አግባቦች በዝርዝር ቀርበዋል

2.2.የመንግስታት ግኝኙነት ጠቀሜታዎች

ለመንግስታት ግንኙነት መኖር ወሳኝ ከሆነ ጉዳዩች አኳያ በዋናነት የሚገለጹት የህገመንግስት የስልጣን ክፍፍል ጋር ተያይዞ የስልጣን ክፍፍሉ ትስስርን ሙሉ በሙሉ ማስቀረት የማይችል መሆኑ እና በተለይ ጣምራ ስልጣን ባለበት ሁኔታ ግንኙነቱን የበለጠ የሚያደረጉ ሁኔታዎች መኖር ሲሆን ሌላዉ በፌደሬሽኖች ዉስጥ ያሉ መንግስታት ህገመንግስትን መስረት አድርጎ የተሰጣቸዉ ሃላፊነት ለመወጣት የሚስፈልጋቸዉ ዉጭ እና በራሳቸዉ የሚሰበስቡት የገቢ መጠን አለመመጣጠንም የፊስካል ክፍተት ይፈጥራል ይህ ክፍተቱ የተለያየ ቅርጽ ያለዉ (የተዋረድ ክፍተት ፤ የጎንዩሽ ክፍተት) ሲሆን ክፍተቱን የማጣጣም ተግባር ፊስካል የመንግስታት ግንኙነት አስፈላጊ ያደርገዎል። ይህ ፊስካል የመንግስታት ግንኙነት መንግስታቱ የግድ እንዲገናኙ እና በጋራ እንዲሰሩ ያደርጋቸዋል ይህም ለግንኙነት መኖር እንደ አንድ ዋና ምክንያት ተደርጎ ይወሰዳል (ብሮድወይ እና ፍላተር, 1982; ቦክስ እና ማርቲኒዝ ቫንኩይዝ, 2006; ሳህ,2007) ። በፌደሬሽኖች ዉስጥ ያሉ አባል መንግስታት መካከል ያለዉ ያልተመጣጠነ የአቅም ልዩነት ምክንያት በአንድ ሃገር ዉስጥ የሚኖሩ ዜጎች አንጻራዊ በሆነ ተመጣጣኝ የሆነ የታክስ መጠን በአንጻራዊ መልኩ ተመጣጣን የሆነ አገልግሎቶችን ለማቅረብ አዳጋች ይሆናል ስለሆነም የፌደራል መንግስቱ እና ሌሎች በአንጻራዊ መልኩ የተሻለ አቅም ያላቸዉ አባል መንግስታት በእነዚህ መንግስታት ዉስጥ የሚኖሩ ዜጎች እኩል የሆነ

እድል እንዲፈጠርላቸዉ መደገፍ በአንድ ፌደሬሽን ዉስጥ በጋራ ለመኖር ከወሰኑ አካላት የሚጠበቅ ነዉ። በመሆኑም ድጋፉን ለማስተባበር እና ለማቀናጀት የመንግስታት ግንኙነት አስፈላጊ ይሆናል።

ሌላዉ እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ባለብዙ ብሄር በሆኑ ፌደሬሽኖች እና የፌደሬሽኖቹ አባል ክልሎች አሰፋፋፈርን፤ ቋንቋን፤ማንነት እና ፈቃድ ላይ መሠረት አድርገዉ የተዋቀሩ ፌደሬሽኖች ዉስጥ የሚገኝ የባህል፤የቋንቋ እና የማንነቶች ብዝሃነትቶች እና ከዚህ ጋር ተያይዞ የመኖሩ የማህበራዊ፤ፖለቲካዊ እና አኮኖሚዊ ፍላጎቶች አሰተሳስሮ እና አጣጥሞ ለመሄድ ቸእና አንድ አካታች የሆነ ፌደራላዊ አስተዳደር ለመገንባት የመንግስታት ግንኙነት ወሳኝ ሚና ይጫወታል።

በጥቅሉ የመንግስታት ግንኙነት ጠቀሜታቸዉም ሲታይ ደግሞ የፌደራል ሥርዓቱ በአግባቡ እንዲሰራ እና ከተለዋዋጭ ሁኔታዎች ጋር አብሮ ለመሄድ፤ፌደሬሽኖች በየጊዜዉ ለሚያጋጥማቸዉ ችግሮች ወቅታዊ መፍትሄ እየሰጡ ለመሄድ ሁሌም በየወቅቱ የሚያጋጥሞቸዉን ተለዎዎጭ ሁኔታዋች እና ችግሮች ለመፍታት ወደ ህገ መንግስት ማሻሻል እና ትርጉም ማሰጠት ሁኔታ ሳይገቡ በህገ መንግስቱ መንፈስ እና ሃገራዊ እና ክልላዊ ፍላጎት አንጻር እየተመካከሩ ለወቅታዊ ተለዋዋጭ ሁኔታዎች እና ችግሮች የፌደራል ሰርዓቱን ሂደት እና አስተሳሰብ በሚያጠናክር መልኩ እየፈቱ ለመሄድ፤ፖሊሲዎችን ስትራቴጅዎችን እና እቅዶችን አጣጥሞና አሰተሳስሮ ለመተግበር፤ዉጤታማና ቀልጣፋ የሕዝብ አገልግሎት ለማቅረብ ፤ የሚፈጠሩ አለመግባባቶችን በየጊዜዉ የፌደራል ሥርዓቱን በሚያጠናክር መልኩ እየፈቱ ለመሄድ ፤በመደጋገፍ በጋራ ለመልማት፤ የግልና የጋራ ኃላፊነት/ሥልጣንን አጣጥሞ ለማስኬድ፤ ድግግሞሽን ለማስቀረት እንደሚጠቅም ታሳቢ ይደረጋል (ዋትስ,2008; ኤላዛር, 1987;አግራኖፍ,2004; በርገስ,2006 ;ፍሊፖቪ እና ሊሎች, 2004; ዊብልስ, 2005 ; ራይት, 2000)።

የመንግስታት ግንኙነት በመንግስታት መካከል የሚፈጠሩ አለመግባባቶችን ከመፍታት አኳያ ሰፊ ሚና የሚጫወት በመሆኑ በፌደራል ስርዓት በመንግስታቱ መካከል የአለመግባባት ምንጮች ሊሆኑ የሚችሉ ጉዳዩችን በዝርዝር በመለየት የመንግስታት ግንኙነቱ አለመግባባቶችን በምክክር እና በድርድር መፍታት የሚቻልበት መድረክ ሆኖ ሊገለግል ይችላል። በመሆኑም ሚክኢስን (2001) የካናዳን ፌደሬሽን መሰረት አድረጎ በፌደሬሽኖች በመንግስታት መካከል የአለመግባባት ምንጭ ሊሆኑ የሚችሉ ጉዳዩችን በማለት ከዘህ በታች የተዘረዘሩ ጉዳዩችን አስቀምጧል

- ✓ በህገመንግስት ከተሰጠ የስልጣን ወሰን አተገባበር ጋር ተያይዞ ሊፈጠሩ የሚችሉ አለመግባባቶች

- ✓ በገቢ ክፍፍል እና ከተዋረድ የፊስካል አለመመጣን ጋር ተያይዞ ሊፈጠሩ የሚችሉ አለመግባባቶች
- ✓ ከጎንዮሽ የፊስካል አለመመጣጠን ጋራ ተያይዞ ሊፈጠሩ የሚችሉ አለመግባባቶች
- ✓ የፌደራል መንግስት ካለዉ ወጭን መሸፈን የሚስችል ከፍተኛ አቅም እና ይህን አቅም ስራ ላይ ለማዋል ከሚኖሩ የአፈጻጸም ሂደቶች ጋር ተያይዞ ሊፈጠሩ የሚችሉ አለመግባባቶች
- ✓ ከባቢያዊ የልማት ፖሊሲ ጋር ተያይዞ የትኛዉ ከባቢ ምን ያህል የፌደራል መንግስቱን ድጋፍ ያግኝ በሚል ሊፈጠሩ የሚችሉ አለመግባባቶች
- ✓ የተፈጥሮ ሃብትን ከማስተዳደር እና ከመቆጣጠር ጋር ተያይዞ ሊፈጠሩ የሚችሉ አለመግባባቶች
- ✓ የቋንቋ፤የባህል፤የሃይማኖት ብዝሃነቶችን ከማስተናገድ ጋር ተያይዞ ሊፈጠሩ የሚችሉ አለመግባባቶች
- ✓ የፌደራልም ሆነ የክልል መንግስታት በሚመሩ ግለሰቦች መካከል ሊፈጠሩ የሚችሉ አለመግባባቶች
- ✓ የተጠናከረ እና ተቋማዊ የሆነ የመንግስታት ግንኙነት ሰርዓት አለመኖር እና ከዚህ ጋር ተያይዞ በተናጥል የሚከናወኑ ተግባራት እና የሚወሰዱ ርምጃዎቸ በአንድም ይሁን በሌላ መልኩ ለአለመግባባት ምንጭ ለሆን ይችላል።

የመንግስታት ግንኙነት ከዚህ በላይ የተዘረዘሩትን አለመግባባቶች ለመፍታት ቀልፍ መሳሪያ ሲሆን የመንግስታት ግንኙነት የፌደራ ስርዓቱ ዋነኛ መገለጫ ሆኖ ይወሰዳል ይህንም ጉዳይ ኤላዛር (1987፡12) አጠር ባለ እና ገላጭነት ባለዉ መልኩ እንደሚከተለዉ አስቀምጦታል, ፌደራሊዝምን ፌደራሊዝም የሚያሰኘዉ ጉዳይ የተወሰኑ ተቋማት መኖር አለመኖር ሳይሆን በፖለተካ ሂደት ዉስጥ ተሳተፎ ባላቸዉ አካላት መካከል ያለ ግንኙነት ተቋማዊ መሆን ነዉ ስለሆነም በስርዓቱ ተሳታፊ በሆኑ አካላት መካካል ተገማች፤የሚተነበየ፤ የሚታወቅ የአሰራር እና የግንኙነት ሥርዓት ያለዉ ግንኙነት የሌለበት ፌደራላዊ ሰርዓት ዉጤታማነቱ እና ቀጣይነቱ አጠያያቂ ይሆናል። የመንግስታት ግንኙነት ለፌደራ ስርዓቱ ምን ያህል ወሳኝ መሆኑን ንጽጽራዊ በሆነ መልኩ ለማየት የሰዉን ልጅ አጽም ህይወት የሚያላብሱት ስጋና ደም እንደሆኑት ሁሉ በፌደራል ሥርዓት ህገመንግስቱን ጨምሮ ሌሎች ተቋማት ህይወት ያለዉ እንቅስቃሴ እንዲያደርጉ የሚያስችላቸዉ የመንግስታት ግንኙነት ነዉ ቢባል የተጋነነ

ሊሆን አይችልም። እንግዲህ የመንግስታት ግንኙነት ይህን ያህል አስፈላጊ እና ጠቃሚ ከሆነ ግንኙነቱ የሚፈጸምበት አግባብ እና ገጽታዎች በዘርፉ እስከአሁን ካሉ ጥናቶች በመነሳት በቀጣይ ክፍሎች በዝረዝር ቀረቧል።

2.3.የግንኙነቱ ገጽታዎች

አስካሁን በመንግሥታት ግንኙነት ዙሪያ ከተካሄዱ ጥናቶች በመነሳት የመንግሥታት ግንኙነቶች የሚካሄድባቸዉን ገጽታዎች እንደሚከተለዉ መከፋፈል ይቻላል፤ መደበኛና መደበኛ ያልሆኑ፤ተቋማዊ የሆኑ እና ጊዜያዊ በሆነ መልኩ የሚካሄዱ፤ የጎንዩሽና የተዋረድ ገጽታ ያላቸዉ ፤ ባለብዙና የሁለትዩሽ የግንኙት ገጽታ ያላቸዉ ሃገራዊ ወይም ከባቢያዊ የሆኑ ፤በአንድ ፖሊሲ ዘርፍ ወይም በአጠቃላይ ጉዳዩች ላይ የሚያተኩሩ እና የተለያዩ የግንኙነት ገጽታዎችን በማቀናጀት የሚካሄዱ።፤

እነዚህ የተለያዩ ገጽታዎች ያላቸዉ ግንኙቶች በፌደሬሽኖች ዉስጥ የፌደራል መንግስቱን አስፈጻሚ አካል የሚመራዉ አካል ከሁሉም የክልሎችን አስፈጻሚዉን አካል ከሚመሩ አካላት ጋር ቁልፍ በሆኑ ሃገራዊ አጀንዳዎች ላይ የሚመክር ባለብዙ ዘርፍ / ሃገሪዊ የሆነ አጠቃላይ ጉዳዩችን በሚያይ መልኩ የሚደራጁ ሲሆን በሌላ መልኩ ሴክቶራል የሆነ ሴክቶራል በሆነ የፖሊሲ ጉዳይ የሚያተኩር በፌደራ ሆነ በክልል ደረጃ የተለያዩ ሴክተሮችን የሚመሩ አካላት የሚገናኙበት ባለብዙ ዘርፍ/ሀገራዊ የሆኑ ሴክቶራል መድረኮች ሊኖሩ ይችላሉ።

የፌደራ መንግስቱን ከተወሰኑ የከባቢ መንግስታት አስፈጻሚዎች ጋር በአጠቃላይም ሆነ ሴክቶራል በሆኑ ጉዳዩች ላይ የሚገናኝ ከባቢዊ የሆነ አጠቃላይ እና ሴክቶራል መድረኮች ይኖራሉ።

የጎንዩሽ የመንግስታት ግንኙነት ገጽታ ስንመለከት ሁሉንም የክልል መንግስታት በአጠቃላይ ጉዳይም ሆነ በሴክቶራል ጉዳዩች ባአንድ ላይ የሚያገናኝ መድረክ የጎንዩሽ ባለብዙ ዘርፍ አጠቃላይ እና ሴክቶራል መድረኮች ይኖራሉ ከዚህም ሌላ የጎንዩሽ ከባቢዊ የሆኑ በአጠቃላይም ሆነ በሴክቶራል ፖሊሲ ጉዳዩች ላይ የተወሰኑ ከባቢያዊ መንግስታትን የሚገናኙ መድረኮች ይኖራሉ። ከላይ የተዘረዘሩት በዋናነት በህግ አስፈጻሚዉ በኩል የሚኖሩ የግንኙነት ገጽታዎች ሲሆኑ የህግ አዉጭዉም ሆነ የህግ ተርጓሚዉ በተመረጡ ጉዳዩች ላይ ከላይ የተዘረዘሩት ገጽታዎች ያላቸዉ መድረኮች ሊፈጥሩ ይችላሉ።

በየደረጃዉ በፌደራ መንግስት እና በክልል መንግስታት፤ በክልል መንግስታት እርስ በዕር ከዚም አልፎ የፌደራል መንግስት ከክልሎች በታች ካሉ የአስተዳዳር አካለት እንዲሁም የክልል መንግስታት ከእነርሱ በታች ካሉ አስተዳዳር አካላት ከላይ የተዘረዘሩትን የግንኙነት ገጽታዎች መሰረት ያደረጉ ግንኙነቶች የሚያሳለጡባቸዉ መድረኮችን፤ኮንፈረንሶች፤ምክርቤቶች፤ማህበራት በመፍጠር የመንግስታት ግንኙነቶችን ማካሄድ የተለመደ ነዉ።

አንድ ወይም ሌላ ገጽታ ላለዉ የግንኙነት መድረክ መፈጠር እና መድረኩ ተቋማዊ ቅርጽ እየያዘ መሄድ አስተዋጽኦ የሚደርጉ ከፌደሬሽኖቹ አፈጣጠር እና ባህሪ፤ በየጊዜዉ ከሚኖሩ ተለዋዋጭ ከሆኑ ፖለቲካዊ ፤ኢኮኖሚዊ እና ማህበራዊ ሁኔታዎች ጋር የሚገናኙ ምክንያቶች ይኖራሉ።

ሁሉም ፌደሬሽኖች አንድ ወይም ሌላ ገጽታ ያለዉ የመንግስታት ግንኙነቶች ያላቸዉ ሲሆን የግንኙነቱ ተቋማዊ እና መደበኛ መሆን አለመሆን እንደየ ፌደሬሽኖቹ ነባራዊ ሁኔታ የተለያየ ደረጃ ይኖረዎል።

2.4. የግንኙነቱ አግባቦች

በፌደሬሽኖች የመንግስታት ግንኙነት አግባቦች የሚከፋፈሉባቸዉ፤የሚገለጹባቸዉ፤ የሚደራጁባቸዉ ብዙ መንገዶች ያሉ ሲሆን አንዱ የሚከፋፈሉበት ስርዓት ሁሉንም ዝርዝር የሆኑ የግንኙነቱ አግባቦችን አሞልቶ ላይዝ ይችላል።። ቢሆንም በዘርፉ በተደረጉ ጥናቶች በፌዴሬሽኖች ወሳኝ የሆኑ የግንኙነት አግባቦች ተከፋፍለዉ የሚታዩባቸዉ እና የሚገለጹባቸዉ መንገዶችን በመለየት የመንግስታት ግንኙነቶችን አግባቦችን ለማጥናት የሚያስችል ሁኔታ መፍጠር ተችሏል (ኪንክኤድ, 2008; ቦሊየር, 2009; ሲመርማን, 2001)

የመንግስታት ግንኙነቶች የሁሉም ፌደሬሽኖች የስርዓቱ አካል እና አንዱ ዋንኛ መገለጫ ቢሆኑም ፌደሬሽኖች የሚኖራቸዉ የግንኙነት አግባቦች ሁሌም አንድ አይነት እዳልሆነና በፌደሬሽኖች ከሚኖሩ ተለዋዋጭ ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚዊ ሁኔታዎች ጋር ተያይዞ የተለያየ መልክ ሊኖራቸዉ እንደሚችል በዘርፉ የተደረጉ ጥናቶች ያመላክታሉ (ኪንክኤድ,2000; ዋትስ,2008; ቦሊየር,2009)።

በፌደሬሽኖች የመንግስታት የግንኙነቱ አግባቦችም በትብብር ላይ የተመሰረቱ፤ በአለመግባባት ላይ የተመሰረቱ፤ በአንዱ አካል ጫና አድራጊነት ላይ የተመሰረተ፤በዉድድር ላይ የተመሰረተ፤በቁጥጥር ላይ የተመሰረተ በሚሉ ማዕቀፎች ማጥናት ቢቻልም

የአንድ ፌደሬሽን የመንግስታት ግንኙነት ይህን የግንኙነት አግባብ ብቻ የተከተለ ነዉ ብሎ መደምደም አይቻልም። ለምሳሌ በዩናትድ ስቴትስ በፌደራሉ እና የክልል መንግስታት መካከል ያለዉ ግንኙነት በትብብር ላይ የተመሰረተ፤በጫና ላይ የተመሰረተ እና በዉድድር ላይ የተመሰረተ በሚሉ አግባቦች በፌደራሊዝም አጥኝ ምሁራን የተተነበትን ሁኔታዎችን ማየት ይቻላል (ሲመርማን, 2000). በፌደሬሽኖች የመንግስታት ግንኙነቶች በተለያዩ አግባቦች ሊፈፀሙ እንደሚችሉ እና አንዱን ወይም ሌላዉን አጣምረዉ ሊይዙ እንደሚችሉና ከጊዜ ወደ ጊዜም ተለዋዋጭ ሊሆን እንደሚችል የብዙ ፌደሬሽኖች የመንግሥታት ግንኙነት ተሞክሮዎች ያሳዩናል። በፌደሬሽኖች በተለያዩ ጊዜያት እንዱ ወይም ሌላዉ የግንኙነት አግባብ ጎልቶ ሊወጣም ይችላል። ለተለያዩ የግንኙነቱ አግባቦች ጎልቶ መዉጣት አሰተዋጽኦ የሚያደርጉ የተለያዩ ምክንያቶች እንዳሉ በዘርፉ የተደረጉ ጥናቶች ያመላክታሉ (ኪንክኤድ,2000; ዋትስ,2008; ቦሊየር,2009)።

ለአንዱ ወይም ሌላዉ አይነት የግንኙነት አግባብ ጎልቶ እንዲወጣ ከሚያደረጉት ዋና ዋና ምክንቶች አንዱ የፖለቲካል ፓርቲዎች አደረጃጀት እና የፖለቲካ ዳይናሚክሱ እንደሆነ ይገለጻል። በአንድ ፌደሬሽን ዉስጥ የፓርቲ ስርዓቱ የተማከለ መሆን እና አለመሆን በመንግስታት ግንኙነት አግባቦች ላይ የጎላ ልዩነት እንደሚፈጠር በዘርፉ የተደረጉ ጥናቶች ያመላክታሉ (ፍሊፖቪ, ኦርዶሽኪቪ እና ሲቫስቶቪ ,2004). ከዚህ ጋር በተያያዘ የፓርቲ ስርዓት በመንግስታት ግንኙነት ላይ ስለሚያሳድረዉ ተጽኖ በምሳሌ በማስደገፍ ዋትስ (2008፣ 146) እንደሚከተለዉ ገልጾታል፣

አንድ ዋና በመንግስታት ግንኙነትን ባህሪ ላይ ተጽእኖ የሚፈጥር ጉዳይ የፓርቲ ስርዓቱ ባህሪ ነዉ። አንድ ፓርቲ ወይም የፓርቲዎች ጥምረት የፌደራል መንግስቱንም ሆነ የክልል መንግስታቱን በሚቆጣጠሩበት ወቅት እንደ ህንዱ ኮንግረንስ ፓርቲ ቀደም ሲሉት አስርት አመታት፤በማሌዥያ አሊያንስ ፓርቲ፤ በሚክሲኮ 2000 ፓርቲ ኢኒስቲቱሲዮን ሪቮሉሲዮን ፤ በደቡብ አፍሪካ አፈሪካን ናሽናል ኮንገርንስ እንዲሁም በኢትዮጵያ ኢህአዴግ የፌደራሉ ፓርቲ መሪዎች በክልል ፓርቲ መሪዎች እና ተቋማት ላይ ከፍተኛ ጫና መፍጠር ያስችላቸዎል በዚህ ሁኔታ ብዙዎቹ የመንግስታት ግንኙነት ጉዳዮች በፌደራል መንግስቱ እልባት የሚገኙ ሲሆኑ የፓርቲ ቻናሉም ዋናዉ የግንኙነት መድረክ ይሆናል። በሌሎቹ ፌደሬሽኖች ሁለቱ የመንግስት አካላት በተለያዩ ፓርቲዎች ቁጥጥር ስር ሲሆኑ በካናዳ፤ በአዉስትራሊያ እና ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በህንድ እደታየዉ መደበኛ የሆኑ የመንግስታት ግንኙነት ሂደት እና ተቋማት ዋና የመንግስታት ግንኙነት ጉዳዮች የሚታዩበት የዉይይት፤ ድርድር እና ትብብር ቻናሎች ይሆናሉ።

በሌላ በኩል ህገመንግስታዊ የስልጣን ክፍፍልን መሠረት አድረጎ ለፌደራ መንግስቱ እና ለክልሎች ስልጣን የተከፋፈለበት አግባብ የመንግስታት ግንኙነት የሚፈጸምበት አግባቦች ላይ የራሱን አስተዋጽኦ ይኖረዎል።

ሁለቱም መንግስታት የሕግ ማዉጣት፤ ማስፈጸምና የዳኝነት ስልጣን ካላቸዉ እና ሁለቱም መንግስታት በብዙ ጉዳዩች ላይ ፖሊሲ የሚያወጡና የሚያስፈጽሙ ሲሆን ይህ ሂደት ወደ ዉደድር ሊያመራቸዉ ይችላል። ይኽም ማለት የስልጣን ክፍፍሉ ጣምራ ፌደራሊዝም የሚመስል ቅርጽ ካለዉ ሁለቱም መንግስታት የራሳቸዉን ጉዳይ ያለማንም ጣልቃ ገብነት የመፈጸም እንቅስቃሴ ዉስጥ ይገባሉ ተብሎ ስለሚታሰብ የሚኖራቸዉ ግንኙነት ቢያንስ በንድፈ ሃሳብ ደረጃ እንኳን ቢሆን በዉድድር ላይ የተመሠረተ እእንደሚሆን ይገመታል። በዉድድር ላይ የተመሰረተዉ ግንኙነት በፌደረል መንግስቱ እና በክልሎች እንዲሁም በክልሎቹ እርስ በእርስ ሊሆን ይችላል። ወድድሩ ሁለት ገጽታዎች ያሉት ሊሆን ይችላል እነርሱም ገንቢ እና አፍራሽ የሆኑ ዉድድሮች ናቸዉ። ኢፍህታዊ እና በስርዓት የማይመራ ወድድር አጥፊ የመሆን እድሉ ሰፊ ሲሆን ፍህታዊ እና ሰርዓት ያለዉ ዉደድር ግን ገንቢ የሆነ ገጽታ ይኖረዎል። ገንቢ በሆነ ዉድድር አሸናፊዉም ሆነ ተሸናፊዉ የሚያተረፉበት ይሆናል (ደች 2006)። ከዚህ ጋር ተያይዞ በአግባቡ የተደራጀ የመንግስታት ግንኙነትም ዉድድሩን ፍህታዊ እና በስርዓት የሚመራ እና ገንቢ ዉድድር እንዲሆን የራሱን ሚና ይጫወታል።

ሌላዉ የግንኙነት አግባብ በጫና ላይ የተመሰረተ የግንኙነት አግባብ ሊሆን ይችላል። በጫና ላይ የተመሰረተ የመንግስታት ግንኙነት መነሻዉ የፌደራ መንግስቱ በተለያየ መልክ በክልሎች ጉዳይ ጣልቃ መግባት ጋር የተያያዘ ነዉ። ጣልቃ ገብነቱም በተለያዩ ሁኔታዎች ሊገለጽ ይችላል ለምሳሌ ኪንክኤድ (2008፡60) የዩኤስን ተሞክሮ መሰረት ዕድረጎ ጣልቃ ገብነቱ የሚፈጸምባቸዉን አግባቦች እንደሚከተዉ አስቀምጦል፡

ሁለቱም መንግስታት ህግ ማዉጣት በሚችሉባቸዉ ጉዳች ላይ ክልሎች ህግ ቢያወጡም የፌደል መንግስቱ በዚያዉ ጉዳይ ላይ ህግ በማዉጣት የክልሎች ህግ ሥራ ላይ እንዳይዉል በማድረግ፤ የፌደራል መንግስቱ ያለዉን የፋይናንስ አቅም በመጠቀም ክልሎች ድጎማ ለመዉሰድ ማሟላት ያለባቸዉን ሁኔታዎች በማስቀመጥ ይኽንም ከፌደራሉ መንግስት ፍላጎት ጋር በማስተሳሰር ክልሎች የፌደራል መግስቱን ግብ እንዲፈጽሙ ጫና ማድረግ፤ የመንግስታት ግንኙነት ተቋማትን በማዳከም ግንኙነቱን በፌደራ መንግስቱ ፍላጎት ብቻ የሚመራበት አቅጣጫ መከተል፤ የፖለቲካዊ ትብብር

መዳከም፤ ጉዳዩችን በፍርድ ቤቶች ዉሳኔ ላይ ተመስርቶ ለማስፈጸም መንቀሳቀስ ዉሳኔዎች የፌደረል መንግሰቱን ሃሳብ የሚደግፉ ሲሆን

በጫና ላይ የተመሰረተ ግንኙነት ከላይ በተዘረዘሩት መልኩ ሊፈጸም የሚችል ሲሆን ግንኙነቱም በፌደራል መንግስቱ እና በክልል መንግስታት መካከል የሚከሰት ነዉ።

በትብብር አግባብ የሚፈጸምን የመንግስታት ግንኙነት ስንመለከት ደግሞ ለግንኙነቱ መሰርት የሚሆነዉ የግንኙነቱ ተዋንያን የጋራ ጉዳይን ለመፈጸም ወይንም ችግርን ለማስወገድ የትብብር አስፈላጊነት ላይ የጋራ ሃሳብ ሲይዙና ለትብብሩ መሳካት ያላቸዉን ስልጣን ለማካፈል ፈቃደኛ ሲሆኑ ነዉ። እንደ በትብብር ላይ የተመሰረተ ፌደራላዊ ስርዓት ንድፈሃሳብ ትብብር ሊኖር የሚችለዉ ትብብርን አስፈላጊ የሚያደርግ መነሻ ሁኔታዎች መኖር ነዉ፣ ለምሳሌ ወሰን ተሻጋሪ የሆነ ችግር መኖር፤በጋራ የሚለማ ሀብት መኖር፤በቅንጅት እና በትብብር የሚፈጸሙ ፖሊሲዎች መኖር፤የተቀላጠፈ እና የተናበበ አገልግሎት ለማህበረሰቡ ለማቅረብ በጋራ መስራት አስፈላጊነት መኖር፤ ትስስር እና ትብብርን በማጠናከር የራስ አስተዳደር እና የጋራ አስዳደርን ሚዛን ጠብቆ ለመፈጸም ወዘተ.. እና በመንግስታት ግንኙነት ተዋንያን መካከል የእኩልነት፤ የአጋርነት እና የመተማመን መንፈስ መኖር በትብበር አግባብ ለሚፈጸም ግንኙነት መሰረት መሆኑን በዚህ ዙሪያ የተደረጉ ጥናቶች ያመላክታሉ (ቤንሰን እና አንድሪዉ, 2006)።

2.5. የመንግስታት ግንኙነቱ የሚፈጥራቸዉ ተቋማት እና የሌሎች ፌደሬሽኖች ተሞክሮ

ከላይ በተዘረዘሩት ገጽታዎች እና አግባቦች መደበኛ በሆነ መልኩ የሚፈጸሙ የመንግስታት ግንኙነቶች የመንግስታት ግንኙነቶቹ የሚካሄዱባቸዉ ፎረሞች፤ ኮንፈረንሶች፤ ካዉንስሎች፤ ኮሚቴዎች፤ማህበራት የመሳሰሉት ተቋማዊ አደረጃጀቶች የሚፈጥሩ ሲሆን የነዚህ አደረጃጀቶች የተቋማዊነት ጥንካሪያቸዉ እነዚህ አደረጃጀቶች ለመፈጠር መሰረት የሆናቸዉ የህግ ማዕቀፍ መኖር አለመኖር እና ካለም የህግ ማእቀፍ ደረጃ ማለትም ህገመንግስታዊ መሰረት ያለዉ፤ በፓርላማ የወጣ አዋጅን መሰረት ያደረገ፤ በአስፈጻሚ አካል የወጣ ደንብን መሰረት ያደረገ፤ የጋራ የመግባቢያ ስምምነት ብቻ መሰረት ያደረገ መሆን አንዱ የሚታይ ጉዳይ ነዉ። ሌላዉ ግንኙነቱ የሚካሄድበት የታወቀ ጊዜ እና ድግግሞሽ መኖር፤ በግንኙነቱ ተሳታፊ አካለት በግልጽ የሚታወቁ እና ተሳትፏቸዉም አጀንዳ ከመወሰን እስከ ዉሳኔ አሰጣጥ ድረስ የተረጋገጠ መሆን አለመሆን እንዲሁም የመንግስታት ግንኙነቱን

የሚያስተባብር በግንኙነቱ ተሳታፊ አካለት በጋራ የተቋቋመ አካል መኖር እና አለመኖር የግንኙነቱን የተቋማዊ መሆን አለመሆን ደረጃ የሚገልጹ ናቸዉ።

የመንግስታት ግንኙነትን መሰረት አድረገዉ መንግስታቱ በጋራ ለመስራት ሲወስኑ ዉሳኔያቸዉን ለማስፈጸም ዉሳኔያቸዉን የሚገልጹት በተለያየ መልክ ሲሆን ከነዚህም እንዱና ዋናዉ የመንግስታት ግንኙነት ስምምነቶች (Intergovernmental Agreements (IGA) ተብለዉ የሚታወቁት ናቸዉ። እነዚህ የመንግስታት ግንኙነት ስምምነቶች በፌደሬሽኖች በብዛት የሚፈረሙ እና ``የመንግስታት ግንኙነት ስምምነቶች የመንግስታት ግንኙነቶች የሚመሩባቸ የተለመዱ መሳሪያዋች ሲሆኑ በየአንዳንዱ ዓመት በጣም ብዙ ቁጥር ያላቸዉ ስምምነቶች በመንግስታቱ ግንኙነት አጋር አካላት በሆኑት መካከል በተለያዩ የፖሊሲ ጉዳዩች ላይ ይፈረማሉ። የሚፈረሙት ስምምነቶች በቁጥር በኦስትሪያ ሁለት መቶ አካባቢ፤ በብራዚል እሰከ ስምንት ሽህ ይገመታል ይህ በእንዲህ እንዳለ በስፔን ደግሞ በአንድ የሆነ ዓመት ዉስጥ አንድ ሽህ አካባቢ አሳሪ የሆኑ ስምምነቶች ይፈረማሉ። በስፔን፤ ብራዚል፤ሲዊዘርላንድ እና የተወሰኑ የፌደሬሽኑ አባል መንግስታት እንዲሁም ሌሎች ፌደሬሽኖች፣ ስምምነቶቹ ሪፖርት የሚደረጉበት እና የሚታተሙበት ስርዓት የሌለ በመሆኑ በጣም ሰፊ የሆነዉን ከስምምነቱ ጋር ተያይዞ ሊገኝ የሚችል የመረጃ ሃብት ግልጽነት የጎደለዉ አድርጎታል። የመንግስታት ግንኙነት ስምምነቶቹ የተለያየ ስም ይዘዉ የሚገኙ ሲሆኑ መጠሪያቸዉ የሚከተሉትን ያካትታል፡ ኮምፓክት፤ ኮንኮርዳትስ፤ኮንቪንሽንስ፤የትብብር ስምምነቶች፤ፕሮቶኮሎች፤የመግባቢያ ሰነዶች፤ ኮንቪኖስ እና ትሪቲስ (ዉሎች) የመሳሰሉትን የያዙ ኖቸዉ። በመንግስታት ግንኙነት ከሚፈጠሩ የመንግስታት ግንኙነት ስምምነቶች ሌላ የመንግስታት ግንኙነቱ ተሳታፊ አካላት የጋራ ጉዳዩቻቸዉን የሚያስፈጽሙባቸዉ. የጋራ ኤጀንሲዎች ፤የጋራ ፕሮግራሞች እና የመሳሰሉት መፍጠር የተለመደ ነዉ።

ክፍል 3 በኢትዩያ ፌደራላዊ ስርዓት የመንግስታት ግንኙነት የሚገኝበት ሁኔታ

3.1. የግንኙነቱ አስፈላጊነት

የባለብዙ ብሄር፤ ባህልና ሃይማኖት ማህበረሰብ የኢኮኖሚ፤ማህበራዊ እና ፖለቲካዊ ፍላጎቶችን ለማጣጣም፤የራስና የጋራ አስተዳደር በባለብዙ ብሄር ፌደሬሽን ነባራዊ ሁኔታ ዉስጥ አመዛዝኖ መተግበር እንዲሁም ሃገሪቱ የምትገኝበት ስር የሰደደ

ድህነት እና የዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ ችግሮች ለመሻገር በባለብዙ ፈርጅ እና ትብብር ላይ የተመሠረተ የመግስታት ግንኙነቶች አስፈላጊነት አጠያያቂ አይደለም።

ምክንያቱም የህገሪቱ ነባራዊ ሁኔታ እና የምትገኝበት ዉስበስብ ችግሮች በፌዴራል ሥርዓቱ ዉስጥ የማያቋርጥ እና ተከታታይነት ያለዉ በእኩልነት እና አጋርነት ላይ የተመሰረተ ምክክርን፤ድርድርን፤ የጋራ መግባባትን እና ሚዛኗዊነቱን የጠበቀን ዉሳኔን እና አፈጻጸምን ይጠይቃል።

በመሆኑም ከዚህ በመቀጠል እስከ አሁን በኢትዮጵያ ፌደሬሽን ሲተገበር የቆየዉን የመንግሥታት ግንኙነት ለግንኙነቱ መነሻ ከሚሆን ህገመንግሥታዊ ማዕቀፎች በመነሳት እና በቀጥታም ይሁን በተዘዋሪ ለመንግሥታት ግንኙነት መነሻ የሚሆኑ የህገመንግሥቱን አንቀጾች በዝርዝር በማየት ለግንኙነቱ መነሻ በሚሆኑበት አግባብ በዝርዝር ከቀረበ በኋላ በኢትጵያ በመተግበር ላይ ያለዉ የመንግስታት ግንኙነቶች ገጽታዎች እና አግባቦች እነዚህን ገጽታዎች እና አግባቦች እንዲይዙ ካስቻሉት መሠረታዊ ምክንቶች ጋር ተዳስሷል። በቀጣይም በኢ.ፌ.ዴ.ሪ መደበኛ የመንግስታት ግንኙነቶች ጋር ተያይዘ ያሉ ችግሮችን ለመሻገር ህጋዊ መሰረት ይጥላል ተብሎ የታሰበዉና በቀጣይ ወደ ተግባር እየገባ ሲሄድ የመንግስታት ግንኙነት ስርዓቱን ወደተሻለ ደረጃ ያሸጋግራል ተብሎ የሚታሰበዉን ከጥር /2013 ጀምሮ የፀደቀዉ የመንግስታት ግንኙነት ስርዓት ለመወሰን የወጣዉ አዋጅ ቁጥር 1231/2013 በአጭሩ ቀርቧል።

3.2. ህገ መንግሥታዊ ማዕቀፍ

በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገመንግስት በግልጽ ስለ መንግስታት ግንኙነት የተደነገጉ ድንጋጌዎች ባይኖሩም ከህገመንግስቱ አጠቃላይ ይዘት እና በተወሰኑ አንቀጾች ላይ ያሉ ድንጋጌዎች ለመንግስታት ግንኙነቱ እንደ ህጋዊ ማዕቀፍ ሁነዉ ሊገለግሉ የሚችሉበት አግባብ በመዳሰስ እንደሚከተለዉ ቀርቧል ።

በህገ መንግስቱ መግቢያ ላይ የተቀመጠዉ "አንድ የፖለቲካ እና የኢኮኖሚ ማህበረሰብ መመሥረት" ዓላማ እንደ አንድ የመንግስታት ግንኙነት መነሻ ሃሳብ አድረጎ መዉሰድ ይቻላል። ይህን አንድ የፖለቲካ እና የኢኮኖሚ ማህበረሰብን ለመመስረት ባለብዙ ገጽታ እና ተመጋጋቢ የሆነ የመንግስታት ግንኙነት መኖር የግድ ይላል።

ይህን የታሰበዉን አንድ የፖለቲካ እና ኢኮኖሚ ማህበረሰብ የመመስረት ሂደት ቀጣይነት ያለዉ ግንኙነት እና ትብብር የሚጠይቅ ከመሆኑም በላይ ሃገራዊና ክልላዊ ፍላጎቶች እና አቅሞችን የማቀናጀት፤ ቀልጣፍና እና ዉጤታማ በሆነ መልኩ ጥቅም ላይ የማዋል ፤በኢትዮጵያ ብሄር፤ብሄረሰቦች እና ህዝቦች መካካል ሁበረ ብሄራዊ ፌደራላዊ ዴሞክራሲዊ የሆነ የፖለቲካ አሰተሳሰብ፤ ባህል እና ኑሮ ዘይቤ እያሳደጉ መሄድን ይጠይቃል። ይህም ቀጣይነት ባለዉ፤ በአደረጃጀት እና በአሰራር ስርዓት የዳበረ እና በአጋርነት ላይ የተገነባ የሚተነበይ ከሆነ የመንግስታት ግንኙነት ዉጭ የሚታሰብ አይሆንም። ስለሆነም ይህ ህገመንግስታዊ ዓላማ ትልቅ የመንግስታት ግንኙነት ማዕቀፍ ሀኖ ሊያገለግል ይችላል።

ከዚህም በተጨማሪ የህገ መንግሥቱ የተለያዩ አንቀጾች ለመንግስታት ግንኙነት እንደ መነሻ ህገመንግስታዊ ማዕቀፎች ሊወሰዱ ይችላሉ ለምሳሌ አንቀጽ 1, ስያሜ; የኢትዮጵያ መንግስት ስያሜ የፌደራላዊ ዴሞክራሲዊ የመንግስት አወቃቀር ይደነግጋል ይህ ማለት የፌደራላዊ አወቃቀር በቅርጹ ቢኖንስ ሁለት መንግስታት (የፌደራል እና የክልል) በአንድ ሃገር ዉስጥ እንደሚኖሩ እና ለአንድ ሃገር ህዝብ በተለያየ ይዘት እና አግባብ ቢሆንም የህዝብ አገልግሎት እንደሚያቀርቡ በህዝብ ቀጥታ ለስልጣን እንደሚበቁና ለሕዝብም ተጠሪ እንደሆኑ ታሳቢ ያደርጋል። ስለሆነም እነዚህ በአንድ ሃገር ዉስጥ ያሉ ሁለት መንግስታት ሰፊ የሚያገናኟቸዉ ጉዳዩች እንደሚኖሩ ይገመታል በመሆኑም እነዚህ የሚያገናኟቸዉ ጉዳዩች ላይ በጋራ ለመስራት የመንግስታቱ ግንኙነት የግድ የሚል ጉዳይ ነዉ።

በህገመንግሰቱ አንቀጽ 48/1, የክልሎች ወሰን በተመለከተ ጥያቄ የተነሳ እደሆነ ጉዳዩን በሚመለከታቸዉ የክልል መንግስታት ሥምምነት መፈታት እንዳለበት ይደነግጋል ስለሆነም የተነሳዉ ጥያቄ በስምምነት ለመፍታት በክልሎች መካከል ግንኙነቶችን መፍጠር፤ መመካካር፤መደራደር እና ቀጣይ ግንኙነታቸዉን በሚያጠናክር መልኩ ጥያቄዉን መፍታት ይጠይቃል። በመሆኑም ይህ አንቀጽ የጎንዩሽ የመንግሰታት ግንኙነትን ለመካሄድ እንደ ህገመንግስታዊ ማዓቀፍ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል።

አንቀጽ 50/2,፣ ለፌደራል እና ክልል መንግስታት የህግ ማዉጣት፤ ማስፈጸም እና የዳኝነት ስልጣንን የሰጠ በመሆኑ የፌደራል ስርዓቱ የጣምራ ፌደራሊዝምን ቅርጽ የተላበሰ ቢመስልም በተግባር ግን የፌደራል መንግስቱ የፌደራል ፖሊሲዎችና ህጎችን የሚያስፈጽምበት የራሱ ተቋሞች በየክልሎች ከተወሰኑ ፌደራል ተቋማት ዉጭ ያላደራጀ በመሆኑ የክልሎችን ቢሮክራሲ መጠቀም የግድ ብሎታል በመሆኑም የፌደራል መንግስቱ የፌደራል ህጎችን እና ፖሊሲዎችን ለማስፈጸም ከክልሎች ጋር ግንኙነት ማድረግ የግድ ይለዎል ስለሆነም ይህን አንቀጽ ለግንኙነቶች መነሻ ማአቀፍ አድረጎ መወሰድ ይቻላል።

አንቀጽ 50/8, የፌደራል እና የክልል መንግስታት ስልጣን በህገመንግሰቱ የተወሰነ መሆኑን በመግለጽ የአንዱን ሥልጣን ሌላዉ ማክበር እንዳለበት ያስቀምጣል የአንዱን ስልጣን አንዱ አክብሮ በጋራ ለመስራት አንዱ የአንዱን ስልጣን የማይጋፋ ሆኖም የጋራ ጉዳችን በጋራ መፈጸም የሚያስችል የመንግስታት ግንኙነትን ሊኖር የግድ ይላል። ዞሮ ዞሮ የራስ አስተዳዳር እና ትስስርን አመዛዛኖ መሄድ የፌደራል ስርዓት ዋነኛዉ የመኖር አስፈላጊነት ጉዳይ ነዉ። ይህ ደግሞ ያለ መንግስታት ቀጣይነት ያለዉ ግንኙነት በአግባቡ እና በዘላቂነት ተግባራዊ ሊሆን አይችልም ። ስለሆነም አንቀጽ 50/8 እንድ ህገ መንግስታዊ ማእቀፍ አድረጎ ማየት ይቻላል።

አንቀጽ 50/9, የፌደራል መንግስቱ በአንቀጽ 51 ከተሰጡት ስልጣኖች እና ተግባሮች ዉስጥ እንደ አስፈላጊነቱ ለክልል መንግስታት በዉክልና መሥጠት እንደሚችል ያስቀምጣል እንግዲህ ዉክልና መስጠት እና መቀበል ጋር ተያይዞ የተሰጠዉ ወክልና ጋር ተያይዘዉ የሚኖሩ ወጭዎች አሸፋፈን፣ በዉክልና የተሰጡ ተግባራት አፈጻጸም ፤ በአፈጻጸም ሂደት የታዩ ጥንካሬዎች እና የተከሰቱ ዉስንነቶች በመጨረሻም የተገኙ ዉጤቶች ላይ ወካይ እና ተወካይ መነጋገራቸዉ እና መመካከራቸዉ አይቀርም ይህም የሚፈጸመዉ በመንግስታት ግንኙነት አግባብ መሆኑ ስለማይቀር ይኽን አንቀጽም እንደ አንድ ህገመንግስታዊ ማዕቀፍ መዉሰድ ይቻላል።

የፌደራል መንግስቱን ሥልጣን እና ተግባር የሚወስነዉ አንቀጽ 51/1 ለፊደራል መንግስቱ የሃገሪቱን አጠቃላይ የኢኮኖሚ፤የማህበራዊ የልማት ፖሊሲዎችና ስተራቴጅዎችን እና ዕቅዶችን የማዉጣት እና የመፈጸም ስልጣን ሲሰጠዉ በአንቀጽ 52/2/ሐ ለክልሎች በተሠጠዉ ስልጠን የክልሉን የኢኮኖሚ፤የማህበራዊ የልማት ፖሊሲዎችና ስተራቴጅዎችን እና ዕቅዶች የማዉጣት እና የመፈጸም ስልጣን ለክልሎች ተሰጥቷል። ለሁለቱም አካላት ተመሳሳይ ጉዳይ ሃገራዊ እና ክልላዊ በሆነ መልኩ እዲፈጽሙ ይጠበቃል በመሆኑም ፖሊሲዎች፤ስትራቴጅዎች እና የልማት እቅዶችን አንድ አይነት ማድረግ እንኳ ባይጠበቅ ምክንያቱም የፌደራል ስርዓት አንዱ ጠንካራ ጎኑ እንደ ላብራቶሪ ሆኖ ማገለገል በመሆኑ ቢያንስ በአንድ ሃገር ዉስጥ የሚተገበሩ ፖሊሲዎች፤ስትራቴጅዎች፤ዕቅዶች ማቀናጀት እና ማናበብ ይጠይቃል በመሆኑም ይህን ቅንጅት ለማከናወን እንደ ፖሊሲዉ፤ ስትራቴጅዉ እና ዕቅዱ ባህሪ ፖሊሲ ተኮር ወይም አጠቃላይ የሆነ ባለብዙ ዘረፍ ወይም የሁለትዮሽ፤ የተዎረድ ወይም የጎንዮሽ፤ሃገራዊ ወይም ከባቢያዊ የሆነ የመንግስታት ግንኙነት መኖር የግድ ይላል በመሆኑም እቀጽ 51 እና 52 ምንም

እንኳ የስልጣን ክፍፍልን የሚያመለክቱ አንቀጾች ቢሆኑም ገባ ብሎ ሲታዩ ግን በስልጣን ክፍፍሉ ዉስጥ ትብብርን እና በጋራ መስራትን የሚፈልጉ በመሆናቸዉ ለመንግስታት ግንኙነት መነሻ እንደ አንድ ህገመንግስታዊ ማዕቀፍ አድርጎ መውሰድ ይቻላል።

በኢ.ፌ.ዴ. ሪ ህገመንገስት ለህዝብ ተወካዩች ም/ቤት በተሰጠዉ ስልጣን ስር አንቀጽ 55/5 ም/ቤት የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ እደሚያወጣ የተደነገገ ቢሆንም ክልሎች በፌደራሉ መንግሥት የወንጀለኛ መቅጫ ህግ በግልጽ ባልተሸፈኑ ጉዳዩች ላይ ሕግ የማዉጣ ሥልጣን ይኖራቸዎል እንዲሁም በአንቀጽ 55/6 ሥር አንድ የኢኮኖሚ ማህበረሰብ ለመፍጠር ሲባል በፌደራል መንግስት ሕግ እንዲወጣባቸዉ የሚያስገድዱ ለመሆናቸዉ በፌደሬሽን ም/ቤት የታመነባቸዉ ጉዳዩች ሲኖሩ የፌደራል መንግስት የፍትሃብሄር ህጎችን ያወጣል ምንም እንኳ የፍትሃብሄር ህጎች በዋናነት የክልል ጉዳዩች ቢሆኑም። ይህ በሁለቱ አካላት በአንድ ጉዳይ ላይ ህግ የማዉጣት ሂደት ሊኖር የሚችልበትን ሁኔታዎች ያመላክታል። ስለሆነም ህጎቹ በሚቀረጹበት ሁኔታ ተቃርኖ እንዳይፈጥሩ ቢያንስ ቢያንስ የጋራ መርህን እና ሰታንዳርድ መከተል እንዲቻል የግድ መመካከርን የሚጠይቅ ይሆናል ። ይህ ምክክርም የሚፈጸመዉ በመንግስታት ግንኙነት አግባብ ስለሚሆን እነዚህ አንቀጾች ለመንግስታት ግንኙነቱ እንደ መነሻ መዕቀፍ መዉሰድ ይቻላል።

የህገመንግስቱ አንቀጽ 88/2 ላይ እንደተቀመጠዉ መንግስት የብሔሮችን፤ የብሔረሰቦችን፤ የህዝቦችን ማንነት የማክበር በዚህ ላይ በመመርኮዝ በመካከላቸዉ እኩልነት፤አንድነትና ወንድማመችነትን የማጠናከር ግዴታ እደለበት ያሳየል። በመሆኑም እንደ የኢትዩጵያ ፌደሬሽን ባለ በአሰፋፈር ፤በማንነት ፤በቋንቋ የተካለሉ ክልሎች ዉስጥ የሚኖሩ ብሔሮች፤ ብሔረሰቦች እና ህዝቦች በመካከላቸዉ እኩልነት፤አንድነትና ወንድማማችነትን ለማጠናከር ሰፊ የሆነ ባለ ብዙ ዘረፍ እና ቀጣይነት ያለዉ የመንግስታት ግንኙነት ሥርዓት ሊኖር የግድ ይላል በመሆኑም ይህ አንቀጽም ለመንግስታት ግንኙነት መኖር እንደ ህጋዊ መዕቀፍ ተደርጎ ሊታይ ይችላል።

በአንቀጽ 89 የኢኮኖሚክ ነክ ዓላማዎች ሥር የተደነገጉ ድንጋጌዎች በኢኮኖሚ ተጠቃሚ ለማድረግ ለሁሉም እኩል ዕድል የመፍጠር እና በእድገት ወደኋላ ለቀሩ ብሄሮች ፤ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች መንግስት ልዩ ደጋፍ እንዲያደርግ የሚያመላክቱ እና ሌሎች በአንቀጹ ስር ያሉ ድንጋጌዎች በአብዛኛዉ በአንድ የመንግስት አካል ብቻ መፈጸም ስለማይችሉ የመንግስታትን መደጋገፍና አብሮ መሰራትን የሚጠይቁ ናቸዉ በመሆኑም በአንቀጹ ሰር ያሉ ድንጋጊዎችን ለመተግበር የመንግስታት ግንኙነት መኖርን የግድ ይላል ሰለሆነም ይህን አንቀጽ ለመንግስታት ግንኙነት እንደመነሻ ማዕቀፍ አድረጎ መዉሰድ ይቻላል።

አንቀጽ 94 የፋይናንስ ወጭን በሚመለከት የተደነገጉት ድንጋጌዎች በዉክልና ለሚፈጸም ተግባር የወጭ አሸፋፈን፣ የፈደራል መንግሰት ለክልሎች የሚሰጠዉ የአስቸኳይ ጊዜ ዕርዳታ፣ የልማት ብድር እና ዕርዳታ እንዲሁም ደጎማ ጋር በተገናኘ ዕርዳታ አድራጊወና ዕርዳታ ተቀባዩ አበዳሪዉና ተበዳሪዉ፣ እንዲሁም ደጓሚዉ እና ተደጓሚዉ ሥለ ዕርዳታዉ፣ ድጓማዉ እና ብድሩ መጠን፣ ስለሚከናወኑ ተግባራት ስለ ተወሰደዉ ፋይናንስ አፈጻጸም ወዘተ.. እየተገናኙ መምከር የግድ ይላቸዎል። ይኽዉም ምክክር የመንግስታት ግንኙነትን መሰረት ያደረገ እንደሚሆን ይጠበቃል ስለሆነም ይህን አንቀጽም ለመንግስታ ግንኙነት ዕንደ መነሻ ሀጋዊ ማእቀፍ አድረጎ መዉሰድ ይቻላል።

በመንግስታት ግንኙነት ንደፈ ሃሳብ ብዙ የጋራ ስልጣን ያላቸዉ ፌደሬሽኖች ዘርፈ ብዙ እና ተቋማዊ የሆነ የመንግስታት ግንኙነት እንደሚኖራቸዉ ታሳቢ ያደርጋል በዚህ እሳቤ አንቀጽ 98, የጋራ የታክስና ግብር ስልጣን የመንግስታት ግንኙነት ህገመንግሰታዊ ማእቀፍ አድረጎ መዉሰድ ይቻላል።

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገመንግስት እንደ ደቡብ አፍሪካ፤ ሲዊዘርላንድ እና ህንድ በቀጥታ ሥለ መንግስታት ግንኙነት ያስቀመጠዉ ድንጋጌ ባይኖርም ከላይ በተዘረዘረዉ መልኩ ከህገመንግስቱ አጠቃላይ ይዘት እና ከተወሰኑ አንቀጾች ለግንኙነቱ መነሻ የሚሆኑ ድንጋጌዎችን ማየት ይቻላል። ሆኖም እንደኛ ባለ የባለብዙ ብሄር እና ታዳጊ ፌደሬሽን ያለ በትበብር ላይ የተመሰረተ የመንግስታት ግንኙነት ሕገመንገስቱ ወደ አስቀመጠዉ ግብ መድረስ እና በልማት የበለጸገ፣ በዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ የዳበር ህብረ ብሄራዊ ፌደራላዊ ስርዓት መገንባት አዳጋች ስለሚሆን የመንግስታት ግንኙነት ስርዓት በህግ በግልጽ መደንገግ እና የአሰራር ስርዓቱን ተቋማዊ ማድረግ ቁልፍ ፌደራላዊ ጉዳይ መሆኑ ሊሰመርበት ይገባል።

በኢትዮጵያ ፌደሬሽን ለመንግስታት ግንኙነት መነሻ ሊሆኑ የሚችሉ ሕገመንግስታዊ ማዕቀፎች በቀጥታ የተቀመጡም ባይሆንም ከዚህ በላይ በተገለጸዉ መሰረት ህገመንግስቱን በዝርዝር በማየት መዕቀፍ ሊሆኑ የሚችሉ ህገመንግስታዊ ግቦች እና አንቀጾች ያሉ መሆኑን ከተብራራ በኋላ ቀጣዩ ጉዳይ የፌደራል ስርዓቱ ህገመንግስታዊ ቅርጽ ይዞ መተግበር በተሞከረባቸዉ ሁለት አስርት ዓመታ የነበሩት የመንግስታት ግንኙነት ገጽታዎች እና አግባቦች በዝርዝር ማቅረብ ይሆናል።

3.3. የግንኙነቱ ገጽታዎች፣

3.3.1. ገጽታዎች የሚተነተኑባቸዉ ማዕቀፎች

አስካሁን በመንግሥታት ግንኙነት ዙሪያ ከተካሄዱ ጥናቶች በመነሳት የመንግሥታት ግንኙነቶች የሚካሄድባቸዉን ገጽታዎች እንደሚከተለዉ መከፋፈል ይቻላል፤ መደበኛና መደበኛ ያልሆኑ፤ተቋማዊ የሆኑ እና ጊዜያዊ በሆነ መልኩ የሚካሄዱ፤ የጎንዩሽና የተዋረድ አደረጃጀት ያለቸዉ ፤ ባለብዙ ዘርፍ እና የሁለትዩሽ የግንኙት ቅርጽ ያለቸዉ ሃገራዊ ወይም ከባቢያዊ የሆኑ ፤በአንድ ፖሊሲ ዘርፍ ወይም በአጠቃላይ ጉዳዩች ላይ የሚያተኩሩ እና የተለያዩ የግንኙነት ገጽታዎችን በማቀናጀት የሚካሄዱ የመንግስታት ግንኙነቶች ያሉ ቢሆንም በኢትዩጵያ ፌደሬሽን የመንግስታ ግንኙነት ገጽታዎች ለመተንተን ያመች ዘንድ እንደ መነሻ የሚከተለዉ ሞዴል ከቦሊያር (2009) ለኢትዩጵ ሁኔታ አመላካች ተደርጎ ተወስዶል

የግንኙነቱ ዳራ		ተሳታፊ አካላት
የጎንዩሽ ከባቢዊ	⟶	ሁለት እና ከዚየ በላይ የክልል መንግስታት ግን ሁሉንም ያላካተታ
የጎንዩሽ ባለበዙ ዘርፍ/ ሃገራዊ	⟶	ሁሉም የክልል መንግስታት ያካተተ
የተዋረድ ከባቢ	⟶ የፌደራል መንግስት እና	አንድ ወይም ከዚያ በላይ የክልል መንግስት ግን ሁሉንም የክለል መንግስታት ያለካተተ
የተዋረድ ባለብዙ ዘርፍ/ሀገራዊ	⟶	የፌደራል መንግስት እና ሁሉም የክልል መንግስታት

2.3.2 የተዋረድ ሴክተራል መድረኮች

ከግንኙነቶች ገጽታዎች አኳያ ሲታይ **በኢትዮጵያ ፌዴሬሽን በዋናነት በስፋት በመተግበር ላይ የሚገኘዉ የግንኙነት አይነት የፌደራል ሚኒሰቴር መ/ቤቶች ከአቻ የክልል ቢሮዎች ጋር የሚድርጉት የተዋረድ-ባለብዙ ዘርፍ/ሃገራዊ** የሴክተሮች መድረኮች ሲሆኑ ብዙዋቹ መድረኮች የዘርፋቸዉን ፖሊሲ መሰረት አድርገዉ የሚንቀሳቀሱ ፖሊሲ ተኮር ቢሆንም እና የተለያየ ይዘት ባላቸዉ ጉዳዩች ላይ ቢያተኩሩም የአሰራር ስርዕታቸዉ እና አካሄዳቸዉ ተመሳሳይ ነዉ።

በዚህ የግንኙነት ሂደት የአሰፈጻሚዉ አካል የጎላ ድርሻ ያለዉ ሲሆን የግንኙነቱ ዋና የትኩረት አቅጣጫ ስትራቴጅክ እና ዓመታዊ እቅዶችን የማናበብና ማቀናጀት፣ የሩብ ዓመት፣ የግማሽ ዓመት እና አመታዊ የአፈጻጸም ግምገማዎችን ማካሄድ፤ በጋራ ጉዳች ላይ ተመካክሮ የጋራ አቋም መያዝና ምርጥ ተሞክሮዎችን መለዋወጥ ነዉ። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እነዚህን ግንኙነቶች ተቋማዊ ለማድረግ የመግባቢያ ሠነድ መፈራረም እና የክልሎችን እኩል ተሳትፎ በተወሰነ መልኩ ለመጨመር መድረኮች በተለያዩ ክልሎች በማዘዋወር ለማካሄድ የሚደረገዉ ጥረት በአዉንታዊ መልኩ የሚታይ ነዉ።

በአስፈጻሚዉ አካል ከሚመሩት የሴክተር መድረኮች ባለፈ በህግ አዉጭዉና በህግ ተርጓሚዊ አካል ሃገራዊ መድረኮች የተቋቋመ ሲሆን የመድረኮቹ አላማ እና ቅርጽ ከሌሎች የሴክተር መደረኮች ተመሳሳይነት ያለዉ ቢሆንም የሌሎች ሴክተር መድረኮችን ያህል የተጠናከሩ ናቸዉ ብሎ መወሰድ አይቻልም። ሆኖም የፌደሬሽን ምክርቤት ካለዉ አደረጃጀት እና ተግባራ አኳያ ራሱን አስችሎ ከመንግስታት ግንኙነት አንጻር መዳሰስ ጠቃሚ በመሆኑ በሚቀጥለዉ ከፍል ተዳሶል

ከዚህ በተጨማሪ ሁሌ የሚከናወነዉ የግንኙነት ገጽታ በቀን ተቀን የሚከናወኑ ተግባራት ለማከናወን እና መረጃዎችን ለመለዋወጥ በርከት ያሉ ኢ-መደበኛ የሆኑ በደብዳቤ፣ በስልክ፣ በኢ-ሜል፣ በሚኖሩ ወርክሾፖች እና የተለያዩ ስብሰባዎች በአካል ግንኙነቶች የሚካሄዱ ሲሆን በፓርቲ መሥመር የሚደረግ ሠፊ ግንኙነቶች ዋናዉ ኢ-መደበኛ የሆነ የግንኙነት መስመር አድረጎ መዉሰድ ይቻላል።

3.3.2. የጎንዩሽ ከባቢዊ የመንግስታት ግንኙነት መድረኮች

ሁለተኛዉ የግንኙነት ገጽታ የጎንዩሽ- ከባቢያዊ ግንኙነት ሲሆን፣ ቀደመ ባሉ ጊዚያት በአንጻራዊ መልኩ ባደጉና በማደግ ላይ ባሉ ክልሎች መካከል የሚደረግ ግንኙነት ነዉ። ሁሉም የክልል መንግስታት የጎንዩሽ ከባቢያዊ ግንኙነት ያካሄዳሉ የግንኙነቱ ዋና መነሻ በገሃድ የሚታይ አንጻራዊ የአቅም ልዩነት ነዉ። በግንኙነቱ የሚተኮርባቸዉ ተግባራት፣ግጭቶችን መፍታት፣ ቴክኒካል

ድጋፍ ፣ የጋራ ልማት፣የአቅም ግንባታ ሥራዎች ፣ የሃሰቦችና የመረጃ ለዉዉጦች ናቸዉ። ከአዋጁ መወጣት በኃላ ይሕ ግንኙነት ከባቢያዊ በሆነ መልኩ ተጎራባች ክልሎችን መሰረት አድርጎ ማዋቀር እና በጋራ ጉዳዩቻቻዉ ላይ በጋራ እንዲሰሩ ሰፊ የምክክር መደኽረኮች የተካሄዱ ሲሆን መንሻ ሚሆኑ አደረጃጀቶች ተፈጥረዉ የምስራቅ ኢትዮጵያ፤ የደቡብ ኢትዮጵያ፤ በመሃከላዊ ኢትዮጵያ ተጎራባች ክልሎች የጋራ ተግባር መነሻ ሰነድ በማዘጋጀት ወደስራ የመግባት ጀምሮች አሉ።

በኢትዮጵያ ፌደሬሽን ሁሉንም ክልሎች የጋራ በሚደረጋቸዉ ጉዳይ ዙሪያ የጋራ የአፈጻጸም አቅጣጫ ለማያዝም ሆነ የጋራ የሆነ አቅጣጫዎችን በመያዝ በተባባረ ሃይል ከፌደረል መንግስቱ ጋራ ለመመካከር እና ለመደራደር፣ በራሳቸዉ የስልጣን ክልል ወሰን በሚፈጽሟቸዉ ተግባራት ዙሪያ ምርጥ ተሞክሮዎችን ለመለዋወጥ፣ ከባቢዊ እና ወሰን ተሻጋሪ የሆኑ ተግባራትን በትብብር ለመፈጸም፣ የጋራ ፕሮግራሞችንም ሆነ ፕሮጀክቶችን በማዘጋጀት በክልላቸዉ ወሰን ዙሪያ የሚኖሩ ማህበተሰቦች በጋራ የልማት ተጠቃሚነት እድል ማመቻቸት ወዘተ ላይ የሚመክሩበት ሃገራዊ የሆነ በአጠቃላይ ጉዳዩችም ሆነ ሴክቶራል በሆኑ ጉዳች ዙሪያ የሚንቀሳቀሱ የጎንዩሽ መድረኮች የሌሉ ሲሆን የመንግስታት ግንኙነት ያለ አዲስ አበባ የሚታወቅ አይደለም። ሆኖም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ከባቢዊ የጎንዩሽ ግንኙነት ፎረሞችን በኦሮሚያና በሶማሌያ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስታት መካከል፣ ኦሮሚያ፣ ቤንሻንጉል ጉምዝና ጋምቤላን መካከል፤ በአማራና ቤንሻንጉል ጉምዝ መካከል አቋቁሞ ወደ እንቅስቃሴ የመግባት በጎ ጅምሮች እየታዩ ያለ ሲሆን እነዚህ የጎንዩሽ ከባባያዊ መድረኮች የበለጠ ተጠናክረዉ ከባቢዊ ችግሮችን በመፍታት እና ከባቢዊ የመልማት እድሎችን በጋራ ለመጠቀም በሚያስችል መልኩ መደበኛ የሆነ አደረጃጀትና የአሰራር ስርዓት ዘርግተዉ ወደ እንቅስቃሴ እንዲገቡ ለማድረግ ሚያስችል ተከታታይ ተግባራት ሊከናወኑ ይገባል። ከዚህም አኳያ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ የመንግስታት ግንኙነት ስርዓት ለመወሰን የወጣዉ አዋጅ ቁጥር 1231/2013 ወደ ስራ ከገባ ወዲህ አዋጁን መሰረት አድረጎ የጎንዩሽ ከባቢዊ ግኙኑነቶችን ለማቋቋምና የአሉትን ለማጠናከር በፌደሬሽን ም/ቤት አነሳሽነት የየክልሎቹ ከፍተኛ አመራሮች የተሳተፉበት የምዕራብ እና ስሜን ኢትዮጵያ ተጎራባች ክልሎች እና የደቡብ እና ምስራቅ ኢትዮጵያ ተጎራቦች ክልሎች የምክክር መድረክ ተካሂደዉ በሁሉም መድረኮች ስለመድረኮች አስፈላጊነት ላይ የጋራ መግባባት ተፈጥሮ በቀጣይ በተለያዩ የአደረጃጀት አግባቦች ወደስራ ለመግባትና የነበሩትን ፎረሞች ለማጠናከር ከየክልሉ ለተዉጣጡ ቴክኒካል ኮሚቴዎች ሥልጠና ተሰጥቶ ወደ ስራ ለመግባት እየተደረገ ያለዉን ጥረት ተጠቃሽ ነዉ።

በኢትዮጵያ የፌደራል ስርዓቱ ተጠናክሮ ለመቀጠል፣ የተረጋጋ እና የማህበረሰቡን የተለያዩ ችግሮች እየፈታ የሚሄድ፤ ብዝሃነትን አስተዳደርን ይበልጥ እያዳበሩ ለመሄድ ለማስቻል የመንግስታት ግንኙነቶቹ መደበኛ በሆነ አግባብ ህጋዊ ማዕቀፍ ኖሯቸዉ ማንኛዉም ፓርቲ በየትኛዉም ደረጃ ወደ ስልጣን ቢመጣ መንግስታት እንደ መንግስት እየተገናኙ የሚሰሩበት ስርዓትን መፍጠር የሃገራችን የልማት እና የዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ ቀጣይነት ለማረጋገጥ ቀልፍ ጉዳይ ተደርጎ ሊወሰድ ይገባል። ይህን የበለጠ የሚያደረገዉ ደግሞ በሃገራቱን የፖለቲካ –እንቅስቃሴ ውስጥ ብዙዋቹ ፓርቲዎች ከባቢያዊ እና በማንነት ላይ የተመሰቱ ስለሆነ እና የፌደሬሽኑ አባል ክልሎችም በዋናነት ፤ ማንነት፣ ቋንቋን እና አሰፋፋርን መሰረት አድረጎ የተዋቀሩ መሆን ነዉ። በዚህ ፖለቲካዊ ነባራዊ ሁኔታ ጠንካራ እና መደበኛ የሆነ የተለያዩ ገጽታዎች ያሉት የመንግስታት ግንኙነት መኖር ለጠንካራ እና አካታች ሀገረመንግስት ግንባታ ወሳኝ ጉዳይ ነው።

3.4 የግንኙነቱ አግባቦች

የመንግስታት ግንኙነት ተዋናኞች አንዱም ሆነ ሌለ የግንኙነት አግባብ ተጠቅመዉ ግንኙነት መፍጠራቸዉ አይቀሬ ነው። ምክንቱም በግንኙነቱ አንዱ ከአንዱ የራሱን ግብ ለማሳካት አስፈላጊ ሆነ የሚያገኘዉ ነገር ለምሳሌ ያህል የፋይናንስ ድጋፍ፣ ቴክሊካል ድጋፍ የአቅም ግንባታ ድጋፍ፣ የህግ ማዕቀፍ፣ ፖሊሲና ስትራቴጅን የመፈጸም ድጋፍ፣ ኢንፎርሜሽን ወዘተ.. በመኖሩ ነው። ከዚህም ሌለ የመንግስታት ግንኙነቶችን የፖለቲካ መድረኮች በመሆናቸዉ ጭምር የፖለቲካ ተዋናኞች የራሳቸዉ የተገደበ ምክንያታዊ የሆነ ፍለጎታቸዉን –ለማሟለት ዉስብስብ ወደ ሆነ ግንኙነት የሚገቡበት ሂደት ያለ ሲሆን የመንግስታት ግንኙነቱ –የፌደራል ስርዓቱ ዉስጥ ያሉ ተቋማዊ ሁኔታዎች እና የግንኙነቱ ተዋናኞች ያላቸዉን ፍለጎት ለማሳከት በሚያሳድሩት ተጽእኖ ጫና ዉስጥ ሁኖ የሚፈጸም እና ተዋናኞቹ በተቋማቱ ሁኔታ ላይ የራሰቸዉን ጫና እየፈጡ እንዲሁም ተ———ቋማቱ በተዋናኞቹ ላይ ጫና እየፈጠሩ የሚቀጥል ይሆናል።

በኢትዮጵያ ፌደሬሽን የሚታየዉ የመንግስታት ግንኙነት አግባቦች ከዚህ አጠቃላይ መነሻ ሁኔታዎች የተለየ መነሻ የለዉም። በኢትዮጵያ ፌደሬሽን የነበሩት የመንግስታት ግንኙነት አግባቦች በዋናነት በአዉራ ፓርቲ ስርዓት ማእቀፍ የሚተገበሩ ከመሆኑ ጋራ ተያይዞ በኢህአዴግ አባል ድርጅቶች እና አጋራ ድርጅቶች መካካል የነበረዉ ግንኙነት ግልባጭ ሆኖ ይገኛል።

ከዚህ ጋር ተያይዞ ዋና ዋና ሀገራዊ የፖሊሲ እና ስትራቴጅ ጉዳዩች በፓርቲ ደረጃ ስለሚያልቁ እና መንግስታዊ ቅርጽ ስለሚይዙ ከዚያ በኋላ የተዋረድ የሴክተሮች የመንግስታት ግንኙነት መድረኮች ሴክቶራል ትከረታቸዉ የተለያየ ቢሆንም የመድረኮች አካሄድ እና የሚወያዩባቸዉ ጉዳዩች ተመሳሳይነት ያለዉ እና በዋናነት የሚያተኩሩት በስትራቴጅክ እና አመታዊ ዕቅድ ዝግጅት እና አፈጻጸም፣ በተሞክሮ ልዉዉጥ፣ መረጃ ልዉዉጥ፣ የተለያዩ ሃገራዊ ፕሮግራሞች አፈጻጸም በመሆኑ እነዚህን ጉዳዩች በጋራ ማየት የሁሉም ፍላጎት በመሆኑ መድረኮቹ በንድፈ ሃሳብ ደረጃ አንድ የመንግስታት ግንኙነት መድረክ ማሟላት ያለበትን ባህሪ መድረኩን ራሱን ከመፍጠር ጀምሮ አጠቃላይ ሂደቱ ላይ በእኩልነት እና አጋርነት ላይ የተመሰረተን ተሳትፎ ያረጋገጡ ባይሆኑም በሚቀርቡ አጀንዳዋች ዉይይት እና የጋራ ማድረግ ሂደት የትብብር መንፈስ የሚታይባቸዉ ናቸዉ ብሎ ማጠቃለል ይቻላል፡፡ ይህንም ጉዳይ የጥናቱ ተሳታፊ የሆነ እና ጉዳዩ የሚመለከተዉ ከፍተኛ ሙያተኛ ከትምህርት ሚኒሰቴር (ቃለመጠየቅ ፣ አዲስ አባበ ፣ ሰኔ /2006) በሚከተለዉ መልክ ገልጸታል፡

በፌደራል ትምህርት ሚኒሰቴር እና በክልል ትምህርት ቢሮዎች መካከል ያለዉ ትብብር መነሻዉ የሚሊንየሙን የልማት ግብ (በወቅቱ አልጠተናቀቀም ነበር) እና የትምህርት ዘርፍ የልማት ፕሮግራም ለማሳካት የጋራ የሆነ አመለካከት መኖር ሲሆን እነዚህ ግቦች እና ፕሮግራሞች የሁሉም ግብዓት በተካተተበት መልኩ በጋራ የተዘጋጅ ናቸዉ፡፡ የጋራ ግብና ፕሮግራሞች መኖር እና እነዚህን በቅንጅት መፈጸም ደግሞ የትብብሩ መኖር ዋና መነሻ ነዉ፡፡

ሌሎችም እንደ የጤና፤ ግብርና፤ የፋይናንስ ሴክተሮች እና የመሳሰሉት የሴክተሮች የመንግስታት ግንኙነቶች ፎረሞች የግንኙነት አግባቦች የሚገለጹባቸዉ መንገዶች ሴክተሮችን መሰረት ያደረጉ ግቦች እና ፕሮግራሞች ላይ መሰረት በማድረግ በትብብር ላይ የተመሰረቱ ግንኙተነቶች የሚለዉ የግንኙነት አግባቦች ናቸዉ፡፡

በአንጻራዊ የተሻለ አቅም ባላቸዉ (በተለምዶ ያደጉ) በሚባሉት እና በአንጻራዊ የአቅም ክፍትት ባላቸዉ (በተለምዶ በማደግ ላይ ያሉ) በሚባሉት ተጎራባች ክልሎች ማለትም በአማራና አፋር ብሄራዊ ክልላዊ መንግስቶች፤ በትግራይ እና በአፋር ብሄራዊ ክልላዊ መንግስቶች፤ በአማራ እና ቤንሻንጉል ጉምዝ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስቶች፤ በኦሮሚያ እና በሱማሌ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስቶች፤ በደቡብ ብሄር ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች እና በጋምቤላ ብሄራዊ ክልላዊ

መንግስት ሲካሄዱ የነበሩ ከባቢያዊ የመንግስታት ግንኙነት መድረኮች ተቋማዊነታቸዉ እና ቀጣይነት ባለዉ መልኩ መካሄዳቸዉ ጋራ ተያይዘ ያለባቸዉ ዉስንነት እዳለ ሆኖ መነሻቸዉም በትብብር ከባቢዊ ችግችን መፍታት እና መደጋገፍ የሚሉ ግንኙነቶቹ በመሆናቸዉ የሚካሄደዉ ግንኙነት በትብብር ላይ የተመሰረተ ነዉ፡፡ የትብብሩም መገለጫም ግንኙነቱ በዋናነት የሚያተኩርውት በተለያዩ መስኮች የአቅም ግንባታ ድጋፍ ላይ ነዉ፡፡ ሆኖም በፌደራል መንግስት ለነዚህ ክልሎች በልዩ የድጋፍ ቦርድ አመካኝነት የሚፈረጉ ግኝኙነቶች በጫና ላይ የተመሰረቱ እና የክልሎችን በሕገመንግስት በተሰጣቸዉ ስልጣን ዙሪ በራስ የመወሰን መብታቸዉን የገደበ እንደነበር ይገለጻል፡፡

ስትራቴጅክም ሆነ አመታዊ እቅዶች ለመፈጸም እንዲሁም የአቅም ግንባታ ድጋፍ ለማድረግ የሚደረጉ መንግስታዊ ግንኙነቶች በሴክቶራል የመንግስታት ግንኙነቶች በሚኖሩ አጀንዳዎች አቀራረብ፣ በመድረኮች ዝግጅት እና አመራር ወዘተ.. የሚኒስቴር መ/ቤቶቹ የበለጠ ተሰሚነት ያላቸዉ ከመሆን በዘለለ አጠቃላይ ሂደቱ በትብብር ላይ የተመሰረተ ነበር ብሎ ማስቀመጥ ይቻላል፡፡ ግንኙነቱ በዋናነት በትብብር ላይ የተመሠረተ የሆነበት ምክንያቶችም የጋራ ዓላማን ለማሳካት በትብብር ላይ የተመሰረተ የጋራ ተግባር የሚል መነሻ በመኖሩ እና መንግሥት ሲከተለዉ የነበረዉ የልማት አቅጣጫ የመንግስትን በኢኮኖሚዉ ዉስጥ በተመረጠ አኳኋን ጣልቃ ገብነት የሚጠይቅ መሆን በትብብር ላይ የተመሠረተ ቅንጅት አሰፈላጊ በመሆኑ የስርዓቱ ባህሪ ትብብርን የግድ የሚል ነዉ።

ክፍል 4. የፌደሬሽን ም/ቤት እንደ አንድ የመንግስታት ግንኙነት መድረክ

ከመንግስታት ግንኙነት አኳያ በኢትዮጵያ ፌደሬሽን የኢፌዲሪ ፌደሬሽን ምክርቤትን አደረጃጀት፤ ተግባር እና ሃላፊነት እና አሰራር መዳሰስ በፌደሬሽኖች የላይኛዉ ምክርቤቶች ይኖራቸዋ ተብሎ ከሚጠበቀዉ ሚና እና በተለያዬ ፌደሬሽኖች የላይኛዉ ምክርቤቶች ከመንግስታት ግንኙነት አኳያ ከሚጫወቱት የተለያየ ሚና አኳያ ማየት ጠቃሚ ነዉ።

የፌደሬሽን ምክርቤት በኢ.ፌ.ደ.ሪ ህገመንግስት አንቀጽ 61/1 መሰረት በፌደራሉ መንግስት አባል ክልሎች የሚገኙት ብሄሮች፤ብሄረሰቦች ህዝቦች የሚልኳቸዉ አባለት የሚወከሉበት ም/ቤት ሲሆን ስለአመራረጣቸዉም በአንቀጽ 61/3 አባላቱ በክልል ምክርቤቶች እንደሚመረጡ በማስቀመጥ ክልል ምክር ቤቶች በራሳቸዉ ወይም በቀጥታ በህዝብ እንዲመረጡ በማድረግ የፌደሬሽን ምክርቤት አባል እንዲወከል እንደሚደርጉ አስቀምጧል። ስለሆነም የምክርቤቱ አባላት በክልል ምክርቤቶች

በራሳቸዉ ወይም በህዝብ እንዲመረጡ በማድረግ የሚላኩ ናቸዉ። ሆኖም እሰካሁን ያለዉ የፌደሬሽን ምክርቤቱ አባላት ምርጫ አካሄድ እንደሚያሳየዉ አባላቱ ክልል ምክርቤቶች በራሳቸዉ የተመረጡ እና በዋናነት የየክልሎች ከፍተኛ ኃላፊዎች ናቸዉ።

እንግዲህ የምክርቤቱ አባላት የብሄር፣ ብሄረሰቦች እና ህዝቦች ተወካዩች ቢሆኑም በተግባር ያለዉ የዉክልና አፈጻጸም ሲታይ የክልል መንግስታትንም የሚወክሉበት አንድምታ እንዳለዉ መወሰድ ይቻላል። ይህም ጉዳይ አንድ የፌደሬሽን ምክርቤት አባል ጋር በተደረገ ቃለ ምልልስ (አዲስ አበባ/ ሰኔ 2006) እደሚከተለዉ ገልጾታል፡

በተግባራዊ እንቅስቃሴያችን እኛ የብሄር፤ብሄረሰቦች እና ህዝቦች እና የክልል መንግስታት ተወካዩች እንደሆን ነዉ የሚሰማን ምክንያቱም የብሄር፤ብሄረሰቦች እና ህዝቦች ተወካይ አርጎ የላከን አካልም ኃላፊነት እንዳለብን ነዉ የሚሰማን። የብሄር፤ብሄረሰቦች እና ህዝቦች ተወካይ በመሆን እና የክልል መንግስትን መወከል መካከል ምንም አይነት የፍላጎቶች መቃረን የለም። የብሄር፤ብሄረሰቦች እና ህዝቦች ፍላጎት እና የክልሎች ፍላጎት አብረዉ የሚሄዱ ናቸዉ። በክልሎች ምክርቤት ብሄር፤ብሄረሰቦች እና ህዝቦችን እንድትወክል ተልከህ እና የክልሎች ምክርቤት እና /ወይንም ስራ አስፈጻሚ ሁነህ ሁለቱን መወከል ችግር አይደለም

ይህ ቃለ ምልልስ ቆየት ያለ ቢሆንም አሁንም ያለዉን ነባራዊ ሁኔታ ይገልጻል ተብሎ ይታሰባል። አንዳንድ አባላቱ የክልል መንግስታት ብቻ ሳይሆን የፓርቲያቸዉን ፍላጎትም በዋናነት መሰርት አድረገዉ የሚንቀሳቀሱ መሆኑ በቅርቡ ኢህአዲግ ከፈረሰ እና የብልግና እና የህዉሃት የምክርቤት አባል ሁነዉ በቀጠሉበት ወቅት ከምርጫ ማራዘም ጋር ተያይዞ ህገመንግስታዊ ትርጉም የመስጠት አጀንዳ ለምክርቤቱ በቀረበበት ወቅት በግልጽ የታየ ነዉ።

በመሆኑም ከላይ በተዘረዘረዉ አባሉቱ የሚልኮቸዉ አካላት እና የሚመረጡበትን አግባብ ከመንግስታት ግንኙነት ንድፈ ሃሳብ አኳያ ሲቃኝ ምንም እንኳ እንደ ጀርመኑ ቡንደስ ራት እና እንድ ደቡብ አፍሪካዉ ናሽናል ካዉንስል ኦፍ ፕሮቪንስስ በቀጥታ በጀርመን የሌንደርስ እና በደቡብ አፍሪካ የፕሮቪንሶችን ፍላጎት እንዲወክሉ የተላኩና ዉሳኔያቸዉም የመጡባቸዉን ላንድ እና ፕሮቪንስ ምክርቤቶች ፍላጎቶች በቀጥታ የሚወክል ባይሆንም የፌደሬሽን ምክርቤት ካለዉ የአባለት ዉክልና አኳያ መንግስታት ግንኙነት መድረክ ሆኖ ሊገለግልበት የሚችልበት አግባብ ያለ መሆኑን ማስቀመጥ ይቻላል።

የአባለቱ አመራረጥ እና ዉክልና ከመንግስታት ግንኙነት አኳያ ይህ ከሆነ ም/ቤቱ በህገመንግስቱ የተሰጡት ሃላፊነት እና ተግባራት ባህሪያት የመንግስታት ግንኙነትን የሚጠይቁ መሆናቸዉን እና አለመሆናቸዉን ማየቱ ምክርቤቱን ከመንግስታት ግንኙነት አኳያ በተገቢዉ ለማዳሰስ ጠቃሚ ይሆናል።

ምክርቤቱ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገመንግስት የተሰጡት ሃላፊነት እና ተግባራት በአንቀጽ 62/1 እስከ 11 የተቀመጡ ሲሆን የመንግስታት ግንኙነትን የግድ የሚሉት ተግባራት እና ሃላፊነቶች እንደሚከተለዉ አንቀጽ በአንቀጽ ቀርበዋል፦

ለምክርቤቱ በአንቀጽ 62/1 የተሰጠዉ ስልጣን ሕገ መንግሥቱን የመተርጎም ሥልጣን ሲሆን ለሕገ መንግስት ትርጉም የሚቀርበዉ ጉዳይ የፌደራል እና የክልል መንግስታት የህገመንግስታዊ የስልጣን ክፍፍል እና ከአፈጻጸም ጋር ተያይዞ የሚነሳ አንዱ አከል የአወጣዉ ህግ, ፖሊሲ ወዘተ.. የሌላዉን ህገመንግስታዊ ስልጣን ተጋፋቢኝ የሚል እና የህገመንግስት ትረጉም የሚያስፈልገዉ ጥያቄ ከቀረበ ጥያቄዉ ሁለት መንግስታትን እና የእነርሱን ግንኙነት ላይ ተጽእኖ የሚፈጥር በመሆኑ የመንግስታት ግንኙነት ላይ የራሱ እንድምታ ስለሚኖረዉ ይህ እና ተመሳሳይ ጥቄዎች ላይ የህገመንግስት ትርጉም የመስጠት ስልጣን የፌደሬሽን ምክርቤትን የመንግስታት ግንኙነት ላይ የራሱ ሚና እንዲጫዎት የሚደርገዉ ሲሆን በትርጉም አሰጣጥ ሂደቱ የተለያዩ የክልል መንግስታት ፍላጎቶች የሚንጸባረቅበት እና የተለያዩ ፍላጎቶች ወይይት የሚደረግባቸዉ እና በምክክር እና በድርድር ወሳኔ ላይ የሚደረስበትን መድረክ መፍጠር ስለሚችል የፌደሬሽን ምክርቤት ከዚህ አንቀጽ አኳያ የመንግስታት ግንኙነት መድረክ ሆኖ ማገልገል የሚችልበት አግባብ እንዳለ ማየት ይቻላል።

በአንቀጽ 62/3 ሌላዉ ለምክርቤቱ የተሰጠ ስልጣን የብሔሮች፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች የራስን ዕድል በራስ የመወሰን እስከ መገንጠል መብትን በተመለከተ በሚነሱ ጥያቄዎች ላይ በሕገ መንግሥቱ መሠረት መወሰን ሲሆን ይህን ስልጣን ተግባራዊ በመሆን ሂደት ምክርቤቱ ጥያቄዉን ካነሱት ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች እና ከሚገኙበት ክልላዊ መንግስት ጋር አብሮ መስራት የሚጠይቀዉ እና ይህም የመንግስታት ግንኙነት ገጽታ ሊኖረዉ የሚችል ሲሆን በምክርቤቱ መድረክ ዉሳኔዉን ከማየት ጋር ተያይዞ የክልልሎች እና ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች የሁሉም ፍላጎቶች ቀርበዉ ወይይት የሚደረግበት እና በምክክር እና በደርደር በሁሉም ተቀባይነት ያለዉ ዉሳኔ ላይ የሚደረስበት መድረክ መፍጠር ስለሚቻል ምክርቤቱ በክልል መንግስታት መካከል የመንግስታት ግንኙነት የሚሳለጥበት መድረክ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል።

በአንቀጽ 62/4 ለም/ቤቱ የተሰጠዉ ተግባር በሕገ መንግሥቱ የተደነገገው የሕዝቦች እኩልነትና በሕዝቦች መፈቃቀድ ሊይ የተመሰረተ አንድነት ስር እንዲሰድና እንዲዳብር ማደረግ ሲሆን ክልሎች በየክልሎቻቸዉ የሚኖሩ ህዝቦች በመፈቃቀድ ላይ የተመሰረተ ክልላዊም ሆነ ሃገራዊ አንድነት ለመፍጠር የሚመክሩበት እና ወደተግባራዊ እንቅስቃሴ የሚገቡበት የመንግስታት ግንኙነት መድረክ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል።

ሌላዉ በአንቀጽ 62/6 ለምክርቤቱ የተሰጠዉ ተግባር በክልሎች መካከል ለሚነሱ አለመግባባቶች መፍትሄ ማፈላለግ ሲሆን ምክርቤቱ የመፍትሄ ማፈላለጉን ሂደት አለመግባባቱ ከተፈጠረባቸዉ ክልሎች ጋር በመሆን ካልሆነ ክልሎችን ሳይዝ የሚያከናወነዉ ተግባር ዉጤታማ ይሆናል ተብሎ ስለማይታሰብ ከክልሎች ጋር የሚያደርገዉ ግንኙነት እና የሚያከናዉነዉ ተግባር የመንግስታት ግንኙነት ገጽታ እንደሚኖረዉ ካለማጠያየቁም በላይ እንደ ምክርቤት መፍትሄ ለማፈላለግ በሚደረጉ ዉይይቶች አለመግባባቱ የተከሰተባቸዉ ክልሎች ፍላጎት ወደ መድረክ ቀርቦ አለመግባባቱ በወይይት፣በምክክር እና በድርድር የሚፈታበትን እና የብዙ ተዋናኞች ፍላጎት ለማጣጣም የሚቻልበትን ሁሉም አሸናፊ የሚሆኑበትን መንገድ ማፈላለግ የግድ ስለሚል እና ዋና ተዋኞችም የክልል መንግስታት ስለሚሆኑ ምክርቤቱ መንግስታት ግንኙነት መድረክ ሆኖ እንዲያገለግል የግድ ይለዋል።

በአንቀጽ 62/7 የተሰጠዉ ሌላዉ ስልጣን የክልሎችና የፌደራል መንግሥት የጋራ ተብለው የተመደቡ ገቢዎች በሁለቱ መካከል የሚከፋፈልበትን፣ እንዲሁም የፌዳራል መንግሥት ለክልልች ድጎማ የሚሰጥበትን ቀመር መወሰን ሲሆን እነዚህ ከሃብት ጋር የተያያዙ ጉዳዩች ከፍተኛ የሆነ የክልሎችን ፍላጎት የሚስቡ ከመሆናቸዉ ጋር ተያይዞ ከጥናት ስራዎች ጀምሮ እስከ ወሳኔ አስጣጥ ድረስ የክልሎችን ተሳትፎ የሚጠይቅ ከመሆኑም በላይ ዉሳኔዎች ላይ ለመድረስ በአባላቱ መካከል **ውይይት ማካሄድን፣ መመካከርን፤ የጋራ መግባባት እና የክልልሎችን የተለያዩ ፍላጎቶች ማቻቻልን የሚጠይቁ ሰፊ የመንግስታት ግንኙነት ገጽታዎች ያለቸዉ ተግባራት የሚከናወንበት በመሆኑ ምክርቤቱ የመንግስታት ግንኙነት መድረክ ሆኖ ሊገለግል ይችላል።**

በመጨረሻም በአንቀጽ 62/ 9 የተሰጠዉ ስልጣን ማንኛውም ክልል ይህን ሕገ መንግሥት በመጣስ ሕገ መንግስታዊ ሥርዓቱን አደጋ ላይ የጣለ እንደሆነ የፌደራል መንግሥት ጣልቃ እንዲገባ ያዛል። ይህ ስልጣን ከክልሎች የዉሰጥ ራስን በራስ የማስተዳደር ልዕላዊነት ጋር ስለሚያያዝ ሕገመንግስቱ መጣሱን እና ህገመንግስታዊ ስርዓቱ አደጋ ላይ መዉደቁን ለማረጋገጥ እና የፌደራል

መንግስት ጣልቃ እንዲገባ ለማዘዝ ህገመንግስቱ እንደተጣሰ እና ህገመንግስታዊ ስርዓቱ በእርግጥ አደጋ ላይ እንደወደቀ ለመወሰን ሰፊ የመንግስታት ግንኙነት ተግባራትን ማከናወን የግድ የሚል ሲሆን ይህም ተረጋግጦ ዉሳኔ ሲወሰን የሌሎችን ክልሎች ይሁንታ ማግኘት ክልሎች በፌደሬሽኑ ከፌደራል ጣልቃገብነት ጋር በተያያዘ የሚወሰኑ ዉሳኔዎች የነሱን ልዕላዊነት ለመጋፋት ሳይሆን በእርግጥ ሕገመንግስታዊ ስርዓቱን በማስከበር የእነርሱን ራስ በራስ የማስተዳደር ስልጣን በህገመንግስቱ ማዕቀፍ አጠናክሮ ማስቀጠል መሆኑ ላይ መግባባት መፍጠር ለፌደሬሽኑ ቀጣይነት እና የተረጋጋ መሆን ወሳኝ ከመሆኑም በላይ በሁሉም ድጋፍ ያለዉ ዉሳኔ ላይ ለመድረስ የሚያስችል በመሆኑ ሰፊ የመንግስታት ግንኙነት ተግባራት የሚገለጽበት ተግባር መሆኑ አይቀርም። ስለሆነም ምክርቤቱ የመንግስታት ግንኙነት መድረክ ሆኖ እንዲንቀሳቀስ የሚያደረግ ሃላፊነት መሆኑን መረዳት ይቻላል።

የፌደሬሽን ምክርቤት ከአባለቱ አመራረጥ እና ጥንቅር እንዲሁም ከተሰጡት ተግባር እና ሃላፊነቶች አኳያ ሲዳሰስ ምንም እንኳ የፌደራል ተቋም ቢሆንም የመንግስታት ግንኙነት መድረክ ሆኖ የሚያገለግል መድረክ አድረጎ መዉሰድ ይቻላል። በተለይም ክልሎች ከፌደራል መንግስት ጋር በሚኖራዊቸዉ የገቢ ክፍፍ ዙሪያ የሚመክሩበት እና የጋራ ሀሳብ የሚይዙበት እና ዉሳኔ ላይ የሚደርሱበት፣ በፌደራል መንግስት ለሚሰጣቸዉ ድጎማ የሁላቸዉን ፍላጎቶች እና አቅሞች መሰረት ያደረገ የደጎማ በጀት ቀመር እንዲዘጋጅ የሚመካከሩበት እና ዉሳኔ ላይ የሚደርሱበት፤ በመካከላቸዉ የሚፈጠሩ ለመግባባቶች ወደ ግጭት ሳያድጉ የፌደራል ስርዓቱን በሚያጠናክር እና የቀጣይ አብሮነታቸዉን በማይንድ መልኩ የሚፈቱበትን መንገድ የሚመክሩበት እና ዉሳኔ የሚሰጡበት፣ ሃገራዊ አንድነት እና **የብሄሮች ብሄረሰቦች ህዝቦች አብሮነትና የጋራ ተጠቃሚነት ለማጎልበት የሚያስችሉ** መሰረታዊ አቅጣጫዎችን የሚመክሩበት እና ወደተግባረዊ እንቅስቃሴ ለመግባት የጋራ መግባባት የሚፈጥሩበት **የመንግስታት ግንኙነት መድረክ ሆኖ ሊ.ያገለግል የሚችል ተቋም ነዉ።**

ከዚህ አኳያ የፌደሬሽን ምክርቤት እስካሁን ባከናወናቸዉ ተግባራት በርግጥም የመንግስታት ግንኙነት መድረክ ሆኖ እየተንቀሳቀሰ ነዉ የሚለዉን ጥያቄ ለመመለስ ዝርዝር የምክርቤቱን እንቅስቃሴዎች ምክርቤቱ የኢ..ፌ.ዴ.ሪ ህገመንግስትን መሰረት አድረጎ ወደ ስራ ከገባበት ጊዜ ጀምሮ መዳሰስ በቀጣይ ሰፊ ጥናት የሚጠይቅ መሆኑን አመላክቶ ማለፍ የግድ ይላል። ሆኖም ከኢህአዴግ የአዉራ ፓርቲ ስርዓት ጋር ተያይዘ ምክርቤቱ የመንግስታት ግንኙነቱ ገጽታዉ ሳይሆን የፓርቲ ግንኙነት ገጽታዉ የጎላ መሆኑን ማስቀመጥ ይቻላል። ም/ቤቱ ከሃገራዊ ለዉጡ በኋላ

በህገመንግስቱ የተሠጡትን ተግባርና ኃለፊነቶች ለመወጣት ህገመንግስታዊ ስርዓቱን ለማስከበር ከወሰዳቸዉ ዉሳኔዎች፤ የጋራ ገቢ የሚከፋፈልበትን ቀመር በማሻሻል የክልሎች ተጠቃሚነት መሻሻል ጋር ተያይዞ፣ በፌደራል መንግስት በየክልሎቹ የሚተገበሩ መሰረተ ልማት ፍታዊነት ለማረጋገጥ የተጀመሩ የስርጭቱን ፍታዊነት የሚወስኑ የአሰራር ስርዓቶችን ለማሰቀመጥ የተጀመሩ ስራዎች፣ የፌደሬሽን ም/ቤት ራስን የበለጠ አጠናክሮ ኃለፊነቱን ለመወጣት የጀመራቸዉ የሪፎርም ስራዎች፣ በህገመንግስቱና በፌደራላዊ ስርዓቱ ላይ ያለዉን አጠቃላይ የግንዛቤ ክፍተት በመሙላት ንቃተ-ህገመንግስቱ እና ፌደራላዊ አስተሳሰቡ ያደገ ማህበረሰብ ለመፍጠር ይህኑ ተግባር የሚከናዉን ራሱን የቻለ ለም/ቤቱ ተጠሪ የሆነ ማዕከል እንዲቋቋም የተገበራቸዉ ተግባራት ም/ቤቱ የመንግስታት ግንኙነት ስራንዉን የበለጠ አጠናክሮ እንዲሄድ የሚያስችሉ ስራዎች ከመሆናቸዉም በላይ የመንግስታት ግንኙነት ስርዓቱን ለመወሰን የወጣዉ አዋጅ ቁጥር 231/2013 እንዲጸድቅ ከዝግጅት ጀምሮ አዋጁ እንዲወጣ ሰፊ ጥረት በማድረግ አዋጁ ከወጣ በኋላም አዋጁን በማስተዋወቅና የተለያዩ የግንኙነት መድረኮች እንዲፈጠሩ ሰፊ ተግባር በማከናወን ላይ ይገኛል፡፡ የመንግስታት ግንኙነት ስርዓት ለመወሰን የወጣዉ አዋጅ ቁጥር 231/213 መሰረት አድረጎ እንዲቋቋሙ በአንቀጽ 6 ስር ከተዘረዘሩት መድኮች አንዱ ም/ቤቱ የሚሰበሰበዉ እና የክልል ም/ቤቶች አፈጉባዔዎች፤ የክልል ርዕሰ መስተዳደሮች እና የተመረጡ ፌደራል አስፈጻሚ አካላት ያቀፈ የግኝኙነት መድረክ እንዲመሰረት የሚደነግግ ሲሆን መድረኩም በዋና ዋና ሀገራዊ የሆኑና ክልሎችንና የፌደራል መንግስቱን እና ክልሎችን እርስበዕርስ የሚያገናኙ ጉዳዩች የሚታዩበት የግንኙት መድረክ ስለሆነ የም/ቤቱን የመንግስታት ግኝንኙት ማዕከል ሆኖ መቀጠል ሚናዉን ይበልጥ ያጠናክረዋል፡፡

ክፍል 5. በኢ.ፌ.ዴ.ሪ የመንግስታት ግንኙነት ለመወሰን የወጣ አዋጅ

በአለፉት ክፍሎች በሰፋት እንዳየነዉ በኢትዩጵያ ፌደሬሽን የመንግስታት ግንኙነት አንዱና ዋነኛዉ ተግዳሮት የመንግስታት ግንኙነቱ የሚመራበት የህግ ማቀፍ የሌለ መሆንና የግንኙነቱ ተቋማዊነት ደረጃ ደካማ መሆን ከዚህ ጋር ተያይዞ የግንኙነቱ ኢ-መደበኛ ገጽታዉ የጎላ መሆን በፌደሬሽኑ ለሚፈጠሩ ችግሮች ምላሽ ከመስጠትና ፌደሬሽኑ በየጊዜዉ ከሚፈጠሩሃገራዊ፤ አሃጉራዊና ዓለማዊ ሁኔታዎች ጋር ራሱን እያዋሃደ እንዲሄድ ከማስቻል አኳያ

የመንግስታት ግንኙነቱ ያደረገዉ አስተዋጽኦ ዝቅተኛ መሆን ነዉ፡፡ ከላይ በዝርዝር እንደቀረበው ምንም እንኳ ሃገሪቱ የምትከተለው የፌደሬሽን ቅርጽ ያለዉ የፌደራል ስርዓት መሰረት አድረጎ ህገመንግስታዊ ዋስትና እና ህገመንግስታዊ የስልጣን ክፍፍል ያላቸዉ ፤በህዝብ በቀጥታ ለስልጣን የሚበቁና ተጠያቂ የሆኑ እንዲሁም በቀጥታ ህዝብን በተለያየ አግባብ የሚያገለግሉ ሁለት መንግስታትን መመስረቱ የመንግስታት ግንኙነት የግድ የሚሆንበት ሁኔታን የፈጠረና በህገመንግስቱ ዉስጥ በቀጥታም ባይሆን ለመንግስታት ግንኙነት መነሻ ሊሆኑ የሚችሉ አንቀጾችን የያዘ ቢሆንም የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገመንግስት በቀጥታ የመንግስታት ግንኙነት የሚመለከቱ ድንጋጌዎች ያለካተተ በመሆኑ ግንኙነቱ የሚመራበት የህግ ማዕቀፍ የሌለ በመሆኑ ግንኙነቶቹን ተቋማዊ ከመሆን ጋር ተያይዞ የራሱ የሆነ አሉታዊ አስተዋጽኦ ሲያደርግ ቆይቷል፡፡

በመሆኑም ይህን የህግ ክፍተት ለመሞላትና የመንግስታት ግንኙነት ስርዓት የሚወሰን አዋጅ እዲወጣ ጽንሰ ሃሳቡም ሆነ የመንግስታት ግንኙነቶችን የአሰራር ስርዓት የሚወሰን ህገ አወጣጥ ሂደቱም አዲስ በመሆኑ ሰፊ ጥናት፤ የተሞክሮዎች ልዉዉጥ እና የምክክር መድረኮች ከተካሄዱ በኋላ የተለያዩ ሂደቶችን አልፎ ከብዙ መጓተት በኋላ ጥር 3/2013 በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የመንግሥታት ግንኙነት ሥርዓት መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 1231/2013 ሊወጣ ችሏል፡፡

ይህ አዋጅ መደበኛ የሆነዉን የመንግስታት ግንኙነቶች ሥርዓት የሚወሰን በመሆኑና ከአዋጅ መወጣት ጋር ተያይዞ በኢትዮጵያ ፌደሬሽን የመንግስታት ግንኙነቶች ከፍ ወዳለና በታወቀ የአሰራ ስርዓት የሚመራበትና አጠቃላይ ሃገራዊ መንግስታዊ አፈጻጸምን የሚያሻሽሉበት፤ የሚፈጠሩ አለመግባባቶችን የሚፈቱበት፤ ከፌደራል ስርዓቱ የሚጠበቁ ሚዛናዊ የሆኑ አካሄዶች የሚጎለበቱበት እና የፌደራል ስርዓቱ የተረጋጋ ዉጤታማ የሚሆንበትን ሁኔታፈ ይጥራል ተብሎ ይጠበቃል፡፡ በመሆኑም የአዋጁን አጠቃላይ ይዘት በአጭሩ በዚህ ጽሁፍ መዳሰስ አዋጁ ወደ ተግባር የገባ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ በፈጻሚ አካላትም ሆነ በአጠቃላይ ማህበረሰቡ አዋጅን ከመፈጸምና የአዋጁን አፈጻጸምና የተገኙ ዉጤቶችን ከመከታታልና አዋጁ ዉጤታማ በሆኑ መልኩ እንዲተገበር ከማስቻል አኳያ ትልቅ ድረሻ ይኖረዎል በሚል ታሳቢ እንደሚከተለዉ ቀርቧል

በኢ.ፌ.ዴ.ሪ የመንግስታት ግንኙነት ሰርዓትን ለመወሰንየወጣዉ አዋጅ ቁጥር 1231/2013 **ስድስት ክፍሎች እና** 34 **አንቀጾችን ያካተተ ሲሆን የአዋጁ አስፈላጊነት እና ዓለማ እደሚከተለዉ በመግቢዉ ተቀምጧል**

ሀገራችን ኢትዮጵያ ፌደራላዊና ዲሞክራሲያዊ የመንግስት አደረጃጀት ሥርዓትን የምትከተል እንደመሆኗ መጠን ዘላቂ ሰላምን ለማስፈን፣ ዋስትና ያለው ዲሞክራሲን ለማረጋገጥ፣ ፈጣን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ልማትን ለማስቀጠልና አንድ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ማህበረሰብን ለመገንባት ይቻል ዘንድ ከተናጠል ጥረቶች ይልቅ የየእርከኑን አካላት አቅሞች በተገቢው መንገድ አቀናጅቶና አዋህዶ ዘርፈ-ብዙ የልማትም ሆነ የመልካም አስተዳደር ተግባራትን ለማከናወን የሚያስችሉ መደበኛ የመንግስታት ግንኙነቶችን በግልፅ መደንገግ አስፈላጊ —ሆኖ በመገኘቱ፣ በስራ ላይ ባለው ፌደራላዊ የመንግስት አደረጃጀት ውስጥ የፌደራልም ሆነ የክልል መንግስታት የተናጠልና የወል ሥልጣንና ኃላፊነቶች በህገ-መንግስቱ ተለይተው የተቀመጡ ቢሆንም የየእርከኑ መንግስታት በወል ከተሰጣቸው ኃላፊነት ባሻገር በተናጠል በየተመደቡላቸው ሥልጣንና ተግባራት ተቀራርቦና እርስ በርስ ተናቦ መስራትና ተገቢ ሆኖ ሲገኝ የጋራ ፖሊሲዎችን ስትራቴጂዎችን ነድፎ በዉጤታማነት ለመንቀሳቀስ የሚያግዝ ትብብራዊ የግንኙነት ማዕቀፍ እንደሚያስፈልጋቸው በመታመኑ፣ በፌደራላዊ ሥርዓተ-መንግስት ውስጥ በመንግስታት መካከል የሚካሄዱ የእርስ በርስ ምክክሮችና፣ የሚደረጉ የትብብር ስምምነቶች ከስርዓቱ ባህርይ የሚመነጩ እንደ መሆናቸው መጠን ለሥርዓቱ ዘለቄታ ተፈላጊ የሆኑ የጋራ አስተሳሰቦችን በመያዝና በማጠናከር ሥርዓቱ በየጊዜው እየጎለበተ የሚሄድበትን አሰራር መዘርጋት በማስፈለጉ፤ በፌደራልና በክልል መንግስታት፣ እንዲሁም በራሳቸው በክልሎች መካከል እርስ በርስ ሲካሄዱ በቆዩ ግንኙነቶች እስከ አሁን የታዩትን ጥንካሬዎች ለማስቀጠልና ያጋጠሙ ወይም ወደፊት ሊያጋጥሙ የሚችሉ ክፍተቶችን ለመሙላት፣ ፌደራላዊ ስርዓቱንም ሆነ የሀገሪቱን ዲሞክራሲያዊ አንድነት ለማጠናከር ብሎም በየእርከኑ መንግስታትና አቻ ተቋማቱ መካከል በመርህ ላይ የተመሰረተ ጠንካራ የትብብር ሥርዓት መፍጠር ለፌደራላዊ ሥርዓቱ ጤናማነትና ቀጣይነት ጉልህ ድርሻ ያለው በመሆኑ እያንዳንዱ መንግስት የተሰጠውን ሥልጣንና ኃላፊነት ለመወጣት የራሱን ዕቅድ በሚነድፍበትና በሚፈጽምበት ጊዜ በተናጠል ከመስራቱ የተነሳ የወጪ መደራረብና የጊዜ ብክነት እንዳይደርስና ከተገልጋዮች ፍላጎት መለዋወጥና ማደግ ጋር በተያያዘም የአገልግሎት አሰጣጥ ስታንዳርዶችን በጋራ በመንደፍና አዳዲስ አሰራሮችን በመዘርጋት እንዲሁም በክልሎች መካከል የልምድ ልውውጦችን በማካሄድ በመካከላቸው የሚታየውን ወጣ-ገባነትና የጥራት ልዩነቶችን ማጥበብና ተቀራራቢ አፈፃፀም እንዲኖር ማድረግ ተገቢ ሆኖ በመገኘቱ፤

በሚል የዓዋጁን አስፈላጊነትነ ዓለማ በዝርዝር ከላይ በተቀመተዉ መልኩ ያስቀመጠ ሲሆን የግንኙነቱ አይቀሬነትና ግንኙነቱን ትብበርራዊ በሆነ መልኩ በሚታወቅ የአስራር ስርዓት መምራት እንዲቻል የወጣ አዋጅ መሆኑን አዋጁ በአግባቡ ተግባራዊመ ከሆነ የሚጠበቁ ዉጤቶችንም አመላክቷል፤፤

በአዋጁ የተደነገገዉ ሌላዉ መሠረታዊ ጉዳይ በአዋጁ ከፍል አራት የተደነገገዉ ግንኙነቶቹ የሚመሩባቸዉ መርሆዎች ሲሆኑ የሚከተሉት 7 መርሆዎች በጥብቅ መከተል እዳለባቸዉ ተደንግጓል፡-

1. የሕገ-መንግሥትን የበላይነት ማክበር፤

2. እኩልነትና የእርስበርስ መከባበር፤

3. ምክክርና ድርድር፤

4. ሀገራዊ ራዕዮችንና እሴቶችን ማጎልበት፣

5. ግልፅነትና ተጠያቂነት፤

6. አሳታፊነትና ውጤታማነት፤

7 ትብብርና የጋራ መግባባት፤

የአዋጁ የተፈታሚነት ወሰን ሁለንም ዓይነት በፌደራል መንግስትና በክልል መንግስታት እንዲሁም በክልል መንግስታት መካከል የሚደረጉ መደበኛ ግኙኑነቶችን የሚያካትት ሲሆን የሚከተሉትን ስድስት የግንኙነት መድረኮች በመዘርዘር የየመድረኮችን

አባላትን፤ የየመድረኮችን ተግባርና ኃላፊነትን፤ መድረኮች የሚከተሉትን የአሰራር ስርዓት፤ መድረኮቹን የሚያስተባብሩ አካላትን አደረጃጀትና ተግባርና ኃላፊነት በዝርዝር ደንግጓል። መድረኮችም

1. ሀገር-አቀፉ የሕግ አውጭዎች ግንኙነት መድረክ፣
2. ሀገር--አቀፉ የሕግ አስፈጻሚዎች ግንኙነት መድረክ፣
3 ሀገር-አቀፉ የህግ ተርጓሚዎች ግንኙነት መድረክ፣
4. ሀገር-አቀፉ የአስፈፃሚዎች ዘርፋዊ ግንኙነት መድረክ፣
5. የፌደሬሽን ምክር ቤትና የክልሎች ግንኙነት መድረክና፣
6. የክልል መንግሥታት የግንኙነት መድረኮች።

በአዋጁ የተዘረዘሩት መድረኮች ከአሁን በፊት የነበሩትን አዋጁን መሰረት አድረጎ በማጠናከር ሎሎች መድረኮችን እንደ ጉዳዩቹ አስፈላጊነት በማቋቋም መድኮቹ የሚመሩበትን ዝርዝር ደንቦችና መመሪያዎችና ጋይድላይኖች በማዘጋጀትና በየደረጃዉ በማጸደቅ ወደስራ በማስገባት መድረኮቹ በርግጥም የማህበረሰቡን ችግሮች የሚፈቱና ማህበረሰቡን ተጠቃሚ የሚደረጉና የትብብር፤ የምክክር፤ የመተማመን ባህልን በማጎለበት በፌደራሊዝም ፍልስፍና የተመሰረተ የሃገረ መንግስትና ህብረ ብሄራዊ ፌደራላዊ ስረዓት ግንባታና ከዚያ ጋር ተያይዞ በኢኮኖሚ የዳበረች፤ ዘላቂና አስተማማኝ ሰላም ያላትን፤ የዲሞክራሲ ስረዓት የዳበረባት ሁሉም የኔ የሚላት ኢትዮጲያን እያጠናከሩ ለመሄድ የመንግስታት ግኙኑነት ስርዓት ማዳበርና በአግባቡና በየጊዜዉ ከሚኖሩ ለዉጦች ጋር እያደገ በሚሄድ መልኩ መተግበር ተገቢ ነዉ፣

ክፍል 8፡- ፌደራላዊ አመራር ለብዝሃነት አስተዳደር እና ለመንግስታት ግንኙነት መዳበር

8.1. መግቢያ

ስለ የፌደራል አመራር ምንነት እና ባህሪያት ትንታኔ ከመግባታችን በፊት አመራር የሚለዉን ጽንሰ ሃሳብ እንደ አጠቃላይ ለዚህ ጽሁፍ መነሻ በሚሆን መልክ መዳሰስ ተገቢ ነዉ። አመራር ለሚለዉ ጽንሰ ሃሳብ የተለያዩ ትርጉሞች የተሰጡት ሲሆን

ሁሉም የተሰጡት ትርጉሞች በመሰረታዊነት አመራር ሂደት መሆኑን ሂደቱ ደግሞ በሰዎች እና በቡድኖች ላይ ተጽእኖ መፍጠር እና የተቀመጠ ግብን ለማሳካት ተከታይ ማፍራት ጋር ይያያዛል።

ለአንድ ሃገር ዘላቂ ሰላም፣ ልማት እና ዋስትና ያለዉ የዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ የሀገሪቱ አመራሩ ቁልፍ ሚና እንደሚጫወት በአመራር ሳይንስ እዉቅና የተሰጠዉ ድምዳሜ ነዉ። ይህ ድምዳሜ ትክክለኛ መሆኑም በተግባር በሃገራት መካከል ያለዉ የሰላም፤ የልማት እና የዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ ሰፊ ልዩነት ሌሎች ታሳቢዎች እንዳሉ ሆኖ በዋናናት በሃገራቱ በየጊዜዉ ከሚፈጠረዉ አመራር ልዩነት ጋር ተያይዞ የሚታይ መሆኑን ያሳያል። አመራር ሲባል በተለያዩ ደረጃዎች እና አግባቦች የተለያዩ የማህበረሰብን ከፍሎችን የሚመለከት ሲሆን በዋናነት የፖለቲካ አመራሩን፤ የአካዳሚክ አመራሩን ፤የሃገር ሽማግሌዎች እና የሃይማኖት አመራሮችን፤ ሲቪል ሰርቪስ አመራሩን፣ የኢኮኖሚ አመራሩን፤ የወታደራዊ አመራሩን ፤ የዘመኑ መገለጫ እየሆነ የመጣዉን ተጽእኖ ፈጣሪዎችን ወዘተ...የሚያጠቃልል ነዉ። እያንዳንዱ ከላይ የተዘረዘረዉ የአመራር ክፍል እንደ አመራር በህብረተሰቡ ዉስጥ የሚኖረዉ ሚና የተለያየ ነዉ። አመራር በዋናናት ማህበረሰብን ለአንድ አላማ እና ርዕይ ለማንቀሳቀስ አቅጣጫ የማሳየት እና ተጽእኖ በማሳደር ግብን ለማሳካት የሚከዉበትን ሂደት የሚያጠቃልል ነዉ። አመራር ከላይ የተገለጸዉን የሚመስል ሲሆን ዉጤታማ አመራር ባህሪያት ደግሞ ሊደረስበት የሚችል ርዕይ እና ይህን በአብዛኛዉ ማህበረሰብ የጋራ ማድረግ መቻል፤ታማኝነት፤ ዉጤታማ ተግባቦት፣ ርህራሄ እና ችግርን የመቋቋም እና የማለፍ ችሎታን የሚያካትት ነዉ። ሁሉም አመራራ የሚጋራቸዉ ከላይ የተዘረዘሩትን ጨምሮ ተቀራራቢ ባህሪያት ያሉ ቢሆንም የተለያዩ የአመራር አይነቶች መኖራችዉ ይታወቃል ። እነዚህም ዴሞክራቲክ፤ በተጽእኖ ላይ የተመሰረተ፤ ዉስን ተጽእኖ የሚፈጥር፤ ትራንዛክሽናል፤ ትርንሰፎርሜትቪ፤ አገልጋይ ወዘተ... እየተባሉ በአመራር ጥናት ጽሁፎች ዉስጥ በሰፋት እና በዝርዝር ይገለጻሉ። ሆኖም የዚህ ሰነድ ዋና ዓላማዉ የተለያዩ የአመራር አይነቶችን በጥልቀት –መተንተን ሳይሆን የፌደራል ስርዓት በትክክለኛዉ መንገድ ተግባራዊ ለማድረግ በህብረ በሄራዊ ፌደራል ስርዓት ብዝሃነትን ለማስተዳደር እና ውጤታማ እና ችግር ፈች የሆነ የመንግስታት ግንኙነት እየዳበረ እንዲሄድ ፌደራላዊ አመራር ወሳኝ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የፌደራላዊ አመራር ምንነትን፤ አስፈላጊነት እና ባህሪያት መተንተን እና በዚህ ዙሪያ ተቀራራቢ አረዳድ መፍጠር ነዉ።..

8.2. ፌደራላዊ አመራር

አመራር የሚለዉ ጽንሰ ሃሳብ ባህሪያት እና አይነቶች እንደተበቀ ሆኖ ፌዴራላዊ አመራር ማለት የፌዴራል ስርዓትን ለመምራት (ከሰነዱ ርዕሰ ጉዳይ ጋር በተያያዘ መልኩ ሲታይ (ብዝሃነት ለማስተዳደር እና የመንግስታት ግንኙነትን በማጠናከር) ተፈላጊ የሆኑ እዉቀት፣ ክህሎት እና አመለካከት የተላበሰ አመራር ማለት ነዉ። ተፈላጊ የሆነዉ እዉቀት፤ ክህሎት እና አመለካከት በአንዴ መላበስ ይቻላል ተብሎ ስለማይታሰብ በሂደት ይህን እያዳበረ ለመሄድ ጥረት የሚያደረግ እና ባለዉ አቅም ልክ ፌዴራላዊ እወቀቱን፣ክህሎቱን እና አመለካከቱን በተግባር የሚገለጽ በዚህም ለፌዴራል ስርዓቱ ዉጤታማነት የአመራር ሚናዉን በተገቢዉ የሚወጣ ነዉ።

ፌዴራላዊ አመራር ሊላበሳቸዉ ከሚገቡ ባህሪያት የመጀመሪያዉ እና ዋናዉ የፌዴራል ስርዓቱ አስፈላጊነት እና ጠቀሜታ ላይ ሙሉ እምነት ያለዉ መሆን፣ ስርዓቱን ለመተግበር መሰረት የሆኑ የህግ ማዕቀፎችን በሚገባ ጠንቅቆ ማወቅ፤ ሰርዓቱ ዉስብስብ በመሆኑ በየጊዜዉ እያደገ የሚሄድ ፌደራላዊ አስተሳሰብ የሚጠይቅ መሆኑን በመረዳት፤ የስርዓቱን መሰረታዊ እሳቤዎች ለመላበስ ቀጣይነት ያለዉ ጥረት ማድረግ። በሁሉም ፌዴፈሬሽኖች በተለይም ህብረ በሄራዊ በሆኑ ፌደሬሽኖች ሁሌም ሁለት እኩል ተፈላጊ የሆኑ ግን ተቃራኒ የሚመስሉ የብዝሃነት መገለጫ የሆኑ ጉዳዮችን ይዞ መቀጠል የሚጠይቅ በመሆኑ በየጊዜዉ ሚዛን ጠብቆ መሄድን የሚጠይቅ መሆኑን በመረዳት የመንግስታት ግንኙነትን እንደ አንድ ሚዛን የመጠበቂያ እና ብዝሃነትን ጋር ይያያዘዉ የሚፈጠሩ ተግዳሮቶችን መፍቻ መሳሪያ አድርጎ የመጠበቅ አመለካከትን እና ክህሎትን ማሳደግ ይጠይቃል።የፌደራሊዝም አጥኝዎች ፌደሬሽኖች ተቃራኒ የሚመስሉና ሁለቱም ተፈላጊ የሆኑ ጉዳዮችን የያዙ በመሆኑ የተቃርንዩሽ ትብብር በማለት ይገልጻቸዎል (ዱካኪስ,1977) እንደ መገለጫም ለምሳሌ ያህል ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ማየት ይቻላል

- ✓ ብዝሃነት እና አንድነት
- ✓ የራስ አስተዳደር እና የጋራ አስተዳዳር
- ✓ የተማከለ እና ያልተማከለ
- ✓ ትስስር እና ራስን መቻል
- ✓ ሃገር አቀፍ/አጠቃላይ እና ክልላዊ መንግስት

- ✓ ሃገራዊ የመልማት ፍላጎት እና-ክልላዊ ፍላጎት እና ምርጫ
- ✓ የግል መብት እና የቡድን መብት
- ✓ ሃገራዊ (በሄራዊ) ማንነት እና ከባቢዊ (የብሄር) ማንነት ወዘተ...

እነዚህን የሚቃረኑ የሚመስሉ ሆኖም ተፈላጊ የሆኑ ጉዳዮች በአንድ ፌደራላዊ አደረጃጀት አቀናጅቶ የሚኬድበት አግባብ ከባድ በመሆኑ እና የተለያዩ አካላትም ከስርአቱ አተገባበር የተለያየ የሚጠብቁት ጉዳይ ስለሚኖር በሚታወቅ እና ተገማች በሆነ የመንግስታት ግንኙነት ስርዓት በቀጣይነት በሚደረጉ ዉይይቶች እና በመተባበር ላይ በተመሰረተ ግንኙቶች ጉዳዩቹን እያጣጣሙና ሚዛናቸዉን እየጠበቁ መሄድ እንደኛ ባሉ በብዝሃነት ላይ ለተመሰረቱ ፌደሬሽኖች ቁልፍ ጉዳይ ነዉ።

የፌደራል አመራር ከህብረተሰብ የሚገኝ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ብዝሃነት መገለጫቸዉ በሆኑ ማህበረሰቦች በግለሰብ ደረጃ አመራሩ የወጣበት አንድ ከባቢ(ብሄር) መኖሩ አይቀሬ ነዉ በመሆኑም ፌደራል አመራር ከአንድ አካባቢ (ብሄር) የተገኘ ቢሆንም ሀገርን የመምራት (ብሄራዊ) እሳቤን ምንግዜም መላበስ እና በሚገኝበት ሁኔታ እና ደረጃ ሁሉ ከዚህ መሰረት ላይ የቆመ መሆን ያስፈልገዎል ምክንቱም የፌደራል ስርዓት ዋናዉ ግብ ብዝሃነትን ያቀፈ አንድነት ነዉ።

ፌደራላዊ አመራር ከላይ ከተዘረዘሩት በተጨማሪ ፌደራላዊ አስተሳሰብ መላበስ ለፌደራላዊ አመራር ወሳን ባህሪ ነዉ። የፌደራል ስርዓትን ለመገንባት ፌደራላዊ ተቋማት፣ የአሰራር ስርዓት እና እነዚህን ወደ ተግባር የሚያስገቡ ተዋንያን አስፈላጊ የመሆናቸዉን ያህል በስርዓቱ ዉስጥ ከሚፈጠር እና በየጊዜዉ ዕያደገ ከሚሄድ ፌደራላዊ አስተሳሰብ ወጭ የተረጋጋ፣ ቀጣይነት ያለዉ ሁሉም የኔነዉ የሚለዉ ስርዓት መገንባት አዳጋች ነዉ። በመሆኑም በዚህ አጭር ጽሁፍ ዉስጥ በእንግሊዘኛ ቃንቃ federal spirit ለሚለዉ ጽንሰ ሃሳብ ፌደራላዊ አስተሳሰብ የሚል ተቀራራቢ የሆነ ትርጉም በመስጠት በጽንሰ ሃሳቡ ምንንት እና ለፌደራለዊ አመራር ወሳን አስተሳሰብ መሆኑ ተመላክቷል ። ፌደራላዊ አስተሳሰብ የሚለዉን ባጭሩ ለማብራራት በፌደራላዊ ፖለቲካ መስክ የሚኖር እይታ ሲሆን እይታዉም የፌደራል ስርዓት ለማዋቀርም ሆነ ከተዋቀረ በኋላ ስርዓቱን ለማስቀጠል በአቻዎች መካከል የሚደረግ ቀጣይነት ያለዉ ዉይይትን፤ ድርድርን መሰረት ያደረገ ፍቃደኝነት እና ስምምነት የሚገለጽበት ፖለቲካዊ እይታ በሁለም ተይዞ የሚቀጥልበትን ሁኔታ መፍጠር ማለት ነዉ። ይህን መሰል አመለካከት ለፌደራላዊ አሴቶች እና መርሆዎች ጥብቅ ተገዥነትን የሚጠይቅ ሲሆን ከፌደረላዊ መርሆዎች መካከል ለፌደራል ስርዓቱ ታማኝነት እና

ፌደራል ኮሚቲ (በፌደራል ስርዓቱ ከሁሉም አካል የሚጠበቅን በሁለም ተቀባይነት ያለዉ አካሄድን መከተል)፣ በስርዓቱ የተካተቱ ሌሎች አካላት ችግሮችን እንደራስ አድረጎ በማየት ዋጋ ለመክፈል ዝግጁነትን በዋናነት መጥቀስ ይቻላል። ለፌደራል ስርዓቱ ታማኝነት ሲባል የፌደራል ስርዓቱ አባል መንግስታት እና የእነርሱ ተወካዮች አጠቃላይ ለሆነዉ ሀገራዊ የፌደራል ስርዓቱ ያላቸዉ ታማኝነት የሚገለጽበት ሲሆን ይህም የጋራ ጉዳያችን ብለዉ ለለዩቸዉ ጉዳዮች ማለትም ለምሳሌ ሀገራዊ ልማት፤ሀገራዊ አንድነት፤ ሀገራዊ ነጻነት እና ልዕላዊነት፤ ሀገራዊ ደህንነት፤ የዜጎች መሰረታዊ መብቶች እና ነጻነቶች– ተግባረዊነት እና ለመሳሰሉት ታማኝነት የሚገለጽበት ነዉ።

ፌደራላዊ ሥርዓት ዉስብስብና የህብረተሰቡን ሆነ የአመራሩን በየጊዜዉ እያደገ የሚሄድ ፌደራላዊ አሰተሳሰብ የሚጠይቅ መሆኑ በተለያዩ የፌደራሊዝም ተመረማሪዎች ትኩረት የተሰጠበት ጉዳይ ነዉ። ለምሳሌ ዳንኤል ኤላዛር (1987) የተባለ የፊደራሊዝም ምሁር ፌደራሊዝምን "የአሰተዳደር ሴሚናር“ በሚል ይገልፀዋል። ይህም በየጊዜዉ ተፈላጊ የሆኑ ተከታታይ ወይይቶችን በማድረግ ከዚያ የሚነሳ አዳጊ ሃሳቦችን እና አመለካከቶችን በመያዝ አሰተዳደሩን እየተገበሩ መሄድን የሚጠይቅ እንደሆነ ለማመላከት ነዉ። ይህ ጉዳይ በተለይም በብዝሃነት ላይ የተመሠረተ የፌደራላዊ ሥርዓት በሚከተሉ ሃገራት መፈጸም ከሚፈለጉት ተቃራኒ ከሚመስሉ ግን ተመጋገቢ እና እኩል ተፈላጊ ከሆኑ ከላይ በምሳሌነት የተገለጸ ተግባራት ሁሌም ሚዛን ጠብቆ መፈጸምን ይጠይቃል። በሃገራችን ይህን ሁኔታ ስንመለከት ግን ከህገ-መንግስቱ ጀምሮ የተለያዩ ተቋማትን ከማደራጀት በዘለለ በፌደራሊዝም ጽንሰ ሃሳብ፣ የተለያዩ ፌደራላዊ አደረጃጀቶች ይዘትና ባህሪ፤ የፌደራላዊ ሥርዓት አሰራር ሄደቶች፤ በመንግሥታት መካከል ስለሚኖሩ የግንኙነት አግባቦች፤ ለፌደራል ሥርዓት መጎልበት እና ቀጣይነት ተፈላጊ በሆኑ ፌደራላዊ አሰተሳሰቦችና አሴቶች ዙሪያ ሰፊ የግንዛቤ ክፈተት መኖሩ እና ይህን የግንዛቤ ክፍተት በጥናት እና ምርምር በተደገፈ መልኩ ለመፍታት የሚያስችል አቅም ለመገንባት በሃገሪቱ የከፍተኛ የትምህርት ሥርዓት ዉስጥ ለዘርፉ የተሰጠዉ ትኩረት አናሳ መሆን በፌደራል ሥርዓቱ አተገባበር ዙሪያ ከሚታዩ ተግዳሮቶች ጋር ተያይዞ ለሚፈጠሩ የተሳሳቱ አመለካከቶች የራሱን አሰተዋጽኦ አድረጓል።

መገለጫዎቹም የሁሉም ብሄር ፤ብሄረሰቦች ራስን በራስ የማስተዳደ ዕድል በህገመንግስት ደረጃ የተረጋገጠ እና ተግባራዊ መደረግ የተጀመረ ቢሆንም ብዝሃነትን በብቃት ለማስተናገድ የሚያስችለውን የዴሞክራሲያዊ እና ፌደራላዊ አሰተሳሰብ በሚፈለገው ደረጃ ስላልተያዘና ስላልተሰፋፋ የተመዘገቡት ውጤቶች እንዳሉ ሆኖ በቀላሉ በወይይት እና በንግግር ልንሻገራቸዉ ይገቡ የነበሩ ተግዳሮቶች ኃይል ወደ ቀላቀለ ግጭት መልክ መከሰታቸዉ አልቀረም። በመሆኑም ለህብረ-ብሄራ ፌደራላዊ

ስርዓታችን በተገቢዉ መንገድ በሚፈለገዉ ደረጃ ለመተግበር አንዱ ተግዳሮት ለስርዓቱ መሰረት የሆነዉ ፌደራላዊ አስተሳሰብ በተገቢዉ ደረጃ ያልዳበረ መሆኑ ነዉ። ይህን ችግር በመገንዘብ የለዉጡ መንግስት የህገመንግስትና ፌደራሊዝም እስምህሮ ማእከል በአዋጅ ቁጥር 1123/2011 እንዲቋቋም በማድረግ ሰፊ የአስተምግሮ ስራዎች እየተሰሩ ቢገኙም ማዕከሉን የበለጠ በማጠናከር የአስተምህሮዉን ተደራሽነት እና ስርጸት ይበልጥ ማጠናከር ይጠይቃል።

ሌላዉ ተፈላጊ የሆነ የፌደራል አመራር ባህሪ ብዝሃና ተመጋጋቢ ማንነትን ማዳበር ነዉ። እንደ ኢትዮጵያ ላሉ መገለጫቸዉ እና ስሪታቸዉ ብዝሃነትን ላቀፉ ማህበረሰቦች በጋራ ለመቀጠል ፣ ጠንከራ እና አካታች የሆነ ሀገረመንግስትን በመገንባት ዘላቂ በሆነ ዴሞክራሲዊ ስርዓት፤ ዘላቂ የሆነ ሰላም እና አስተማማኝ የሆነ ብልጽግና ዉስጥ ለመቀጠል ህብረ በሄራዊ ፌደራላዊ ስርዓት የተሻለ አማራጭ ተደርጎ ይወሰዳል ። ህብረ በሄራዊ ፌደራላዊ ስርዓትን በትክክለኛ አቅጣጫ ለመተግበር ስርዓቱ ዴሞክራሲያዊ መሆንን፤ ብዝሃና ተመጋጋቢ ማንነት መጎልበትን ይጠይቃል። ምክንያቱም ብዝሃነትን ለማስተናገድ ዴሞክራሲያዊ አስተዳደር እና ዴሞክራሚዊ የሆነ ግንኙነት አስፈላጊ ከመሆኑም በላይ ህብረ-ብሄራዊ ፌደራላዊ ስርዓት ብዝሃነትን ከሀገራዊ አንድነት ጋር ተመጋጋቢ አድረጎ ለማስኬድ አንዱ መንገድ ብዝሃ እና ተመጋጋቢ የሆኑ ማንነቶች እያበለጸጉ መሄድ መሆኑን የሌሎች ህብረ ብሄራዊ የሆኑ ፌደሬሽኖች ተሞክሮ ያሳያል። ይህ ጉዳይ በኢትዮጵያ ፌደሬሽን ያለበትን ሁኔታ በየጊዜዉ በጥናት እየዳሰሱ መሄድ እና ከጥናቱ ዉጤቶች ተነስቶ ህብረ ብሄራዊ አንድነትን የሚያጠናክሩ ስራዎችን መስራት የግድ የሚል ነዉ። ብዝሃና ተመጋጋቢ ማንነትን እንደ አንድ የፌደራላዊ አመራር ባህሪ ከመተንተኑ በፊት ማንነት ስለሚለዉ ጽንሰ ሃሳብ የተወሰኑ መንደርደሪዎችን ማቅረብ ተገቢ በመሆኑ ማንነት በዚህ ጽሁፍ በሚከተለዉ መልኩ የሚታይ ነዉ።

ማንነት ሰዎች እራሳቸዉን የሚያዩበት እና እራሳቸዉን እንዲህ ነኝ ብለዉ የሚገልጹበት መንገድ ነዉ። ሰዎች የተለያዩ የማንነት መሰረቶች ያሏቸዉ ሲሆን የግል እና የቡድን (ማህበራዊ) ማንነነቶች ይኖራቸዋል። ማህበራዊ ማንነቶች የአንድ ቡድን አባል መሆንን መሰረት ያደረጉ እና ሚናን መሰረት ያደረጉ ሊሆኑ ይችላሉ። ሚናን መሰረት ያደረጉ ማንቶች ሰዋች በማህበረሰቡ ዉስጥ ያላቸዉን ሚና የሚገለጽበት ነዉ።ማህበራዊ ማንነት ግለሰቡ የዚህ ቡድን አባል ነኝ ከሚል እዉቀት እና ራሱን የቡድኑ አባል አድረጎ ከመወሰድ ጋር የሚገናኝ ነዉ ። የአንድ ማህበራዊ ቡድን የጋራ የሆነ ራሳቸዉን የሚለዩበት ማህበራዊ መገለጫ ያላቸዉ እና አለን ብለዉ የሚያስቡ ግለሰቦች ስብስብ ነዉ። የማህበራዊ ማንነት መገለጫም በአበላቱ መካከል ተቀራራቢ የሆነ አይታዎች እና ተግባሮች መኖር ያካትታሉ። ብዙዋች

የማህበራዊ ማንነት ንድፈሃሳቦች በቡድኖች መካከል ያለ ግንኙነት ላይ ያተኩራሉ ሰዋች እንዴት ነዉ ራሳቸዉን የአንድ ቡድን አባል መሆናቸዉን እና የሌላ ቡድን አበል የሆኑት የሌላ ቡድን መሆናቸዉን የሚያዩት የሚለዉን ለመዳሰስስ ይሞክራሉ።።

ሆኖም ማህበራዊ ማንነቶች ፍጹማዊ የሆነ ገጽታ ያላቸዉ ሳይሆን አንጻራዊ በሆነ አግባብ የሚታዩ ናቸዉ ብዝሀነት እና ተመጋገቢነት ገጽታ እንዳላቸዉ ይወሰዳል።። ይህ ከሆነ በሃገራዊ (ብሄራዊ) ማንነት እና ከባቢያዊ (የብሄርን) ማንነት መካከል የሚቃረን ነገር እንደሌለ አድረጎ መወሰድ ይቻላል።።በማንነቶች መካከል የዜሮ ድምር ዳይናሚክስ መኖሩን የሚያሳይ ማስረጃ የሌለ መሆኑን እንዳንድ ጥናቶ ያመለክታሉ።። አንዱ ማንነት ሲጠናከር ሌለዉ የሚዳከም አይሆንም።። በተቃራኒዉ የሰዉ ልጆች ብዝሃነት ያለዉ አንደ ወፍ ጎጆ የተጠለለፉ ማንነቶ ተመጋጋቢ አድረገዉ መያዝ ይችላሉ (Anderson,2013)።።

ከዚህ ጋር ተያይዞ ሚለር (2001) የተባለ የዘርፉ ተመራማሪ የስፔንን ሁኔታ መሰረት አድርጎ ገለጭ በሆነ መለኩ እንደሚከተዉ አስቀምጦል፣-

> "*ሰዋች ትክክል ነዉ ብለዉ የሚወሰዱት አንዱ የተሳሳተ አስተሳሰብ ብሄሮችን እንደ ተፈጥሮ ዝርያዋች አድረጎ መወሰድ ነዉ።። ልክ አንድ ዝርያ ድመት ወይም ዉሻ ነዉ ከሁለቱም ትንሽ ያለዉ እንደማይሆ ነዉ የሚታሰበዉ አንድ ሰዉ ብሄራዊ ማንነቱን በተመለከተ ወይ ካታላን ወይ ስፓንያርድ ነዉ ሁለቱንም ሊሆን አይችልም።። ይህ በእርግጠኝነት ስህተት ነዉ፣ አንድ ሰዉ ሁለቱንም መሆን ይችላል በትክክል እንዳየ ነዉ ብዙ ሰዋች በካቶሎኒያ ራሳቸዉን የካታሎን እና የስፓኒሽ ማንነቶች እንዳላቸዉ ነው የሚገልጹት (ምናልባት የተለያዩ የሁለቱን ማንነቶች ገጽታዋች ለተለያዩ አለማዋች እና በተለያየ ሁኔታዋች የተለያየ ትኩረት እየሠጡ እራሳቸዉን ሊገልጹ የሚችሉበት ሁኔታ ይኖራል)* "

ብዝሃ እና ተመጋጋቢ ማንነት ብዝሃነትን ላቀፈ አንድነት መሰረት የመሆኑን ያህል ለኢትዩጵያ ፌደሬሽን መሠረት መሆኑ አጠያያቂ አደለም።። በኢትዩጵያ ህብረ ብሄራዊ ዴሞክራሲያዊ ፌደራላዊ ሰርዓት የመገንባት ጉዳይ ከብዝሃ እና ተመጋጋቢ ማንነቶችን ከመገንባት ዉጭ ይታሰባል ተብሎ አይገመትም።። በመሆኑም ከብዝሃ እና ተመጋጋቢ ማንነት

አካያ ያለዉን አሰተሳሰብ እና ሁኔታ በየጊዜዉ እየዳበረ እንዲሄድ የሚያስችል በጥናት ላይ የተመሰረተ ስራዎች መሰራት ተገቢ ነዉ። በሀገራችን ነባራዊ ሁኔታ አንዱን ማንነት ጥሎ ሌለዉን አንጠልጥሎ ዴሞክራሶያዊ እና አካታች የሆነ ጠንካራ ሀገረመንግስት መገንባት የሚቻል አይሆንም ሁለቱንም ሚዛን ጠብቆ እና አመጋግቦ ይዞ መሄድ የግድ ይላል። ምክንያቱም የምንገኝበት 21 ኛዉ ክፍለ ዘመን የመብት ዘመን በመሆኑ የሁሉም መብት አንጻራዊ በሆነ መልኩ እኩል ባልተከበረበት ሁኔታ ሀብረ በሄራዊ ሆኖ በጋራ መቀጠል አስቸጋሪ መሆኑ የሚያጠራጥር አይደለም። በመሆኑም ብዝሃ እና ተመጋጋቢ የሆነ ማንነትን የአገራችን መገለጫ መሆኑ ከማህበራሰባዊ ዉቅራችን የሚመነጭ መሆኑን ተገንዝበን በዚያዉ ልክ አንድ ማንነት ብቻ የሚል የነጠለ ማንነት ትርክት ዘመኑን የማይዋጅ እና ከማህበረሰባችን ውቅር የተፋታ መሆኑን በውል መገንዘብ ተገቢ ነዉ። ፌደራላዊ አመራርም ይህን ባህሪ ተላብሶ ማህበረሰቡን መምራት እና ማስከተል ይጠይቀዎል።

ሌለዉ ጉዳይ ፌደራል አመራር በስርዓቱ ፍልስፍና እና እሳቤዎች ላይ ተቀራራቢ አረዳድ መያዝ እና ፍልስፍናውን እና እሳቤዉን መቀበል፣ ብዘሃነትን እንደ ዕድል ተቀብሎ ብዝሃነትን በአግባብ ለማስተዳደር የሚተጋ እና ለዚሁም የሚሆን አመለካከት እና ክህሎቶች እያዳበረ የሚሄድ፤ ሁሉንም ብሄር፣ ብሄረሰቦች በኩል አይን የሚመለከት፤ ለሁሉም የእኩል ተጠቃሚነት ዕድል መፍጠር ይገባል ብሎ የሚያምን እና ለዚሁ የሚሰራ፤ ለሀገመንግስታዊ ስርዓት እና ሀገመንግስታዊነት የቆመ እና ተግባሩም በዚህ የሚገለጽ፤ ችግሮች ሲያጋጥሙ ሀገመንግስታዊ ስርዓቱን እና በሕገመንግስቱ የተቋቋሙ ተቋማትን እና የአሰራር ስርዓቶች ተከትሎ ለመፍታት የሚጥር፤ በፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሰርዓት የሚያምን እና ለተግባራዊነቱ የሚተጋ፤ለሀገራዊ በሄራዊ ጥቅም የቆመ፤ ከሁሉም በላይ ሃገራዊ ብሄራዊ ጥቅምን የሚያስቀድም፣፤ ችግሮችን በውይይት፣ በምክክር፣ ስጥቶ በመቀበል በመፍታት የሚምን እና በተግባርም የሚገልፅ እንዲሆን ይጠበቃል።።።

ቢያንስ በንድፈ ሃሳብ ደረጃ ፌደራላዊ አመራር በትዕዛዝ ጉዳዩችን የማስፈጸም እድሉ አናሳ በመሆኑ የድርድር፤ ስምምነት የመፍጠር እና የመንግስታት ግንኙነትን የማስተዳደር ክህሎቶች ሊኖሩት ይገባል።

የፌደራል አመራር ሲባል የፌደራል ስርዓትን በትክክለኛ መንገድ ተግባራዊ ለማድረግ ከላይ እንደተገለጸዉ በተለያዩ ማህበረሰብ ክፍሎች ያለ አመራርን የሚያጠቃልል ሆኖ እያንዳንዱ የአመራር ክፍል ለፌደራል ስርዓቱ ስኬት ከላይ

የተዘረዘሩ ባህሪያትን እየተላበሰ መሄድ እና በተግባር መገለጫ ማድረግ ይጠበቃል። ምክንያቱም ያለ ፌደራላዊ አመራር ዉጤታማ የሆነ የፌደራላዊ ስርዓት መገንባት የማይቻል መሆኑ ከሌሎች ያልተሳካለቸዉ ፌደሬሽኖች ታሪክ የተረጋገጠ ነዉ ።

ክፍል **9**፣ ማጠቃለያ

የሃገራችን ኢትዩጵያ ማህበረሰባዊ ዉቅር ብዝሃነት የአቀፈና ማህበረሰቡም ይህን ብዝሃነት የህገሪቱ መገለጫ አድርጎ በመዉሰድ በደስታም ሆነ በሃዘን በአብሮነት የቀጠለ እና በዚህ ሂደትም ብዙ አኩሪ የጋራ ድሎችን ያስመዘገበ እና የተጋመደ ነዉ። በፌደራሊዝም ጥናት እደዚህ ያለ ማህበረሰብን ለመግለጽ ሊቪንግስተን (1965) እንደሚጠቀምበት ማህበረሰቡ "ፌደራላዊ ማህበረሰብ" ነዉ ብሎ መበየን ከእወነታ የራቀ ሊሆን አይችልም። ይህ ማህበረሰብ ያሉበት ተደራራቢ ችግሮችን በመፍታት ዘላቂ ሰላም የተረጋገጠበት፤ ዋስትና ያለዉ የዴሞክራሲያዊ ስርዓት የተገነባበት፤ ሁለንተናዊ ብልጽግና የተረጋገጠበት ጠንካራና እና አካታች የሆነ ህገር መንግስት ባለቤት ለማድረግ ለዚህ አይነት ማህበረሰብ የፌደራል ስርዓት የተሻለ አማራጭ መሆኑ በብዙ የዘርፉ ተመራማሪዎች የሚቀርብ ሃሳብ ነዉ። ይህ የፌደራል ስርዓት በትክክለና አቅጣጫ ለመመራት ሌሎች አሰፈላጊ የሆኑ ጉዳዩች እንደተጠበቁ ሁነው ብዘሃነትን በአግባቡ ማስተዳደር እና በፌደራል ስርዓቱ ዋነኛ ተዎናኝ –የሆኑት በየደረጀዉ የሚገኙ መንግስታዊ አስተዳደሮች መካከል ተቋማዊ የሆነ እና ዘርፈ ብዙ ግኙኙነቶች በማድረግ ፌደራል ስርዓቱ ያስቀመጣቸዉን ግቦች ለማሳካት በጋራ መስራት ይጠይቃል። ይህ ተግባር ለማከናወን የፌደራል ስርዓቱ የሚጠይቀዉን አዉቀት፣ክህሎት እና አመለካከት እየተላበሰ የሚሄድ ፌደራላዊ አመራር ወሳኝ ነዉ። እነዚህን ጉዳዩች ታሳቢ ባደረገ መልኩ በዚህ "በዝሃነትን ማስተዳደር እና የመንግስታት ግኙኙነት ለጠንካራ የፌደራላዊ ሥርዓት ግንባታ" በሚል ርዕሰ በተዘጋጀ የመወያያ ሰነድ ከላይ የተዘረዘሩ ርዕሰ ጉዳዩች በዝርዝር ቀርበዋል። ዋናዉ ጉዳይ ብዘሃነትን ከማስተዳደር አኳያ የሄድንበትን ርቀት የገጠሙን ተግዳሮቶች በመለየት ጥንካሬዎቻችን ለማስቀጠል እና ተግዳሮቶቻችን ለመሻገር የሚያስችሉ ተግባራትን ለማከናወን እንድንችል ሰነዱን መሰረት ባደረገ መልኩ በየከባቢዉ ያሉ ነባራዊ ሁኔታዎችን መሰረት አድርጎ ሰፊ ወይይቶችን በማድረግ አዳጊ ወደሆነ ተግባር ለመግባት የሚስችል መግባባትን መፍጠር ሲሆን የመንግስታት ግንኙነት በተመለከተ ግንኙነቱ ያለበትን ደረጃ፤ በግንኙነቱ የተከናወኑ የጋራ የልማት ስራዎች፤ የተፈቱ ችግሮች፤ ለመከላከል የተቻሉ ግጭቶች ወዘተ..

በየከባቢዉ በመፈተሽ ጥንካሬ እና ድክመቱን በመለየት ትምህርት ሊወሰድበት የሚችል ወይይት በማድረግ በቀጣይ የመንግስታት ግንኙነቱ ተቋማዊ ሆኖ በሚታወቅ እና በሚተነበይ መልኩ ተጨባች የጋር ልማት ዕቅዶችን እና ግቄቶችን አስቀድሞ ለመከላከል በሚያስችል መልኩ መፈጸም የሚስችል የጋራ መግባባት መፍጠር ይጠይቃል። መንግስታቱ በተለያዩ የጋራ ጉዳዩች ላይ በተለያዩ አግባቦች እየገናኙ ከመከሩ የፌደፈራል ስርዓቱ የሚያጋጥሙትን ተግዳሮቶች ስርዓቱን በሚያጠናክር አግባብ እየተሻገሩ በመሄድ –ጠንካራ እና ትክክለኛ የፌደራል ስርዓት በሃገራችን መገንባት ይቻላል። በመንግስታ ግንኙነት ዙሪያ ያየነዉን ግንዛቤ በማህበረሰቡ ውሥጥ እያሳደጉ መሄድም ማህበረሰቡ ከስርዓቱ ትግበራ ጋር ተያይዞ የሚጋጥሙትን ችግሮችን መንግስታቱ ተገናንተዉ ፌደራል ስርዓቱን እና አብሮነትን በሚያጠናክር፤ መተማመንን በሚያዳብር መልኩ እየፈቱለት እንዲሄዱ መጠየቅ የምንችልበትን አቅም ከመፍጠር በዘለለለ በሂደቱም ንቁ ተሳታፊ እንዲሆን ማድረግ ያስችላል። የመነግስታ ግንኙነት ከዛዉ ሳለ ብዝሃነትን ለማስተዳደር አንድ መሳሪያ ሆኖ ማገልገል ይችላል። ለምሳሌ በሁለት ክልሎች ወሰን አካባቢ የሚኖሩ ተቀረራቢ ቋንቋዎች የሚናገሩ፤ ተቀራራቢ ባህል የሚጋሩ ማህበረሰቦች የሁለቱ ክልሎች የግንኙነት ድልድይ በማድረ ኢከኖሚያዊና ማህበራዊ ልማቶችን በጋራ በመስራት እና በጋራ ተጠቃሚ በማድረግ ክልሎቹ በሚያደርጉት ግኝኑነት በሁለቱም ክልሎቸ ወሰን አካባቢ የሚኖሩ ማህበረሰቦች ብዝሃነት ባቀፈ መልኩ ግንኑነቱን መምራት ያስችላል። እንደ ሃገር ያለዉን ብዝሃነት ለማስተዳደር እና ብዝሃነትን በጋራ ለማክበር የመንግስታ ግንኙነትን እንደ አንድ መሳሪያ መጠቀም ያስችላል።

በመጨረሻም በሃገራችን ብዝሃነትን ከማስተዳደር አኳያ በክልሎች፤ በዞኖች፤ ወረዳዎች እና ቀበሌዎች አካባቢ ያለበትን ሁኔታ በመዳሰስ ሰው የመኖሪያ ከባቢዉ በቀበሌዉ በመሆኑ ቀበሌዉ ላይ ብዝሃነትን መቀበል እንደ አንድ መሬት ላይ ያለ እዉነታ በመወሰድ ብዝሃነትን በየደረጃዉ የበለጠ ማስተናገድ የሚታዩ ተግዳሮቶች በዉይይት፤ በአካታችነትና በአብሮነት እሳቤ መሻገር ይገባል።

ዋቢ መጻሕፍት (References)

- Agranoff Robert, (2004). Autonomy, devolution, and intergovernmental relations. *Regional and Federal Studies. 14,* pp. 26–65.

- Arora Balveer (2010). Republic of India. In: Luis Moreno and Cesar Colino (eds.). *Diversity and Unity in Federal Countries*. McGill, Queen's University Press, pp 200--226
- Benson David and Jordan Andrew, (2006). Exploring the Tool-kit of Europea Integration Theory: What Role for Cooperative Federalism? Journal of *European Integration*. 33(1), pp. 1-17.
- Bolleyer Nicole, (2009). *Intergovernmental Cooperation: Rational Choices in Federal System and Beyond*. New York: Oxford University press.
- Bolleyer Nicole, (2006).Consociationalism and Intergovernmental Relations –Linking Internal and External Power-Sharing in the Swiss Federal Polity. *Swiss Political Science Review.* 12(3), pp. 1-34.
- Boex Jamie and Martinez-Vazquez, (2006). *Designing Intergovernmental Equalization Transfers with Imperfect Data: Concepts, Practices, and Lessons*. Unpublished Manuscript. Andrew Young School for Policy Studies: Georgia State University.
- Braun Dietmar (2009). Constitutional Change in Switzerland. *Publius:TheJournalofFederalism 39(2), pp.314-340*
- Broadway Robin and Frank Flatters, (1982). Efficiency and Equalization in a Federal System of Government: A Synthesis and Extension of Recent Results. *Canadian Journal of Economics,* 15(4), pp. 613-33.

- Burgess, Michael (2006) *Comparative federalism: theory and practice*. Abingdon: Rutledge.
- Burgess (2012). *In Search of the Federal Spirit: Theoretical and Empirical Perspectives in Comparative Federalism.* Oxford University Press, Oxford
- Deutsch Morton, (2006). 'Cooperation and Competition.' In: Morton Deutsch, Peter T. Coleman and Eric C. Marcus (eds.). *The Handbook of Conflict Resolution Theory and Practice* 2nd ed. San Francisco: Jossey-Bass.
- Duchacek Ivo D (1977). Antagonistic Cooperation: Territorial and Ethnic Communities. *Publius , The Journal of Federalism, The Center for The Study of Federalism,* pp 1-29
- Elazar Daniel, (1987). *Exploring Federalism.*: University of Alabama Press, Tuscaloosa.
- Filippov Mikhail, Ordeschook Peter C. and Shevtsova Olga, (2004). *Designing Federalism: A Theory of Self-Sustainable Federal Institutions*. New York: Cambridge University Press.
- Intergovernmental Relations Framework Act of the Republic of South Africa, Act No.13/2005, Department of Provincial and Local Government.
- Kalu John Otisi (2016). True Federalism? Illustrations With The Venn Diagram. European Scientific Journal, 12: 8. pp 344-365

- Kincaid John, (2000). 'Intergovernmental Relations in the United States of America.' *In*: J. Peter Meekison (ed.). *Intergovernmental Relations in Federal Countries, A Series of Essays on the Practice of Federal Governance*. Ottawa: Forum of Federation, pp.33-44.
- Kincaid John, (2008). 'Three Faces of Contemporary American Federalism.' *In*: Morgan Iwan W. and Davies Philip J.(eds.). *The Federal Nation: Perspectives on American Federalism*. New York: Algarve Macmillan.
- Meekison J.Peter , (2000),' Interoduction .'*In*: J. Peter Meekison (ed.). *Intergovernmental Relaticons in Federal Countries, A Series of Essays on the Practice of Federal Governance*.Ottawa: Forum of Federation, pp. 71-90.
- Fisterer Thomas (2015). Intergovernmental Relations in Switzerland: An Unfamilar Term for for a Necessary Concept: In Johanne Poirier, Cherly Saunders and John Kincaid (eds.) *Intergovernmental Relations in Federal Systems,* Canada, Oxford Unversity Press.
- Poirier Johanne and Saunders Cheryl (2015). Conclussion: Comparatice Experience of Intergovernmental Relations in Federal Systems: In Johanne Poirier, Cherly Saunders and John Kincaid (eds.) *Intergovernmental Relations in Federal Systems,* Canada, Oxford Unversity Press.

- Sbragia Alberta M., (2006). 'American Federalism and Intergovernmental Relations.' *In:* Rod Rhodes and Sahara Binder (eds.).*The Oxford Handbook of Political Institutions*. Great Britain: Oxford University Press, pp.239-260.
- Simeon Richard (2009). Constitutional Design and Change in Federal Systems: Issues and Questions. *Publius: The Journal of Federalism* volume 39, number 2, pp.241-261.
- Singh M. P and Saxena Rekba (2015). Intergovernmental Relations in India: From Centralization to Decentralization. In: Johanne Poirier, Cherly Saunders and John Kincaid (eds.). *Intergovernmental Relations in Federal Systems,* Canada, Oxford Unversity Press.
- Shah Anwar, (2007). 'A Practitioner's Guide to Intergovernmental Fiscal Transfers.' *In*: Robin Boadway and Anwar Shah (eds.). *Intergovernmental Fiscal Transfers: Principles and Practice*. Washington, D.C.: The World Bank.
- The Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia. Federal Negarit Gazeta, 1st Year No.1, 21st August 1995
- Watts R.L., (2008). *Comparing Federal Systems.* 3rd. ed. Montreal and Kingston: McGill Queen's University press.
- Watts R. L, (2001). 'Intergovernmental Relations: Conceptual Issues.' In: Levy Norman and Tapscott (eds.). *Intergovernmental Relations in South Africa: The Challenge of Co-operative Government*. Cape Town: School of Government University of the Western Cap.

- Wibbels Erik, (2005). *Federalism and the Market: Intergovernmental Conflict and Economic Reform in the Developing World*. New York: Cambridge University Press.
- Wright Deil S. and Cho Chung-Lae, (2000). 'State Administration and Intergovernmental Interdependency: Do National Impacts on State Agencies Contribute to Organizational Turbulence?' *In*: John J. Gargan. *Handbook of State Government Administration*. New York: Marcel Dekker, Inc,
- Wright Deil S., (1974). Intergovernmental Relations: an Analytical Overview, *The Annals of the American Academy of Political and Social Science. 416* (1), pp. 1-16.
- Zimmerman Joseph, (2001). National-State Relations: Cooperative Federalism in the Twentieth Century. *Publius: The Journal of Federalism,* 31(2), pp. 15-30.
- **በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የመንግስታት ግንኙነት ስርዓትን ለመወሰን የወጣ አዋጅ** 1231/2013. **ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ሃያ ሰባተኛ ዓመት ቁጥር** 7 **ጥር** 3 **ቀን** 2013
-
- Watts, Ronald L. (2008). *Comparing federal systems* 3rd ed. Kingston Queen's University Press.
- Livingston, W.S. (1956). *Federalism and Constitutional Change*, Oxford: Clarendon Press.
-